አል ዑዝር ቢል ጀህል

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው።

ምስጋና የዓለማት ጌታ ለሆነው አላህ የተገባ ነው። የአላህ ውዳሴና ሰላም በነቢዩ ሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ ዕለተ ቂያማ ድረስ መንገዳቸውን በተከተለ ሁሉ ላይ ይስፈን።

በመቀጠል አዩሃል ሙስሊሙን! ዛሬ ላይ ኡመተል ኢስላም ከክህደት ባለቤቶችና ከተከታዮቻቸው በሚሰነዘር ርህራሄና ምህረት የለሽ እንዲሁም አውዳሚና ሀይለኛ ለሆነ የቁስና የአመለካከት ዘመቻ የተጋለጡ መሆናቸው ከብዙዎች የሚሰወር አይደለም። በምዕራባዊያን ከሃዲዎች ሴራ ጠንሳሽነትና አቀጣጣይነት በርካታ ሀገራት ፈርሰዋል፤ በርካታ የሰው ልጆች እልቂትና የንብረት ውድመት ደርሷል፣ የልጃገረዶችና እናቶች ክብርም ተደፍሯል፤ በተለይም ከሌሎች ዓለማት ይልቅ ሀገራቸው የጦርነት አውድማ የሆኑ የኢስላምና የዐረብ ሀገራት ይህን የከሃዲዎች መጥፎ ፅዋ ቁጥር አንድ ተጎንጪዎች ሆነዋል። ይህ ሳያንሳቸው ከውድመቱ በኋላ የተጋጩትን አስታራቂ፣ የተራቡትን አጉራሽ፣ የታረዙትን አልባሽ እና የተጎዱትን አካሚ መስለው የሙስሊሞችን እምነትና ጥብቅነት ጥቂት በሆነ ዱንያዊ ጥቅማጥቅም ለማስቀየር የአከፍሮት ተልእኮን ባነገቡ በርካታ ድርጅቶቻቸው በኩል ሊዘምቱ ዳግም ወደ ሀገራቱ ይገባሉ። ኩፋሮች ሙስሊሙን ማህበረሰብ እንዲህ መቀራመታቸው የነቢዩ ሙሐመድን ﷺ መልእክተኛት ከሚያመላክቱ ክስተቶች የሚመደብ ነው። ምክንያቱም ኢማሙ አሕመድ (22397) እና አቡ ዳውድ (4297) ሠውባን ረዲየላሁ ዐንሁን በመጥቀስ ባስተላለፉትና ኢማሙል አልባኒ "አስ ሰሒሓ" (8183) ላይ ሰሒሕ ባደረጉት ሐዲሥ ላይ የአላህ መልእክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋልና፦

يُوشِكُ الْأُمَمُ أَنْ تَدَاعَى عَلَيْكُمْ كَمَا تَدَاعَى« الْأَكَلَةُ إِلَى قَصْعَتِهَا» فَقَالَ قَائِلٌ :وَمِنْ قِلَّةٍ نَحْنُ يَوْمَئِذٍ؟ قَالَ" :«بَلْ أَنْتُمْ يَوْمَئِذٍ كَثِيرٌ وَلَكِنَّكُمْ غُثَاءٌ كَغُثَاءِ السَّيْلِ، وَلَيَنْزِعَنَّ اللهُ مِنْ صُدُورِ عَدُوِّكُمُ الْمَهَابَةَ مِنْكُمْ وَلَيَقْذِفَنَّ اللهُ فِي قُلُوبِكُمُ الْوَهْنَ » فَقَالَ قَائِلٌ :يَا رَسُولَ الله، وَمَا الْوَهْنُ؟ قَالَ :«حُبُّ الدُّنْيَا وَكَرَاهِيَةُ الْمَوْتِ

"ተመጋቢዎች (ምግብ የያዘ) ትሪ ላይ እንደሚጠራሩት (እንደሚረባረቡት) አምሳያ ህዝቦች በናንተ ላይ የሚጠራሩባችሁ (የሚረባረቡባችሁ ጊዜ ሊመጣ) ይቀርባል" አሉ። ከሰሓቦች አንዱ እንዲህ ሲል መልእክተኛውን ﷺ ጠየቀ: "(ይህ የሚሆነው) ያኔ በቁጥር አናሳ ስለምንሆን ነውን?" መልእክተኛውም ﷺ "ያኔ

እናንተ ብዙ ናችሁ፤ ነገር ግን ጎርፍ (እያንከባለለ እንደሚነዳው) አረፋና ምናምን ናችሁ፤ ያኔ አላህ ከጠላቶቻችሁ ልቦች ውስጥ ለናንተ የነበራቸውን ፍርሃት ያነሳና ልቦቻችሁ ውስጥ ወህንን ይጥላል።" አሉ። አንዱ ሰሓቢይም እንዲህ በማለት (በድጋሚ) ጠየቀ: "የአላህ መልእክተኛ ሆይ ወህን ምንድን ነው?" መልእክተኛውም ﷺ "ዱንያን መውደድና ሞትን መጥላት ነው" በማለት መለሱ።

ይህ አይነቱ የኩፋሮች ዘመቻ በሙስሊም ሀገራት ላይ ብቻ ያጠረ አይደለም፤ ይልቁንም እንደ ሀገራችን ኢትዮጵያ ያሉ ሀገራት ውስጥም ተመሳሳይ የእርስበርስ ጦርነት እንዲካሄድ በማድረግ ከፍተኛ እልቂትና ውድመት ያደርሳሉ። በተለይ ደግም ሙስሊም ማህበረሰብ የሚበዛባቸው አካባቢዎች በተደጋጋሚ የጦርነቱ አውድማ ሆነው በርካታ የሰው ህይወት ይቀጠፋል፤ ቤት ንብረቶችም ይወድማሉ። ከዚያም የምእራባዊያን ቅጥረኞች የሆኑ የአክፍሮት ሀይላት በበጎ አድራጊ ስም ወደ ቀጠናዎቹ በመትመም ሙስሊሙን ኡማ እምነቱን ሊነጥቁት ሲለፉ ይታያሉ።

ሙስሊም ማህበረሰቡ ይህን ሁሉ ዘመቻ ተቋቁሞ በጥቅማጥቅማቸው ሳይታለል ፀንቶና ሀይማኖቱን አጥብቆ እንዲይዝ የሚያስችለው ከሚመለከታቸው አካላቶች በቂ የሆነ ደፅዋና ድጋፍ ባላገኘበት ሁኔታ ራሳቸውን ብቻ ትክክለኛ ሙስሊሞች በማድረግ ሌላውን ማህበረሰብ ከኢስላም የወጣ ከሃዲ (ሙርተድ) አድርገው የሚያምኑ ሌሎች የጥፋት አካላቶች ተነስተውም "አንተ ካፊር ነህ፤ እገሌ ካፊር ነው፤ ሸህ እገሌም ሙርተድ ነው፤ እገሊት ጀማዓም ፣፣፣ ሁሉም ኩፋሮች ናቸው። " ሲሉ እንመለከታለን። ሆኖም አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ ከእኛ ይበልጥ ለዲኑ "ሻይራ" (ቅናቻ) ስላለውና ዲኑን ለመጠበቅ ዋስትና የወሰደ ስለሆነ በየዘመናቱ ከዲነል ኢስላምና ከሙስሊሞች የሚከላከሉ ዑለማኦችንና ዱዓቶችን ያመጣል። ኢማሙ አሕመድ ኢብኑ ሐንበል አላህ ይዘንላቸውና እንዲህ ይሉ እንደነበረው ማለት ነው:-

الحمدُ للهِ الذي جعلَ في كلِّ زمانٍ فترةٍ من الرُّسل بقايا من أهل العلم، يدعون من ضلَّ إلى الهدى، ويَصْبِرون منهم على الأذى، يُحْيون بكتاب الله المَوتى ويُبَصِّرون بنور الله أهلَ العَمى، فَكَم مِن قتيلٍ لإبليسَ قد أَحْيَوْه، وكم من ضالٍّ تائهٍ قد هَدَوْه، فما أحسنَ أثرَهم على الناس وأقبحَ أثر الناس عليهم ! يَنْفُون عن كتاب الله تحريفَ الغالين وانتحالَ المُبْطِلين وتأويلَ الجاهلين...

الرد على الجهمية والزنادقة للإمام أحمد رحمه الله

«የመልእክተኞች መልሳክ በሚቋረጥበት በእያንዳንዱ ክፍት ዘመን ውስጥ መንገድ የሳቱ ሰዎችን ወደ ትክክለኛው የኢስላም ጎዳና የሚጣሩ፣ ከነሱም የሚደርስባቸውን መከራ በትእግስት የሚያሳልፉ፣ በአላህ መፅሀፍ (ቁርኣን) የቁም ሙታንን ህያው የሚያደርጉ፣ አይናማ እውራኖችንም በአላህ የእውቀት ብርሃን የሚመሩ ቀሪ ዑለማኦችን ላደረገልን (ላመጣልን) አላህ ምስጋና ይገባው። ስንቱን የኢብሊስ ምርኮኛ ህያው አደረጉት! ቀጥተኛውን መንገድ የሳተና የጠመመውን ስንቱን ሰው ወደ ቅኑ መንገድ መሩት! ለሰዎች የዋሉት መልካም ውለታና (ጥለውት የሚያልፉት መልካም አሻራ) ምን ያህል የሚያምር ነው! ሰዎች በእነሱ ላይ የሚያሳርፉት አሻራ ደግሞ ምን ይህል የሚያስጠላ ነው!! (እነዚህ ዑለማኦች) ድንበር አላፊዎች በአላህ መፅሀፍ ላይ የሚፈፅሙትን ማዛባት፣ የባጢል ሰዎችን አስመሳይነትና መሃይማን ያለ እውቀት የሚናገሩትን ትክክለኛ ያልሆነ ፍች ያወግዛሉ።»

"አር ረድዱ ዐለል ጀህሚያ ወዘናዲቃ" የሚለው የኢማም አሕመድ ኪታብ መግቢያ ላይ ተወስቷል።

ወጣቱን ክፍል ከቅኑ መንገድ በማራቅ ሙስሊሞችን እንዲያከፍሩ፣ ሐራም የሆኑ ደሞቻቸውን፣ ንብረቶቻቸውንና ክብሮቻቸውንም ሐላል አድርገው እንዲመለከቱ የሚያነሳሳ የሆነውና ህዝበ ሙስሊሙ ውስጥ የተከሰተው የተከፊርን እንቅስቃሴ ለማምከን ከድሮ ዘመን አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ ያሉ ዑለማኦች ያላሰለሰ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል፤ ተከፊር የሚባለው መርዝ የሚያስከትላቸውን መጥፎ ውጤቶች ሸሪዓዊ በሆኑ መነሻዎች በመደገፍ በተለያየ ቋንቋና በተለያየ መንገድ ለህዝበ ሙስሊሙ እውቀትና ግንዛቤ ሲያስጨብጡም ይታያሉ።

ወላሂ ያሳዝናል!! ገና የቁርኣንን ለፍዝ (ቃል) እንኳ በቅጡ መቅራት የማይችሉ፣ ስለ ተውሒድና ሽርክ፣ ስለ ጦሃራ፣ ስለ ውዱእና ሰላት እንዲሁም ስለሌሎች መሰረታዊ የኢስላም ጉዳዮች በቂ እውቀት የሌላቸው ወጣቶች ለዚህ አደገኛ የተከፊር ፈለግ ሰለባ ሆነው ታላላቅ የኢስላም ሊቃውንቶችን ሳይቀር ሲያከፍሩ ስታይ በጣም ታዝናለህ ትፈራለህም።

የአክፍሮት ሀይሎች ስለ ዲኑ በቅጡ ግንዛቤ የሌለውን ሙስሊሙን ማህበረሰብ እዚህ ግባ በማይባል ስጦታ እያባበሉና እየሸነገሉ እምነቱን ሲነጥቁት፤ ራሳቸውን ብቸኛ ሙስሊም አድርገው የሚያዩት ተከፊሮችና መሰሎቻቸው ደግሞ ባለማወቁ ምክንያት ከኢስላም ጋር የሚፃረርን ተግባር የሚፈፅምን በቂ ሑጃ ያልደረሰውን ሚስኪን በርህራሄ፣ ጥበብ በተሞላበትና በመልካም ግሳቤ ሳያስተምሩትና መረጃ

ሳያቆሙበት እንዲሁ ጥፋቱን በመፈፀሙ ብቻ ካፊር (ሙርተድ) ሆነሃል በማለት እምነቱንና ኢስላሙን ይቀሙታል።

እናም የአላህ ፍቃድ ከሆነ የሙስሊሙ ማህበሰረብ በተለይም ወጣቱ ክፍል ከእንዲህ አይነት ዋልታ ረገጥ አስተሳሰብ ርቆ ዲኑን ከትክክለኛ የሱንና ዑለማኦች በመቅሰም አቋሙንና እምነቱን እንዲያስተካከል፣ ውስጣዊ አንድነቱና ትስስሩ ተበራቶ ተውሒድ ለመላው ህዝበ ኢስላም ተደራሽነት እንዲኖረው፣ ሺርክና ቢድዓዎችም እንዲወገዱ በቻለው አቅም ሁሉም የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ አደራ ከማለቴ ጋር የዚህ አደገኛ የተከፈር እንቅስቃሴ መግቢያ በር ስለሆነውና “ዑዝር ቢል ጀህል” ስለሚባለው ጉዳይ በተለያዩ ኢጋጣሚዎች የፃፍኳቸውን ፅሁፎች በአንድ ሪሳላ ልሰብስባቸው ወደድኩ። በሪሳላው ውስጥ፡-

• በቅድሚያ ሰዎች ካሉበት ሁኔታ ደረጃ በደረጃ ወደ ተከፈርነት እንዴት እንደሚሸጋገሩ ተዳሶበታል።

• በዑዝር ቢል ጀህል ዙሪያ የተሰጡ የተወሰኑ ዑለማኦች ፈታዋዎችም በሀገረኛ ቋንቋ ተተርጉመው ተወስተውበታል።

• እንዲሁም ተከፈሮችና መሰሎቻቸው ለአቋማቸው መነሻ አድርገው ስለሚያቀርቧቸው አንዳንድ መደገፊያዎችና ማምታቻዎች ዑለማኦች ካዘጋጇቸው ኩቱቦችና ረሳኢሎች በመያዝ ሰፋ ባለ መልኩ መልስ ተሰጥቶባቸዋል።

ለምሳሌ ያህል፡-

• ኢስላም ትክክለኛ ሀይምኖት ነው በሚል ዲን አድርገው ይዘውት ነገር ግን ባለማወቃቸው ምክንያት ሺርክ የሚሰሩ አካላትንና ኢስላምን ሙሉ በሙሉ ያልተቀበሉ የቀድሞዎቹ የዐረብ ሙሽሪኮችን አንድ አድርገው ማየታቸው፤

• ሰዎች ላይ በግልፅ (በዚሂር) በታየው መበየንን በተመለከተ፤ ማለትም እነሱ እንደሚሉት ሽርክ ሲሰራ በገሃድ የታየ ሰው ሙሽሪክ ተብሎ ይተሓከምበታል በሚለው መነሻቸው ዙሪያ፤

• እንዲሁም መስአላ ዚሂራና ኸፊያ ስለሚባሉት የተከፈር ምሽጎች ዙሪያ ሰፋ ባለ መልኩ ተዳሶበታል። ወሏሁል ሙስተዓን።

ተንቢህ: የአላህ ፍቃድ ከሆነ ወደፊት ከተወሰነ ጭምርማሪዎች ጋር በተሻለና ሰፋ ባለ መልኩ ለማቅረብ እሞክራለሁ።

هذا وأسأل الله عز وجل أن يجعل رسالتي هذه خالصة لوجهه ونافعة لعباده، وأن يبصِّر الأمة الإسلامية، ويهدي ضُلَّالها، ويعيدهم إلى رشدهم إنه ولي ذلك والقادر عليه

وكتب :أبو عبد الله سعيد بن محمد بن أحمد السلفي

***** ***** ***** *****

ወንድሞች ሆይ!

ብዙውን ጊዜ በተውሒድና በዐቂዳ ስም ዐዝር ቢልጀህል የሚባለውን መስአላ ሽፋን በማድረግ ከሚነሱ ንቅናቄዎች የተነሳ በርካታ ወንድሞቻችን ወደ ተክፊር መንሀጅ የሚንነድዱ መሆናቸው ከብዙዎቻችን የማይሰወር እውነታ ነው።

ጅማሯቸው ላይ "ዐዝር ቢል ጀህል የሚባለው ጉዳይ መስአላ ኺላፊያ ስለሆነ አይለያየንም፤ አብረን ከመጓዝም አያግደንም" ይሉ ይሆናል። ነገር ግን በጊዜ ሂደት ቀስ በቀስ ነጥቡን ያላቅሙ በማሸከምና በመለጠጥ ጉዳዩን ከባድ ዐቂዳዊ ጉዳይ ያደርጉትና ማባሪያ ወደሌለው የተክፊር ፊትና እና ረብሻ ይቀየራል።

እንደሚታወቀው ሸይጧን ዐለይሂ ለዕነቱላህ አንድን ሰው ወደ ሆነ ከባድ ጥፋት በቀጥታ አይወረውረውም። ይልቁንም በመጀመሪያ ወደ ጥፋቱ አድራሽ ከሆኑ መግቢያዎች ቀለል ወዳለው መንደርደሪያ ጎራ እንዲል ይጋብዘዋል፤ ቀስ እያለም እንዲላመድ ያደርገዋል፤ ከዚያም እንዲሁ እያለ ወደ ቀጣዩ ከዚያም ወደ ቀጣዩ በመጨረሻም ሳያስበው ነፍሱን እዚያ ከባድ ጥፋት ላይ ሆና ያገኛታል።

ለምሳሌ ያህል አንድ ሰው ዝሙት ላይ ከመውደቁ በፊት ሸይጧን በርካታ ሙቀዲማዎችን እንዲያልፍ አድርጎ ነው በመጨረሻ ዝሙት ላይ እንዲወድቅ የሚያደርገው። እንደተባለውም፦

نَظْرَةٌ فَابْتِسامةٌ فَسَلامٌ فَكَلامٌ فَمَوْعِدٌ فَلِقَاءُ

"ቅድሚያ እንዲመለከታት ያደርገዋል፤ ቀጥሎ ፈገግ እንዲላት ያነሳሳዋል፤ ከዚያም ሰላምታ ያለዋውጣቸዋል፤ ይህን ሲላመዱትም የሞቀ ወሬ ይጀመራል፤ ከዚያም ቀጠሮ ያቀጣጥራቸውና በስተመጨረሻም ነፍሱን ዝሙቱ ላይ ወድቃ የሚያገኛት ይሆናል።"

ሸይጧን ሰውዬው እንደማይቀበለው ስለሚያውቅ መጀመሪያውኑ በቀጥታ ዝሙት ላይ እንዲወድቅ አያዘውም። ይልቁንም እነኚህን መንደርደሪያዎች

ቀስበቀስ እንዲያልፍባቸው ይገፋፋዋል ማለት ነው። ልክ እንደዚሁ ተከፊሪዮች (የሰው ሽያጢኖች) አንድን በሱንና ላይ ያለን ወንድም መጀመሪያ ዑለማኦችንና ተማሪዎቻቸውን በቀጥታ እንዲበድዕና እንዲያከፍር አይጋብዙትም። ኢብኑ ተይሚያ፣ ኢብኑል ቀይዩም፣ አልባኒ፣ ኢብኑ ዐሠይሚን፣ ሙቅቢል፣ ሙሐመድ አማን አልጃሚና የመሳሰሉትን ኡለማዎች ከጀህሚያ የማይሻሉ ሙርጂኣዎች ናቸው ብለውም ቅድሚያውኑ እርኩስ እይታቸውን ይፋ አያደርጉለትም። ምክንያቱም ስለሚሸሻቸውና ስለሚጠነቀቃቸው ማለት ነው።

ነገር ግን ኢብሊስ ዐለይሂ ለዕነቱሏህ: "ኢንኒ ለኩማ ለሚነንናሲሒን" እያለ ኣደምና ሐዋእን እንዳሳሳተው እነሱም "እኛ ላንተ ኸይር የምንሻ መልካም መካሪዎችህ ነን" በሚል ነው የሚቀርቡት። ከዚያም ቀስበቀስ እያለማመዱ እቅዳቸውን ተግባራዊ በማድረግ እንደነሱ እንዲሆን ያበቁታል።

ተከፊሪዮች ራሳቸው ሲጠምሙና ሰዎችን ሲያጠሙ የሚያልፉባቸው መራሒሎች

• በቅድሚያ ዑዝር ቢል ጀህል የለም የሚለው ጉዳይ ቁርኣንና ሐዲሥ የሚደግፉት መሆኑንና ጀግኖቹ የነጅድ ዑለማዎችም የሚያራምዱት መሆኑን በማወጅ፤ "እኛ ዑዝር ቢል ጀህል አለ የሚሉ ዑለማኦችን ሙርጂኣ፣ ሙብተዲዓ ፣፣፣ አንልም፤ ነገር ግን ለእነሱ ካለን ክብር ጋር ተሳስተዋል እንላለን።" ይላሉ።

• ከዚያም መስአላው የዕለት ተዕለት ህሳብና ወሬያቸው ሆኖ ከዚህም ከዚያም ጋር በመከራከር ጉዳዩን በየቦታው ያራግቡታል። አለፍ ይሉናም: "መስአላው ኢጅማዕ አለበት፤ በጉዳዩ የመጡ መረጃዎችም እውሮች ዘንድ እንጂ ለሁሉም ሰው ግልፅ ናቸው፤ ሆኖም ዑዝር አለ የሚሉ ዑለማኦችን ሙብተዲዕ አንልም፤ ነገር ግን አጠንክረን በመቃወም መሳሳታቸውን ከመግለፅ ወደኋላ አንልም። ምክንያቱም ጉዳዩ የዐቂዳና የተውሒድ ጉዳይ ነውና። እነዚህ ኡለማኦች ምን ያህል ብናከብራቸውም ከተውሒድ አይበልጡም።" ይላሉ።

• ከዚያም ዑዝር ቢልጀህል አለ በማለት የሚቃወሟቸውን አካላት "የኢርጃእ ሹብሃ የተጠናወታቸው ልፍስፍሶች፣ ፈሪዎች፣ ዐቂዳ ያልገባቸው ሙንሐሪፎች፣ የቀብር አምላኪዎችና የሙሽሪክ ጠበቃዎች" ወደ ማለት ይራመዳሉ።

• እየቆዩም ዑዝር አለ የሚሉ ዑለማኦችን "እነ ሸህ እገሌ በዚህ፣ በዚህ የእውቀት ዘርፍ ጎበዞች ነበሩ፤ ነገር ግን በዐቂዳ ላይ ጥንካሬያቸው እንደ ጀግኖቹ ነጅዲዮች አይደለም፤ ያግራራሉ፤ የኢርጃእ ሹብሃ ገብቶባቸዋል፤ በዚህ አቋማቸውኮ

የተልፈሰፈሰና የላሸቀን ትውልድ ነው የሚያፈሩት፣፣፣ " እያሉ መቆንጠጥ ይጀምራሉ።

• የእነዚህን ዑለማኦች ንግግር እያጣቀሱ አቋማቸውን የሚያራምዱ ዱዓቶችንና ተማሪዎችንማ ከጀህሚያ የማይሻሉ የለየላቸው ሙርጂኣዎች አድርገው ነው የሚቆጥሯቸው።

• በመቀጠል የተከታዮቻቸውን ስነ ልቦና እያጤኑ እነኚህን ዑለማኦች ዐቂዳ ያልገባቸው ሙርጂአቱል ዐስር፣ ሙብተዲዓ፣ ዱልላል ፣፣፣ እያሉ በገሃድ መዘርጠጥ ይጀምራሉ።

• ዑዝር ቢል ጀህል አለ ከሚሉ ከእንዲህ አይነት ዑለማኦችና የነሱን ፈታዋ ከሚያራግብ ሰው ጎላ ሰላት መስገድ እንደማይበቃም ያውጃሉ።

• ከዚያም «እነዚህ ዑዝር ቢል ጀህል አለ በማለት ለቀብር አምላኪዎችና ለሙሽሪኮች ጠበቃ የሆኑ ዑለማኦችና ተማሪዎቻቸው ጥሪት ያሉ ካፊሮች ናቸው። ምክንያቱም ከሙሽሪኮች ዲፋዕ የሚያደርጉ (የሚከላከሉ) እና የነሱ ረዳቶች ስለሆኑ፤ አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ ደግሞ እንዲህ ብሏል:

وَمَنْ يَتَوَلَّهُمْ مِنْكُمْ فَإِنَّهُ مِنْهُمْ

سورة المائدة :٥١

{ከናንተም ውስጥ እነሱን (ከሃዲዎቹን) የሚወዳጃቸው (ረዳቶች የሚያደርጋቸው) ሰው እሱ ከእነሱ ነው} ወደማለት ይሸጋገራሉ።

N.B ተከፊሪዮች ለአቋማቸው ማጠናከሪያ የሚያቀርቧቸው የቁርአን አንቀፆች ምን እና ማን እንደተፈለገባቸው ከሰለፎች የተወሰደ ዕውቀት ስለሌላቸውና ጁህሃል ስለሆኑ ብዙ ጊዜ አንቀፆቹን ካለቦታቸው ሲጠቀሙ ይስተዋላሉ። ይህም አንድ ማሳያ ነው።

• በመጨረሻም የተከፊሩን ምህዳር ሰፋ አድርገውት «እነኚህን ከሃዲዎች (ዓዚሮቹንና ተከታዮቻቸውን ማለታቸው ነው) ካፊር አድርጎ የማያይ ሁሉ እራሱ ካፊር ነው። ምክንያቱም

(من لم يُكفِّرِ الكافِرَ فَهَو كافرٌ)

(ካፊርን ካፊር የማይል እሱ እራሱ ካፊር ስለሚሆን)» በማለት ከመሰሎቻቸው በስተቀር ኡማውን በመደዳ አክፍረውት እርርፍፍ ይላሉ!!

• ጉዞው በዚህ አይቆምም ይልቁንም እነኚህ የተከፈሩ አካላት በተከፊሮች እይታ ከሰለሙ በኋላ ሙርተድ የሆኑ ሰዎች ስለሆኑ ደማቸውና ገንዘባቸው ሐላል ይሆናል። (እንደሚሉት ከሆነ) ሀይል ቢያገኙ ከሌሎች አካላት በፊት ዘመቻ በእነዚህ ሙርተድ ባደረጓቸው አካላት ይጀምራሉ!! በጥቅሉ የድሮዎቹ ኸዋሪጆች ወይም የዛሬዎቹ አይ ኤስ ኤስ ኮፒ ወደ መሆን ይሸጋገራሉ ማለት ነው።

በዑዝር ቢል ጀህል ዙሪያ የመጡ የተወሰኑ ዑለማኦች ፈታዋ

①

ከዘመናችን ታላላቅ ዑለማኦች አንዱ የነበሩት ሸይኽ ሙሐመድ ኢብን ሷሊሕ አል ዑሠይሚን "ዑዝር ቢል ጀህልን" በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ:

ጥያቄ: የሙርጂኣዎች ብይን ምንድን ነው?

"ዑዝር ቢልጀህል አለ" የሚሉ ሰዎችን የሙርጂኣዎችን መንገድ ገብተዋል በማለት የሚገልፁ አካሎችስ ብይን ምንድን ነው?

መልስ: በመጀመሪያ ደረጃ ሙርጂኣዎች እነማን እንደሆኑ ማወቅ ግድ ይለናል። ሙርጂኣዎች ኢማን ማለት የልብ ስራ ነው በማለት እምነትን ያለ አካላዊ ተግባርና ያለ ንግግር በልብ እምነት ብቻ የሚገለፅ ነው የሚሉ ናቸው። ይህ አባባላቸው በማያጠራጥር መልኩ ውድቅ የሆነ ንግግር ነው። ምክንያቱም ከቁርአንና ከሐዲሥ መረጃዎች ጋር የሚፃረር ነውና።

ዑዝር ቢል ጀህል (አንድ ሰው ባለማወቁ ምክንያት ወንጀል ላይ ሲወድቅ ዑዝር መስጠት) የቁርአንና ሐዲሥ ጥቅል መረጃዎች የሚያስፈርዱት (የሚያመላክቱት) ጉዳይ ነው።

ዑዝር ቢልጀህል የለም ለማለት ወይም አንድ ሰው ባለማወቅ ምክንያት በሚያጠፋው ጥፋት ዑዝር አይሰጠውም ለሚለው አቋም ትክክለኛ መረጃ ማቅረብ የሚችል ማንም አካል አይኖርም!!

አላህ ﷻ እንዲህ ብሏል:

وَمَا كُنَّا مُعَذِّبِينَ حَتَّىٰ نَبْعَثَ رَسُولًا( )الإسراء :15(

(መልዕክተኛንም እስከምንልክ ድረስ የምንቀጣ አይደለንም፡፡) እንዲህም ብሏል:

رُّسُلًا مُّبَشِّرِينَ وَمُنذِرِينَ لِئَلَّا يَكُونَ لِلنَّاسِ عَلَى اللهِ حُجَّةٌ بَعْدَ الرُّسُلِ

(النساء: 165)

[ከመልክተኞቹ በኋላ ለሰዎች በአላህ ላይ አስረጅ እንዳይኖር አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች የሆኑን መልክተኞች (ላከን)]

ዐዝር ቢል ጅህል ባይኖር ኑሮ መልእክተኞችን ወደ እኛ መላክ ፋይዳ አይኖረውም ነበር፤ የሰው ልጆችም ተፈጥሯዊ ህሊናቸው በሚያስፈርደው ነገር እንዲያምኑ ይጎደዱ ነበር፤ መልክተኞችንም መላክ አያስፈልግም ነበር!!

ስለዚህ ዐዝር ቢልጀህል አለ የሚለው ሀሳብ የቁርአንና የሐዲሥ መረጃዎች የሚያመላክቱት ጉዳይ ነው።

ሸይኽል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያንና ሸይኽል ኢስላም ሙሐመድ ኢብኑ ዐብደል ወሃብን ጨምሮ በርካታ የእውቀት ባለቤቶችና የሀይማኖቱ መሪዎችም በማያሻማ መልኩ የገለፁት ነገር ነው።

ነገር ግን ሰውየው የሚገስፀውን እውቀት በመማር ላይ ሊሳነፍ ይችል ይሆናል፤ ከዚህ አኳያ በወንጀሉ ይያዝበታል። ማለትም ፦ ለመማር ሁኔታዎች ተመቻችተውለት በመሳነፍና ትኩረት ባለመስጠት ወይም ደግሞ "ይህ ተግባርህ ሀራም ነው" ተብሎ እየተነገረውንኳ ቦታ የማይሰጥ ከሆነ ከዚህ አንፃር ተጠያቂ ይሆናል።

ባለማወቃቸው ምክንያት ወንጀሉን የተፈቀደ ተግባር አድርገው የሚያዩ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖርን ግለሰብ መረጃ ሳይደርሰው በወንጀሉ ይጠየቅበታል ማለት ግን ትክክል አይደለም።

እኛ ሀቂቀተን ፍርድን ስናስቀምጥ ሸሪዓው በሚያስፈርደው መልኩ እንጂ ስሜታችን በምታስፈርድልን አይደለም!!

የላቀውና የተከበረው ጌታችን አላህ በሐዲሠል ቁድሲ እንዲህ ይላል፦

«إِنَّ رَحْمَتِي سَبَقَتْ غَضَبِي» متفق عليه

[እዝኑቴ ቁጣዬን ትቀድማለች (ታሸንፋለች)።]

ታድያ የስራው ሐራምነት ሳይታወሰው ባለማወቅ በሚሰራው ወንጀል እንዴት ተጠያቂ እናደርገዋለን!?

ኧረ እንደውም ሸይኽል ኢስላም ሙሐመድ ኢብኑ ዐብደል ወሃብ እንዲህ ብሏል:

وإذا كُنَّا لا نكفِّر مَن عَبَدَ الصنم الذي على عبد القادر، والصنم الذي على قبر أحمد البدوي، وأمثالهما لأجل جهلهم وعدم من يُنَبِّهُهم، فكيف نكفِّر من لم يشرك بالله إذا لم يهاجر إلينا أو لم يكفر ويقاتل، سبحانك هذا بهتان عظيم

الدرر السنية : 1/ 66

«በዐብደልቃዲር አልጀይላኒ፣ በአሕመድ አልበደዊና በሌሎች መሰል አካላት መቃብር ላይ የተገነቡ ታቡቶችን (ዶሪሐችን) የሚያመልኩ ሰዎች ባለማወቃቸውና የሚገስፃቸው ሰው ባለመኖሩ ምክንያት ካላከፈርናቸው (ከኢስላም ያላስወጣናቸው ሆነን እያለ)፤ በአላህ የማያጋራን ሰው ወደእኛ ባለመሰደዱ፣ ባለማከፈሩና ከእኛ ጋር ሆኖ ጠላትን ባለመፋለሙ ምክንያት እንዴት ከኢስላም እናስወጣዋለን!? አላህ ሆይ ጥራት ይገባህ፤ ይህ ከባድ የሆነ ቅጥፈት ነው።» (አድ - ዱረር አስ - ሰኒያ: 1/66)

ሙርጂኣዎች በርካታ ስህተቶችና ጥፋቶች ቢኖራቸውም ከኢስላም ያስወጣቸውን አንድንም (ዓሊም) አላውቅም። ምንጭ: (ሲልሲለቱ ሊ ቃኣቲል ባቢል መፍቱሕ: 33)

②

የሀገረ የመን ታላቁ ሰለፊይ ዓሊም አል ሙሐዲሥ አል ዐላማህ አሸይኽ ሙቅቢል ኢብኑ ሃዲ አል ዋዲዒይ ረሒመሁላህ እንዲህ በሚል ተጠየቁ:

[ሀገረ ግብፅ የሚገኙ ወንድሞች መካከል "ዑዝር ቢል ጀህል አለ፤ የለም" በሚል እየተጨቃጨቁ እርስበርስ እስከ መደባደብና አንዱ አንዱን እስከ ማዋረድ ይደርሳሉ፤ እንዲሁም አንዱ ሌላኛውን ሙብተዲዕ ወይም ፋሲቅ ያደርገዋል።

ስለዚህ የዚህ ጉዳይ ትክክለኛ ብይን ምንድን ነው? የሚቃረነውስ ሰውዬ ምን ተብሎ ይሰየማል?

ሸይኹም እንዲህ በማለት መልስ ሰጡ:

«ዑዝር ቢል ጀህል የሚባለው ጉዳይ አህሉ - ሱናዎች ራሳቸው የተለያዩበት ነጥብ ነው፤ (በተለይም) ተውሒይድ ነክ በሆኑ መስአላዎች። ሆኖም ግን መረጃዎች በግልፅ እንደሚጠቁሙት ዑዝር ቢል ጀህል አለ።

•አላህ አዘ ወጀል እንዲህ ብሏልና:

{وَمَا كُنَّا مُعَذِّبِينَ حَتَّىٰ نَبْعَثَ رَسُولًا} (الإسراء: 15)

{መልዕክተኛንም እስከምንልክ ድረስ የምንቀጣ አይደለንም።።}

• እንዲሁም አላሁ አዘ ወጀል የሚሳ ዐለይሂ ሰላም ምርጥ ተከታይ የነበሩት ሐዋሪዮች ነቢያቸውን እንዲህ በማለት መጠየቃቸውን ነግሮናል፦

هَلْ يَسْتَطِيعُ رَبُّكَ أَن يُنَزِّلَ عَلَيْنَا مَائِدَةً مِّنَ السَّمَاءِ

(المائدة: 112)

{የመርየም ልጅ ሚሳ ሆይ! ጌታህ በእኛ ላይ ከሰማይ ማእድን ሊያወርድልን ይችላልን?}

ያኔ ታዲያ ሚሳ ዐለይሂ - ሰላም "እናንተ ሐዋሪያቶች! በእርግጥ ከፍራችኋል!!" አላላቸውም። ነገር ግን :

{قَالَ اتَّقُوا اللهَ إِنْ كُنْتُمْ مُؤْمِنِينَ}

{አማኞች እንደ ሆናችሁ አላህን ፍሩ} ነው ያላቸው።

• በተጨማሪም አላህ ﷻ የነቢዩላህ ሙሳ ተከታዮች እንዲህ ማለታቸውን ነግሮናል፦

{يَا مُوسَى اجْعَل لَّنَا إِلَٰهًا كَمَا لَهُمْ آلِهَةٌ ۚ قَالَ إِنَّكُمْ قَوْمٌ تَجْهَلُونَ} (الأعراف: 138)

{ሙሳ ሆይ፡- ለእነርሱ (ለሰዎቹ) አማልክት እንዳሏቸው ለእኛም አምላክን አድርግልን» አሉት፡፡ «እናንተ ጃሂል የሆናችሁ ሕዝቦች ናችሁ፤» አላቸው፡፡}

• ከብዙ ሰሓቢዮች ተወርዶ ቡኻሪ፣ ሙስሊምና ሌሎችም በዘገቡት የነቢዩ ﷺ ሐዲሥ ላይ እንዲህ የሚል አለ፡- {መልካም ስራ የሌለው አንድ የሆነ ሰው ሊሞት ሲል ልጆቹን እንዲህ ሲል ተናዘዘ፡- "እኔ ለእናንተ ምን አይነት ወላጅ ነኝ?" እነሱም "ምን ያምር ወላጅ ነህ!" አሉት። "እንግዲያውስ ስሞት አቃጥሉኝና ፍጭት አድርጉኝ። ከዚያም በነፋሻማ ወቅት ባህር ውስጥ አመዱን በትኑት። በአላህ ይሁንብኝ! አላህ እኔን ከሞት ለማንሳት ችሎ ቢቀሰቅሰኝ (እና ቢያገኘኝ) አለማት ላይ ካሉ ፍጡራኖች ማንኛውንም የማይቀጣውን ቅጣት ይቀጣኛል።" አላቸው። በሞተ ጊዜ ልጆቹ የታዘዙትን ፈፀሙ። ከዚያም አላህ ﷻ ባህሩንም የብሱንም አመዱን እንዲሰበስቡ አዘዘ፤ ሰውየውንም ቀሰቀሰውና: "ይህን ለማድረግ ያነሳሳህ ነገር ምንድን ነው? " አለው። እሱም: "ጌታዬ! ፈርቼህ ነውኮ" ሲል መለሰ። አላህም ﷻ "በእርግጥ ምሬሃለሁ" አለው።)

ሐዋሪያቶች በአላህ ችሎታ እንደተጠራጠሩት ሁሉ፤ ይህም ሰው (እንደምታዩት) በአላህ ቻይነት የሚጠራጠር ሰው ነው።

• እነዚህ መረጃዎች ዑዝር ቢል ጀህል መኖሩን ይጠቁማሉ።

• "ዑዝር ቢል ጀህል የለም" የሚሉ አካሎች መነሳት የምትችል መረጃ የላቸውም (መረጃቸው ደካማ ናት።)

ካለፉት መረጃዎች በመቀጠል ሙስነድ ኢማም አሕመድ የተባለው ኪታብ ላይ ከአቡ ሁረይራና ከአስወድ ኢብኑ ሰሪዕ ረዲየላሁ ዐንሁማ የተወራ ቀጣዩን የነቢዩ ﷺ ሐዲሥ እንገኛለን፡-

[በቂያማ እለት አራት አይነት ሰዎች ይፈተናሉ፡- የማይሰማ (ደንቆሮ) የነበረ፣ ሞኝ የነበረ፣ የጃጀ ያረጀ አዛውንትና ሷሒቡል ፈትራ (መልእክተኛ ወይም አስተማሪ በሌለበት ዘመንና ቦታ ኖሮ፤ መሆን የሚጠበቅበትን ሳይሆን የሞተ) ናቸው። ያኔ አራቱም አይነት ፍጡሮች ዑዝራቸውን ያቀርባሉ። አላህም ለመፈተን: "እሳት ግቡ" ይላቸዋል። ከውስጣቸው አላህን በመታዘዝ እሳቷ ውስጥ የሚገባ እሳቷ ሰላም ያላትና ቀዝቃዛ ትሆንለታለች፤ እንቢ አንገባም የሚሉትን ደግሞ "አሁን

እናንተ እኔን አመፃችሁ፤ ዱንያ ላይ መልእክተኞቼ ቢመጧችሁ ኖሮ ለእኔ ካሳያችሁት አመፅ ይበልጥ ታምፆቸው ነበር።" ይላቸዋል።]

• በመጨረሻም ኢማም አቪንቂጢ አድዋኡል በያን የተሰኘው ተፍሲራቸው ላይ ለቀጣዮቹ አንቀፆች ያሰፈሩትን ተፍሲር በጥሞና ታነቡ ዘንድ እመክራችኋለሁ።

)15: ءاسراﻹ} (وَمَا كُنَّا مُعَذِّبِينَ حَتَّىٰ نَبْعَثَ رَسُولًا{

{መልዕክተኛንም እስከምንልክ ድረስ የምንቀጣ አይደለንም።}

()115: التوبة} (وَمَا كَانَ اللهُ لِيُضِلَّ قَوْمًا بَعْدَ إِذْ هَدَاهُمْ حَتَّىٰ يُبَيِّنَ لَهُم مَّا يَتَّقُونَ

{አላህም ሕዝቦችን ከአቀናቸው በኋላ የሚጠነቀቁትን (ሥራ) ለእነሱ እስከሚገልጽላቸው (እስከሚተውትም) ድረስ ጥፋተኛ የሚያደርግ አይደለም።}

• *ዑዝር ቢል ጀህል አለ/የለም የሚለው ጉዳይ በአህሉሱና መካከል የሚከሰት መስአላ ኺላፊያ በመሆኑ፤ የሚቃረነውን አካል: ሙብተዲዕ፣ ፋሲቅ፣ ሙርጂእና የመሳሰሉ ብይኖችን አንሰጠውም። ነገር ግን ራጂሑ (አመዛኝ) ፍርድ: "ዑዝር ቢል ጀህል አለ" የሚለው ነው]*

ምንጭ:(ጀረቱል አሽሪጧህ 2/447 448 -)

③

በዛሬው ፅሁፍ የኢማሙል አልባኒ ፈትዋ ቅድሚያ የቀረበ ሲሆን በስተመጨረሻም የኢማም ኢብኑል ቀዪም አጠር ያለች ንግግር ታክሎበታል ወሏሁል ሙወፊቅ!!

የዘመናችን ታላቁ ሙሐዲሥ አቪይኽ አል ዐላማህ አል ፈቂህ ሙሐመድ ናሲሩዲን አል አልባኒ ረሒመሁላሁ ተዓላ እንዲህ በሚል ተጠየቁ:

[አንዳንድ ሰዎች ጠማማ ከሆኑ ዑለማዎቻቸው በተማሩት መሰረት ሙታኖችን በመለመን (በአላህ እያጋሩ)፤ እንደሚጠቅሟቸውና እንደሚጎዷቸውም የሚያምኑ ሆነው ይሞታሉ፤ ነገር ግን ትክክለኛ ተውሒይድን አያውቁም እና የእነዚህ ሰዎች ብይን ምንድን ነው?

ሸይኹም እንዲህ በማለት መልስ ሰጡ:

«እኔ የምለው እነዚህ ሰዎች ኢስላማዊ ማእዘኖችን የሚሰሩባቸው ከሆነ፤ ነገር ግን ባለማወቃቸው ምክንያት (ያን ጥፋት ካጠፉ)፤ ስለ እነሱ ተጠያቂ የሚሆኑት እነዚያ ያጠመሟቸው ዑለማዎች ናቸው። እነኚህ (በዚህ ጥፋት) የሞቱ ሰዎች በመሰረቱ ሙስሊሞች ናቸው፤ ሌሎች ሙስሊሞች ጋር በምናደርገው ሙዓመላ አምሳያ እነሱንም ሙዓመላ እናደርጋቸዋለን። ሲሞቱ ሙስሊሞች መቃብር ይቀበራሉ፤ በመቀጠል በመቃብራቸው አላፊ ካለፈም:

السلام عليكم أهل الديار من المسلمين والمؤمنين ...

"እናንተ የመቃብር ባለቤት የሆናችሁ ሙስሊም አማኞች ሆይ! ሰላም በእናንተ ላይ ይስፈን ... " በማለት የአላህን ምህረትና እዝነት ይጠይቅላቸዋል። ከዚያም የመጨረሻቸው ጉዳይ ወደ አላህ ነው የሚመለሰው። ምክንያቱም አላህ አዘ ወጀል እንዲህ ብሏልና:

إِنَّ اللهَ لَا يَغْفِرُ أَن يُشْرَكَ بِهِ وَيَغْفِرُ مَا دُونَ ذَٰلِكَ لِمَن يَشَاءُ

النساء:48)

{አላህ በእርሱ ማጋራትን በፍጹም አይምርም:: ከዚህ ሌላ ያለውንም (ኀጢአት) ለሚሻው ሰው ይምራል::}

በአላህ የሚያጋራ ሰው ደግሞ ደዕዋው በእርግጥ ደርሶት የሆነ እንደሁ እንጂ ተጠያቂ አይሆንም!!

{وَمَا كُنَّا مُعَذِّبِينَ حَتَّىٰ نَبْعَثَ رَسُولًا}

{መልዕክተኛንም እስከምንልክ ድረስ የምንቀጣ አይደለንም::}

• የተከበረውና የላቀው ጌታችን ከቸርነቱና ከእዝነቱ የተነሳ ባሪያው (ሑጃህ ወይም ማስረጃህ አልደረሰኝም ብሎ) ምክንያት ቢያቀርብ ይቀበለዋል። ከእነዚህ ኹራፊዩን (መሰረተ ቢስ የሆነ እምነት ያላቸው) ከሆኑ ሙስሊሞች አንዱ (ያን ጥፋት ሲፈፅም) የሚያስታውሰው፣ የሚያስጠነቅቀውና ከጥመቱ የሚከለክለው ባለመኖሩ ምክንያት ቅኑን መንገድ ቢስት አላህ ተባረከ ወተዓላ ዘንድ መዕዙውር

ነው (ተጠያቂ አይሆንም)፤ መረጃ ደርሶት አሻፈረኝ ያለ ሰው ተጠያቂ የሚሆነውን ያህልም አይጠየቅም (አይያዝበትም)። ምክንያቱም አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ:

{وَمَا كُنَّا مُعَذِّبِينَ حَتَّىٰ نَبْعَثَ رَسُولًا}

{መልዕክተኛንም እስከምንልክ ድረስ የምንቀጣ አይደለንም::} ብሏልና።» ምንጭ: (ሲልሲለቱል ሁዳ ወን - ኑር, ካሴት ቁጥር: 95)

قال الإمام ابن القيم رحمه الله تعالى

(فأما أهل البدع الموافقون لأهل الإسلام ولكنهم مخالفون في بعض الأصول كالرافضة والقدرية والجهمية وغلاة المرجئة ونحوهم فهؤلاء أقسام:

أحدها :الجاهل المقلد الذي لا بصيرة له فهذا لا يكفَّر ولا يفسَّق ولا تردُّ شهادته إذا لم يكن قادرا على تعلم الهدى وحكمه حكمُ المستضعفين من الرجال والنساء والولدان الذين لا يستطيعون حيلة ولا يهتدون سبيلا فأولئك عسى الله أن يعفو عنهم وكان الله عفوا غفورا

اهـ . من الطرق الحكمية: 254/1

فهذا ابن القيم لم يكفِّر جُهَّال الرافضة، مع وقوعهم في الشرك، لِمانِعِ الجَهل

• ኢማም ኢብኑል ቀዩም ረሒመሁላህ እንዲህ ብለዋል:

«ሙስሊሞች ጋር በአንዳንድ መሰረታዊ የእምነት ከፍሎች የሚስማሙና በሌሎች መሰረታዊ ከፍሎች ደግሞ የሚቃረኗቸው የሆኑ የቢድዓ ባለቤቶች ለምሳሌ ያህል: ራፊዷዎች፣ ቀደሪያዎች፣ ጀህሚያዎች፣ ፅንፈኞቹ ሙርጂአዎችና የመሳሰሉት አካላቶች በተለያየ ከፍል (መደብ) ነው የሚታዩት።

①ኛ ጠቃሚ እውቀት የሌለው፣ ሙቀሊድ (ያመነበትን አካል በጭፍን የሚከተል) እና ጃሂል የሆነው ነው። ይህ አይነቱ የሰዎቹ ከፍል ቅኑን ጎዳና ለመማር ካልቻለ አይከፈርም፤ ፋሲቅም አይደረግም፤ እንዲሁም ምስክርነቱም ውድቅ አይሆንም። የዚህ አይነቱ ሰው ብይን እንደነዚያ (በሶሓቦች ዘመን ከመካ ወደ መዲና) ለመሰደድ ብልሃት የሌላቸውና መንገድን የማይመሩ እንደሆኑት

ደካማ ወንዶች፣ ሴቶችና ህፃናቶች አይነት ብይን ነው። እነዚህ ሰዎች ደግሞ አላህ ለእነሱ ይቅርታ ማለቱ እርግጥ ነው። አላህም ይቅር ባይና መሃሪ ነውና»

ምንጭ: (አጥ - ጡሩቅ አልሒከሚያህ: 1/254)

«እዚህ የኢማም ኢብኑል ቀዪም ንግግር ላይ በግልፅ ተቀምጦ እንደምናየው፡- መሃይም የሆኑ ራፊደዎች ሽርክ ውስጥ ከመዘፈቃቸው ጋር ጅህልናቸው (እነሱን ከማክፈር) የሚከለክል ምክንያት በመሆኑ አላከፈራቸውም!! »

④

ጊዜ ቁቡውሪዮች (ቀብር አምላኪዎች) ባጠቃላይ ሁኟ ደርሷቸዋል የሚለው አባባል እንዴት ይታያል?

የየመኑ ሸይኽ ሙቅቢል አልዋዲዒ ኽሊፋ የሆኑት ታላቁ ዓሊም አሸይኽ የሕያ ኢብን ዐሊይ አል ሐጁውሪ ቀጣዩን ጥያቄ ተጠየቁ:

አንዳንድ ሰዎች "ዛሬ ጊዜ መገናኛ ብዙሃን ስለተሰራጨ ቀብር አምላኪዎችና መሰሎቻቸው ላይ ሑጃ ቆሞባቸዋል" ይላሉ። ይህ ትክክል ነውን? ምንስ ያስከትላል?

ሸይኽ የሕያም እንዲህ በማለት መልስ ሰጡ:

{መገናኛ ብዙሃን መሰራጨታቸው በተጨባጭ የሚታይ ነገር ነው። አንባቢና አድማጭ ለሆኑ አካላት በሬዲዮ፣ በካሴቶችና በመፅሀፎች እየተሰራጨ ይገኛሉ። ሆኖም ግን "ዑዝር ቢልጀህል የለም" ማለት ስህተት ነው!! ማንኛውም ሙስሊም (እንዲህ አይነት) ስህተት ላይ ከመውደቅ መጠንቀቅ ይኖርበታል። ሑጃ ያልደረሰው ወይም ደርሶት ያልተረዳው ሰው ከተገኘ ይህ ሰው መዕዙውር ነው። ምክንያቱም አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ እንዲህ ብሏልና:

{وَمَا كُنَّا مُعَذِّبِينَ حَتَّىٰ نَبْعَثَ رَسُولًا}

• {መልዕክተኛንም እስከምንልክ ድረስ የምንቀጣ አይደለንም::}

• አስወድ ኢብኑ ሰሪይዕ ሐዲሥ ላይ ነቢዩ ﷺ: «አራት አይነት ሰዎች የቂያም እለት ይፈተናሉ» ብለው የተናገሩበት ላይ አራተኛው ሰው ሷሒቡል ፈትራ (መልእክት አድራሽ ሰው በሌለበት ዘመን ወይም ቦታ ላይ ያለ ሰው) እንደሆነ ተወስቷል።

• አቡ ሰዒድ አል ኹድሪይ ባስተላለፉት የነቢዩ ﷺ ሐዲሥ ላይ እንዲህ የሚልም አለ፦

{መልካም ስራ የሌለው አንድ የሆነ ሰው ሊሞት ሲል ልጆቹን እንዲህ ሲል ተናዘዘ፦ "እኔ ለእናንተ ምን አይነት ወላጅ ነኝ?" እነሱም "ምን ያምር ወላጅ ነህ!" አሉት። "እንግዲያውስ ስሞት አቃጥሉኝና ፍጩኝ። ከዚያም በነፋሻማ ወቅት ባህር ውስጥ አመዱን በትኑት። በአላህ ይሁንብኝ! አላህ እኔን ከሞት ለማንሳት ችሎ ቢቀሰቅሰኝ (እና ቢያገኘኝ) አለማት ላይ ካሉ ፍጡራኖች ማንኛውንም የማይቀጣውን ቅጣት ይቀጣኛል።" አላቸው። በሞተ ጊዜ ልጆቹ የታዘዙትን ፈፀሙ። ከዚያም አላህ ﷻ ባህሩንም የብሱንም አመዱን እንዲሰበስቡ አዘዘ፤ ሰውየውንም ቀሰቀሰውና: "ይህን ለማድረግ ያነሳሳህ ነገር ምንድን ነው? " አለው። እሱም: "ጌታዬ! ፈርቼህ ነውኮ" ሲል መለሰ።

• ዑለማኦች ስለ ሐዲሡ ትንታኔ ሲያወሩ እንዲህ ብለዋል: "አላህ ﷻ ለዚህ ሰው ምህረት ያደረገለት በጅህልናው ወይም ባለማወቁ ምክንያት ነው፤ ያለበለዚያማ ጥግ የደረሰ የአላህ ፍራቻ ያለው የሆነ ሰው በአላህ ችሎታ የሚጠራጠር ከሆነ በጥርጥሩ ምክንያት ይከፍራል!! (ፍርሃቱ አይሸፍዕለትም)።

• ሰውየው ሑጃዋን ወይም ማስረጃዋን ካልተረዳት በስተቀር ደርሰዋለች ሊባል አይችልም!!

ምክንያቱም አላሁ ﷻ እንዲህ ስላለ:

وَمَن يُشَاقِقِ الرَّسُولَ مِن بَعْدِ مَا تَبَيَّنَ لَهُ الْهُدَىٰ وَيَتَّبِعْ غَيْرَ سَبِيلِ الْمُؤْمِنِينَ نُوَلِّهِ مَا تَوَلَّىٰ وَنُصْلِهِ جَهَنَّمَ وَسَاءَتْ مَصِيرًا

(النساء: 115)

{ቅኑም መንገድ ለእሱ ከተገለጸ በኋላ መልክተኛውን የሚጨቃጨቅና ከምእምኖቹ መንገድ ሌላ የኾነን የሚከተል ሰው (በዚህ ዓለም) በተሾመበት

(ጥመት) ላይ እንሾመዋለን፤ ገሀነምንም እናገባዋለን። መመለሻይቱም ከፋች!} (አን ኒሳእ: 115)

ቅኑ መንገድ ተገልፆለት ካልተቀበለው ይህ ሰው ሑጃ የደረሰው እንቢተኛ ይሆናል ማለት ነው።

አላህ ﷻ እንዲህ ብሏል:

وَمَنْ أَعْرَضَ عَن ذِكْرِي فَإِنَّ لَهُ مَعِيشَةً ضَنكًا وَنَحْشُرُهُ يَوْمَ الْقِيَامَةِ أَعْمَىٰ

{ከግሣጼዬም የዞረ ሰው ለእርሱ ጠባብ ኑሮ አለው። በትንሣኤም ቀን ዕውር ኾኖ እንቀሰቅሰዋለን።}

قَالَ رَبِّ لِمَ حَشَرْتَنِي أَعْمَىٰ وَقَدْ كُنتُ بَصِيرًا

{«ጌታዬ ሆይ! ለምን ዕውር አድርገህ አስነሳኸኝ በእርግጥ የማይ የነበርኩ ስኾን» ይላል።}

قَالَ كَذَٰلِكَ أَتَتْكَ آيَاتُنَا فَنَسِيتَهَا وَكَذَٰلِكَ الْيَوْمَ تُنسَىٰ

{(ነገሩ) እንደዚሁ ነው። «ታምራታችን መጣችልህ። ተውካትም። እንደዚሁም ዛሬ ትተዋለህ» ይለዋል።}

(طه: 124 -126)

. . .

እንዲህም ብሏል:

وَمَن يُعْرِضْ عَن ذِكْرِ رَبِّهِ يَسْلُكْهُ عَذَابًا صَعَدًا

الجن :17

{ከጌታውም ማስታወሻ የሚያፈገፍግ ሰው አስቸጋሪን ቅጣት ያስገባዋል።}

وَمَنْ أَظْلَمُ مِمَّن ذُكِّرَ بِآيَاتِ رَبِّهِ ثُمَّ أَعْرَضَ عَنْهَا إِنَّا مِنَ الْمُجْرِمِينَ مُنتَقِمُونَ

(السجدة: 22)

(በጌታውም አንቀጾች ከተገሰጸና ከዚያም ከተዋት ሰው ይበልጥ በደለኛ ማነው? (የለም)፤ እኛ ከሙጅሪሞቹ ተበቃዮች ነን።።}] ምንጭ: (አስኢለቱ አሰ - ሰለፊዩን ቢልሙከላ ሐድረመውት፣ ለይለተል ጁሙዓ 9 ጁማደል ኡውላ 1423ﻫ ደማጅ - ሰዕዳ)

⑤

[የዛሬው ፅሁፍ በበርካታ የቁርአንና የሐዲሥ መረጃዎች የተደገፈና ሰፋ ያለ፤ እንዲሁም የቀደምቶችና የዘመናችን ዑለማዎች ትንታኔ ያለበት ነው። ስለዚህ ያንብቡ፤ ሹብሃዎንም ያስወግዱ!!]

የሸይኽ ዐብደል ዐዚዝ ኢብን ባዝ እና የሸይ ዐብደረሕማን አስ - ሰዕዲ ተማሪ የነበሩት አሸይኽ አልፈቂህ ሙሐመድ ሷሊሕ አልዐሡይሚይን
(ረሒመላሁልጀሚዕ) ሰፋ ያለ ፈትዋ:

ሸይኹ "በዐቂዳዊ ጉዳዮች ዐዝር ቢል ጀህል ይኖራል ወይ?" ተብለው በተጠየቁ ጊዜ እንዲህ በማለት መለሱ:

«በዐዝር ቢልጀህል ጉዳይ ያለው ኢኽቲላፍ ፊቅሃዊና ኢጅቲሃዳዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ እንዳለው አይነት ኢኽቲላፍ (የሀሳብ ልዩነት) ነው። አንድን ግለሰብ ለይቶ በላዩ ላይ ፍርድን ተግባራዊ ለማድረግ ሲባል የሚፈጠር በመሆኑ ምናልባትም አንዳንዴ ቃላዊ ልዩነት ሊሆን ይችላል። ማለትም አንድ የሆነ ንግግር ወይም ተግባር ወይም ደግሞ መተው ኩፍር በመሆኑ ሁሉም ይስማሙና፤ መስፈርቶች ስለተሟሉና ከልካዮች ስለተወገዱ ሰውየውን በተዕዩን ለይቶ ቢሰየንበት ብይኑ ትክክል ይሆናል? ወይስ ከፊል መስፈርቶች ስላልተሟሉና ከፊል ከልካዮችም ስለተገኙ ብይኑ ተስማሚ አይሆንም በሚል ማለት ነው።

•የሚያከፍሩ ነገሮችን ባለማወቅ ኩፍር ውስጥ የሚወድቅ ሰው በሁለት አይነት መልኩ ነው የሚታየው።

• አንደኛ: የሌላ እምነት ተከታይ ወይም እምነት የሌለው ከሆነ ሰው የሚገኝ ሆኖ፤ ነገር ግን እሱ ያለበትን ሁኔታ የሚቃረን ትክክለኛ ሐይማኖት መኖሩ በህሊናው ውል የማይል ከሆነ፤ የዚህ ሰው ብይን በዱንያ እሱ ላይ በግልፅ በምናየው ነገር እንፈርድበታለን። በኣኺራ ግን ጉዳዩ ወደ አላህ ነው

የሚመለሰው፤ በዚህ ላይ አመዛኝ የሆነው የዑለማዎች ንግግርም አላህ በፈለገው ፈተና ይፈትነዋል የሚለው ነው። ይሰሩ የነበሩትንም አላህ ያውቃል። ነገር ግን ሰው በጥፋቱ እንጂ እሳት እንደማይገባ እናምናለን፤ ምክንያቱም አላህ ﷻ እንዲህ ብሏልና:

{وَلَا يَظْلِمُ رَبُّكَ أَحَدًا}

{ጌታህ ማንንም የሚበድል አይደለም}

• ይህ አይነቱ ሰው ዱንያ ላይ ከእሱ በግልፅ በምናየው በኩፍር አሕካሞች እንበይንበታለን ያልንበት ምክንያት:- በመሰረቱ ኢስላምን እምነት አድርጎ ባለመያዙ ነው፤ ስለዚህ ሙስሊም አንለውም። በኣኺራ ደግሞ አመዛኙ ብይን ይፈተናል ያልነው:- በዚህ ጉዳይ በርካታ ኣሣሮች ስለመጡ ነው። እነሱንም ኢብኑል ቀይም አላህ ይዘንለትና "ጠሪይቁል ሂጅረተይን" የተሰኘው ኪታቡ ላይ ስለ ሙሽሪኮች ህፃናት የሚዳስስበት ስምንተኛ ባብ፤ አስራ አራተኛ ደረጃ ላይ ጠቅሷቸዋል።

•ሁለተኛው አይነት ደግሞ :- ሐይማኖቱ ኢስላም ሆኖ ነገር ግን በዚህ የሚያከፍረው በሆነ ስራ ላይ የኖረ ነው። ስራው ኢስላምን የሚቃረን መሆኑ በህሊናው ውል አይልም፤ ኩፍርነቱንም ማንም ሰው አላስታወሰውም። ለዚህ አይነቱ ሰው ኢስላማዊ አሕካሞችን እንበይንበታለን። በኣኺራ ደግሞ ጉዳዩ የሚመለሰው ወደ አላህ ነው።

ይህ ብይን ቁርኣን፣ ሐዲሥና የዑለማዎች ንግግሮች በእርግጥ የሚጠቁሙት ጉዳይ ነው።

•ከቁርኣን ማስረጃዎች ለምሳሌ ያህል:

• {وَمَا كُنَّا مُعَذِّبِينَ حَتَّىٰ نَبْعَثَ رَسُولًا} (النساء: 15)

{መልዕክተኛንም እስከምንልክ ድረስ የምንቀጣ አይደለንም።}

• وَمَا كَانَ رَبُّكَ مُهْلِكَ الْقُرَىٰ حَتَّىٰ يَبْعَثَ فِي أُمِّهَا رَسُولًا يَتْلُو عَلَيْهِمْ آيَاتِنَا وَمَا كُنَّا مُهْلِكِي الْقُرَىٰ إِلَّا وَأَهْلُهَا ظَالِمُونَ (القصص: 59)

{ጌታህም ከተሞችን በዋናዋ (ከተማ) ውስጥ አንቀጾቻችንን በእነሱ ላይ የሚያነብ መልክተኛን እስከሚልክ ድረስ አጥፊ አልነበረም፡፡ ከተሞችንም ባለቤቶቿ በዳዮች ሆነው እንጅ አጥፊዎች አልነበርንም፡፡}

• رُسُلًا مُّبَشِّرِينَ وَمُنذِرِينَ لِئَلَّا يَكُونَ لِلنَّاسِ عَلَى اللَّهِ حُجَّةٌ بَعْدَ الرُّسُلِ

(النساء :165)

{ከመልክተኞቹ በኋላ ለሰዎች በአላህ ላይ አስረጅ እንዳይኖር አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች የኾኑን መልክተኞች (ላክን)፡፡}

• وَمَا أَرْسَلْنَا مِن رَّسُولٍ إِلَّا بِلِسَانِ قَوْمِهِ لِيُبَيِّنَ لَهُمْ فَيُضِلُّ اللهُ مَن يَشَاءُ وَيَهْدِي مَن يَشَاءُ

(إبراهيم :4)

{ከመልክተኛ ማንኛውንም ለእነርሱ ያብራራላቸው ዘንድ በወገኖቹ ቋንቋ እንጂ በሌላ አልላክንም፡፡ አላህም የሚሻውን ያጠማል፡፡ የሚሻውንም ያቀናል፡፡}

• وَمَا كَانَ اللهُ لِيُضِلَّ قَوْمًا بَعْدَ إِذْ هَدَاهُمْ حَتَّىٰ يُبَيِّنَ لَهُم مَّا يَتَّقُونَ

(التوبة 115)

{አላህም ሕዝቦችን ካቀናቸው በኋላ የሚጠነቀቁትን (ሥራ) ለእነሱ እስከሚገልጽላቸው (እስከሚተውትም) ድረስ ጥፋተኛ የሚያደርግ አይደለም፡፡}

• وَهَٰذَا كِتَابٌ أَنزَلْنَاهُ مُبَارَكٌ فَاتَّبِعُوهُ وَاتَّقُوا لَعَلَّكُمْ تُرْحَمُونَ ۝ أَن تَقُولُوا إِنَّمَا أُنزِلَ الْكِتَابُ عَلَىٰ طَائِفَتَيْنِ مِن قَبْلِنَا وَإِن كُنَّا عَن دِرَاسَتِهِمْ لَغَافِلِينَ ۝ أَوْ تَقُولُوا لَوْ أَنَّا أُنزِلَ عَلَيْنَا الْكِتَابُ لَكُنَّا أَهْدَىٰ مِنْهُمْ ۚ فَقَدْ جَاءَكُم بَيِّنَةٌ مِّن رَّبِّكُمْ وَهُدًى وَرَحْمَةٌ

(الأنعام :155 - 157)

{ይህም ያወረድነው የኾነ የተባረከ መጽሐፍ ነው፡፡ ተከተሉትም፡፡ ይታዘንላችሁም ዘንድ (ከክህደት) ተጠንቀቁ፡፡ «(ያወረድነውም) መጽሐፍ የተወረደው ከፊታችን በሁለቱ ጭፍሮች ላይ ብቻ ነው፡፡ እኛም ከንባባቸው ዘንጊዎች ነበርን» እንዳትሉ ነው፡፡ ወይም «እኛ መጽሐፍ በእኛ ላይ በተወረደ

ኖሮ ከእነሱ ይበልጥ የተመራን እንኾን ነበር» እንዳትሉ ነው፡፡ ስለዚህ ከጌታችሁ ግልጽ ማስረጃ፣ መምሪያም፣ እዝነትም በእርግጥ መጣላችሁ፡፡}

እነዚህና የመሳሰሉት የቁርኣን አንቀፆች ሑጃ ወይም ማስረጃ የሚባለው ነገር ከእውቀትና ከገለፃ በኋላ እንጂ እንደማይቆም ነው የሚጠቁሙት።

•ከሐዲሥ ደግሞ ለምሳሌ ያህል:

ኢማም ሙስሊም አላህ ይዘንለትና አቡ ሁረይራን ረዲየላሁ ዐንሁ በመጥቀስ ነቢዩ ﷺ እንዲህ ማለታቸውን ዘግቦልናል:

وَالَّذِي نَفْسُ مُحَمَّدٍ بِيَدِهِ، لَا يَسْمَعُ بِي أَحَدٌ مِنْ هَذِهِ الْأُمَّةِ يَهُودِيٌّ وَلَا نَصْرَانِيٌّ، ثُمَّ يَمُوتُ، وَلَمْ يُؤْمِنْ بِالَّذِي أُرْسِلْتُ بِهِ إِلَّا كَانَ مِنْ أَصْحَابِ النَّارِ

(رواه مسلم برقم: 153)

«የሙሐመድ ነፍስ በእጁ በሆነው ጌታ ይሁንብኝ! ከኡመተ - ደዕዋ ማንኛውም አይሁድም ይሁን ክርስቲያን ስለ እኔ ሰምቶ፤ በዚያ በተላኩበት መልእክት ሳያምን አይሞትም ከእሳት ባለቤቶች ቢሆን እንጂ።»

[ይህን ሐዲሥ ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ "አልጀዋቡ ሶሒሕ ሊመን በደለ ዲይነል መሲሕ" የተሰኘው ኪታቡ ገፅ: 138 ላይ ሲተነትነው እንዲህ ይላል፡-

«መስማት የሚለው ቃል የተፈለገበት ሀሳብ፡- ከእሱ ጋር (ቁርአንን) የሚገነዘብበት የሆነ መስማት መሆኑ በእርግጥ የታወቀ ጉዳይ ነው፤ ምክንያቱም መገንዘብ በማይቻለው መልኩ ቃሉን በመስማቱ ብቻ የሚፈለገው አላማ አይገኝምና! ዐረብ ያልሆነ ሰው ከሆነ ሑጃው እንዲቆምበት በቋንቋው ሊተረጎምለት ግድ ነው፤ ዐረብ እንኳ ሆኖ ነገር ግን ቁርአን ውስጥ እንግዳ የሆኑ ቃላቶች በመኖራቸው ሰውየው "ፉስሓ" የሆነው የቁርአንን ቋንቋ ከማይናገሩትና ከማይነገዘቡት ዐረብ ከሆነ ሊብራራለት ግድ ነው።»]

ከዑለማዎች ንግግር ለምሳሌ ያህል:

• (ኢብኑ ቁዳማ) "ሙኽኒ" 8/131) የተባለው ኪታቡ ላይ እንዲህ ብሏል:

«ግዴታነቱን የማያውቅ ከሆነ፤ ለምሳሌ አዲስ ሰለምቴ የሆነ፣ ከኢስላም ሀገራት ውጪ ያደገ፣ ወይም ከከተሞችና ከዑለማዎች ራቅ ያለ ገጠራማ ቦታ የሚኖር ሰው ከሆነ፤ ካፊር ተብሎ አይተሓኸምበትም።»

• ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ "አል ፈታዋ: 3/229 - መጅሙዕ ኢብኑ ቃሲም" ላይ እንዲህ ብሏል:

«እኔ ሁልጊዜ አንድን ሰው በተዕዩን ለይቶ ወደ ኩፍር፣ ወደ ፊስቅና መዕሲያ ማስጠጋትን በጣም አድርገው ከሚቃወሙ ሰዎች የምመደብ ነኝ፤ ይህንንም እኔን የሚያቀማምጡ ሰዎችም ያውቃሉ!! ነገር ግን የታቀረናት ሰው እንደ ሁኔታው አንዳንዴ ካፊር፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ፋሲቅ ወይም ወንጀለኛ የሚሆንባት ነቢያዊ ሑጃ ሰውዬው ላይ በእርግጥ መቆሙ ከታወቀ በቀር (ከዚህ ውጭ ሑጃ ሳይቆምበት ካፊር ፋሲቅ ዓሲ እያሉ መበየንን አጥብቀው ከሚያወግዙ ዑለማዎች ነኝ)። አሁንም እኔ ለዚህ ህዝበ ሙስሊም አላህ ስህተታቸውን በእርግጥ ምሯቸዋል በማለት ደጋግሜና አስረግጬ እናገራለሁ!! ስህተቱ ደግሞ ዐቂዳዊም ሆነ አሕካማዊ ጉዳዮችን ያጠቃልላል። ሰለፎች በበርካታ መሳኡሎች ከመለያየታቸውም ጋር ከውስጣቸው አንዱ በሌላው ላይ በኩፍር ወይም በፊስቅ ወይም ደግሞ በወንጀል ይሐኩሙ አልነበረም!!»

...

ሸይኽል ኢስላም ቀጥለው እንዲህ አሉ:

«ከሰለፎችና ከአኢማዎች "ይህን፣ ይህን መሰል ንግግር የተናገረ ይከፍራል" እያሉ በኢጥላቅ (በልቅ) ተናግረውት ወደኛ የደረሰን ንግግራቸው ሐቅ መሆኑን እገልፅ ነበር፤ ነገር ግን በጥቅል የሚሰጠውንና በተዕዩን (በተናጠል) የሚተሓኸመውን ብይን መለየት ግድ ነው»

...

ሸይኹል ኢስላም አሁንም ቀጠሉ:

«ተክፊይር (ሰውን ከኢስላም ማስወጣት) ከወዒይድ (ዛቻዊ) ነጥቦች ነው፤ አንድ ንግግር መልእክተኛው ﷺ ከተናገሩት ንግግር ጋር የሚቃረን ቢሆንም ተናጋሪው ሰውዬ ግን አዲስ ሰለምቴ ሊሆን ይችላል፤ ወይም ራቅ ያለ ገጠራማ ስፍራ ሊኖር

ይችላል፤ ይህ አይነቱ ሰው በሚከደው ክህደት ሑጃ እስካልቆመበት ድረስ አይከፈርም፤ እንዲሁም ይህ ሰው መረጃዎቹን አልሰማቸው ይሆናል፤ ወይም ሰምቷቸው ነገር ግን እሱ ዘንድ አልሠበቱለት (አልተረጋጡለት) ይሆናል፤ ወይም መረጃዎቹን የሚቃረንበትና ተእዊል የሚያደርግበት የሆነ (ሹብሃ) እሱ ዘንድ ይኖረው ይሆናል፤ ሰውየው (በትክክለኛ እይታ) ስህተተኛ ቢሆንም።»

• ሸይኽ ሙሐመድ ኢብኑ ዐብደል ወሃብ "አድ - ዱረር አስ - ሰኒያ: 1/56" ላይ እንዲህ ብሏል:

«ስለተከፈር (እናውራ ከተባለ) የመልእክተኛውን ﷺ ሐይማኖት አውቆ፤ ከተረዳው በኋላ የሚሰድበው ከሆነ፤ ሰዎችንም (እንዳያምኑበት) የሚከለክል ከሆነ፤ በኢስላም የሚሰሩ ሰዎችንም ጠላት አድርጎ ከያዘ፤ እኔ የማከፍረው ይህ አይነቱን ሰው ነው!!» (ያለፈው ምንጭ) ገፅ : 66 ላይም እንዲህ ይላል:

«በእኛ ላይ የሚዋሹብንና የሚቀጥፉብንማ፤ እኛ በጥቅል እንደምናከፍርና ሀገራቸው ላይ ሐይማኖታቸውን በነፃነት ይፋ ማድረግ የሚችሉ ሰዎችን ወደኛ መሰደድ ግዴታ አለባቸሁ እንደምንል አድርገው የሚያስወሩት ሁሉ፤ ይህ ሰዎችን ከአላህና ከመልእክተኛው ዲን ለማገድ ከሚዋሹብንና ከሚቀጥፉብን ነገሮች ነው። በዐብደልቃዲር አልጀይላኒ፣ በአሕመድ አልበደዊና በሌሎች መሰል አካላት መቃብር ላይ የተገነቡ ታቡቶችን (ዶሪሑችን) የሚያመልኩ ሰዎች ባለማወቃቸውና የሚገስፃቸው ሰው ባለመኖሩ ምክንያት ካላከፈርናቸው፤ በአላህ የማያጋራን ሰው ወደእኛ ባለመሰደዱ፣ ባለማከፈሩና ከእኛ ጋር ሆኖ ጠላትን ባለመፋለሙ ምክንያት እንዴት እናከፍረዋለን!? አላህ ሆይ ጥራት ይገባህ፤ ይህ ከባድ የሆነ ቅጥፈት ነው።»

ይህ አቋም የቁርአንና የሐዲስ መረጃዎች እንዲሁም የዑለማዎች ንግግሮች የሚያስፈርዱት ነገር ነው፤ የአላህ ﷻ ጥበብ እዝነትና ርህራሄም ይህንኑ ነው የሚያስፈርዱት፤ ከዚህም የተነሳ ሑጃ ሳያቆም በፊት ማንንም አይቀጣም። ምክንያቱም የሰው ልጅ አእምሮ ከአላህ ዘንድ ሑጃ የሚሆን መልእክት ሳይደርሰው እንዲሁ ራሱን ችሎ ለአላህ ምን፣ ምን እንደሚጎሳው ሊያውቅ አይችልም፤ ይህ ቢሆን ኖሮ በሰው ልጆች ላይ ሑጃን ማቆም በመልእክተኞች መልላክ አያጥርም ነበር። በሸሪዓዊ መረጃ የሰውየው እስልምና መወገዱ እስካልተረጋገጠ ድረስ፤ በመሰረቱ ወደ ኢስላም የሚጠጋ ሰው በኢስላም ላይ እንዳለ ነው።

አንድን ሰው ከኢስላም ከማስወጣታችን በፊት ሁለት ነገሮችን ማጤን ግድ ይላል።

① በአላህ ላይ መዋሸት እንዳይሆን ያ አክፋሪ ተደርጎ የታየው ነገር የቁርአንና የሐዲሥ መረጃዎች አክፋሪነቱን ሊጠቁሙ ይገባል።

② ካፊር የሚለው ብይን ሰውዬው ላይ ተስማሚ መሆኑ ልብ ሊባል ነው። ማለትም እንድናከፍረው የሚያስችሉን መስፍርቶች ተገኝተው፤ እንዳናከፍረው የሚከለክሉ ነገሮችም ከተወገዱ ማለት ነው። አሳሳቢ ከሆኑት መስፈርቶች መካከል አንዱ: እንዲከፍር ግድ ያደረገችበት ነገር ከኢስላም ጋር ተፃፃሪ መሆኗን ማወቁ ነው። ምክንያቱም አላህ ﷻ እንዲህ ብሏልና:

وَمَن يُشَاقِقِ الرَّسُولَ مِن بَعْدِ مَا تَبَيَّنَ لَهُ الْهُدَىٰ وَيَتَّبِعْ غَيْرَ سَبِيلِ الْمُؤْمِنِينَ نُوَلِّهِ مَا تَوَلَّىٰ وَنُصْلِهِ جَهَنَّمَ ۖ وَسَاءَتْ مَصِيرًا

(النساء: 115)

{ቅኑም መንገድ ለእሱ ከተገለጸ በኋላ መልክተኛውን የሚጨቃጨቅና ከምእምኖቹ መንገድ ሌላ የኾነን የሚከተል ሰው (በዚህ ዓለም) በተሾመበት (ጥመት) ላይ እንሾመዋለን፤ ገሀነምንም እናስገባዋለን፡፡ መመለሻይቱም ከፋች!}

(እዚህ ላይ እንደምታዩት) ሰውየው በእሳት ይቀጣ ዘንድ ቅኑ መንገድ ከተገለፀለት በኋላ መልእክተኛውን የሚቃረን መሆኑ መስፈርት ተደርጓል።

"የሰራት ሙኻለፋ ኩፍርም ሆነ ሌላ ውጤት እንደምታስከትል ማወቁ እንደመስፈርት ይታያል? ወይስ ሙኻለፋዋ የምታስከትለውን ውጤት ባያውቅም እንዲሁ ከቅኑ መንገድ ጋር የሚቃረን መሆኑን ማወቁ ብቻ በቂ ነው?" ከተባለ፤

መልሱ፦ መረጃዎች በግልፅ እንደሚጠቁሙት ሰውየው ላይ በሚገባው ልክ ለመበየን ከቅኑ መንገድ ጋር የሚቃረን መሆኑን ማወቁ ብቻ በቂ ነው። ምክንያቱም ባለቤቱን በረመዷን በቀን የተገናኘው ሰውየ "ከፋራ" እንዳለበት ካለማወቁ ጋር ነገር ግን ከሐቅ ጋር እንደተቃረነ ስላወቀ ብቻ ነቢዩ ﷺ ከፋራህን ግድ አድርገውበታል።

እንዲሁም የዝሙትን ሐራምነት የሚያውቅ ሆኖ ያገባ ዝሙት ሰሪ፤ ጥፋቱ ተቀጥቅጦ መገደልን የሚያስከትል መሆኑን ባያውቅም ይገደላል። ምናልባት የሚያስከትለውን ቢያውቅ ላይሰራ ይችል ይሆናል።

ባጠቃላይ አንድ ሰው የሚናገረው ንግግር ወይም የሚሰራው ስራ ኩፍር ወይም ፊስቅ መሆኑን ሳያውቅ ቢናገር ወይም ቢሰራ ዑዝር ይሰጠዋል። ይህም በቁርአንና በሐዲስ መረጃዎች እንዲሁም በዑለማዎች ንግግር መሰረት ነው።» ኢ ን ተ ሃ ። ምንጭ: (መጅሙውዑ ፈታዋ አሸይኽ አል ዑሠይሚይን 2/224 የዚህ ቁጥር ጥያቄ መልስ ላይ)።

⑥

የሱዑዲያ ጠቅላይ ሙፍቲ የሆኑት የሸይኽ ዐብደል ዐዚዝ ኣሉሸይኽ አስተማሪ የነበሩትና ከ1335 እስከ 1423 ሂጅሪ ይኖሩ የነበሩት አል ዐላመቱ አስ ሰለፊ አሕመድ ኢብኑ ሐጀር አል ቡኻሚ አላህ ይዘንላቸውና "አል ዐቃኢዱ አስ ሰለፊያ ቢአዲለቲሃ አነቅሊያ ወል ዐቅሊያ" (1/39) የተሰኘው ኪታባቸው ላይ እንዲህ ብለዋል፦

قال العلامة السلفي الأصولي القاضي أحمد بن حجر آل بوطامي رحمه الله في كتابه

العقائد السلفية بأدلتها النقلية والعقلية) "1/39")

هل يُحْكَم على الشخص المعيَّنِ أو الطائفة المخصوصة ـ المتلوّثة بتلك الخصال المُنافِيةِ للتوحيد ـ بالشِّرك والكفر مع أنها مؤمنةٌ بالله والرسول وآتيةٌ بِسائر الشرائع؟

الجواب : يقالُ هذا العملُ شركٌ أو كفر مثلًا كالسجود لولي أو الطواف بقبره والنذر له ولكن الشخص المعين أو الطائفة المخصوصة لا نُبادِرُها بالتكفير بل الواجب تَبليغُها بآيات القرآن وأحاديث الرسول ﷺ المبيّنة للشرك والمحذِّرة عنه وأنْ ليس لصاحبه نصيبٌ من الجنة، وأنَّ هذه الأعمالَ هي شركٌ ، فإذا أصرَّ الشخصُ المعيَّنُ أو الطائفةُ المخصوصةُ وعانندتْ ولم تقبلْ، فعند ذلك يحلُّ عليها إطلاقُ الشرك أو عليه إن كان فردًا معيَّنًا

«አንድ ሰው ላይ ወይም በአላህና በመልእክተኛው ﷺ አማኝ ሆና እና ሌሎችንም ሸሪዓዊ ድንጋጌዎችን ከመተግበሯ ጋር ተውሒድን የሚቃረኑ በሆኑ ባህሪያት የተለወሰች አንዲት ጀማዓ ላይ በተዕዪይን ነጥሎ በሺርክ ወይም በኩፍር ይበየናልን?

መልስ: ይህ ተግባር ሺርክ ነው ወይም ኩፍር ነው ይባላል፤ ለምሳሌ ለወልይ ሱጁድ ማድረግ ወይም በቀብሩ ዙሪያ ጠዋፍ ማድረግ፣ ወይም ለሱ ስለትን መሳል (ይህ አይነቱ ተግባር ሽርክ ነው ወይም ኩፍር ነው ሊባል ይችላል)፤ ነገር ግን (ይህን ተግባር የሚሰራን) አንድን ግለሰብ ወይም የሆኑትን ጀማዓ በተዕዪይን ነጥለን በኩፍር ለመሐከም አንሸቀዳደምም። ይልቁንም (ከማከፈር በፊት) ሺርክን የሚገልፁና ከሱም የሚያስጠነቅቁ፣ ስራዎቹ ሺርክ መሆናቸውንና ይህን ተግባር የፈፀመ ሰው በጀነት እጣ ፈንታ የሌለው መሆኑን የሚያብራሩ ቁርኣናዊ አንቀፆችንና ነቢያዊ ሐዲሦችን ልናደርሳቸው ግድ ነው። ያ ግለሰብ ወይም ያቺ ጀማኣ ከተመከረች በኋላ ባሉበት ስራ ላይ ከዘወተሩና ሐቅን ባለመቀበል እንቢተኛ ከሆኑ በተዕዪይን ነጥሎ የሺርክ ሑክም ይተሓከምባቸዋል።»

تنبيه :الشيخ ابن حجر آل بوطامي هو مِن مشايخ سماحة الشيخ عبد العزيز بن عبدالله آل الشيخ مفتي عام المملكة

⑦

የአኢሞቱ አድ ደዕዋ አን ነጅዲያ ተማሪዎች ከሸይኾቻቸው ቀስመውና ሰብስበው ያዘጋጁት ታዋቂ የሆነው ኪታብ ላይም እንዲህ የሚል አለ:

جاء في كتاب مجموعة الرسائل والمسائل النجدية:

المبحث الثالث :فيمن مات على التوحيد وإقامة قواعد الإسلام الخمس، وأصول الإيمان الستة، ولكنه كان يدعو وينادي ويتوسل في الدعاء إذا دعا ربه ويتوجه بنبيه في دعائه معتمدا على الحديثين اللذين ذكرناهما، أو جهلا منه وغباوة، كيف حكمهم؟

فالجواب أن يقال :قد قدمنا الكلام على سؤال الميت، والاستغاثة به، وبيَّنَّا الفرق بينه وبين التوسل به في الدعاء، وأن سؤال الميت والاستغاثة به في قضاء الحاجات وتفريج الكربات، من الشرك الأكبر الذي حرمه الله تعالى ورسوله، واتفقت الكتب الإلهية والدعوات النبوية على تحريمه وتكفير فاعله والبراءة منه ومعاداته؛ ولكن في أزمنة الفترات، وغلبة الجهل لا يكفر الشخص المعين بذلك حتى تقوم عليه الحجة بالرسالة ويبين له ويعرف أن هذا هو الشرك الأكبر الذي حرمه الله ورسوله .فإذا بلغته الحجة وتليت عليه الآيات القرآنية، والأحاديث

النبوية، ثم أصر على شركه فهو كافر؛ بخلاف من فعل ذلك جهالة منه ولم ينبَّه على ذلك. فالجاهل فِعلُه كفرٌ، ولكن لا يحكم بكفره إلا بعد بلوغ الحجة إليه؛ فإذا قامت عليه الحجة ثم أصرَّ على شركه فقد كفر، ولو كان يشهد أن لا إله إلا الله، وأن محمدا رسول الله، ويصلي، ويزكي، ويؤمن بالأصول الستة

الدرر السنية في الكتب النجدية)

(13 / 273)

«ሶስተኛው ጭብጥ መልእክት:

አምስቱን የኢስላም ማእዘኖችና ስድስቱን የኢማን መሰረቶች በማስገኘት በተውሒድ ላይ የሞተ ሰው፤ ነገር ግን አላህን ሲለምን ከላይ ባወሳናቸው ሁለት ሐዲሦች በመደገፍ ወይም ከጅህልናውና ከሞኝነቱ የተነሳ (ከአላህ ውጭ ያለን አካል) በመጣራት ተወሱል ያደርጋል፤ በዱዓውም ውስጥ በነብይህ ይሁንብህ ይላል። የዚህ አይነቱ ሰው ሑክም እንዴት ነው?

መልስ: የሞተን ሰው መለመንና በእሱም ኢስቲኟዛ ማድረግን በተመለከተ ንግግርን በርግጥ አሳልፈናል። በዚህ አይነቱ (የሺርክ) ተግባር እና በሞተው ሰውዬ ይሁንብህ እየተባለ በሚደረገው ተወሱል መካከል ያለውን ልዩነትም አብራርተናል። ሐጃዎችን እንዲፈፅምና ጭንቀቶችንም እንዲያስወግድ የሞተን ሰው መለመንና በእሱም ኢስቲኟዛ ማድረግ አላህና መልእክተኛው ሐራም ካደረጉት ከትልልቁ ሺርክ የሚመደብ መሆኑንም ገልፀናል። መለኮታዊ መፅሀፎችና የነቢያት ደዕዋዎችም ስራው ሐራም መሆኑን፣ ሰሪውም ካፊር መደረግ እንዳለበት፣ ከእሱ መፅዳት እንዳለብንና ጠላት ተደርጎ መይያዝ እንዳለበትም ተስማምተዋል። ነገር ግን ነቢያዊ ደዕዋ በሚቋረጥባቸውና በሚጠፉባቸው ዘመናት እንዲሁም ጅህልና በሚሃይልበት ወቅት ነቢያዊ ሑጃ እስከሚደርሰውና ተግባሩ አላህና መልእክተኛው ሐራም ያደረጉት ትልቁ ሺርክ መሆኑ ተገልፆለት እስከሚያውቅ ድረስ ያን ስራ በመስራቱ (ብቻ) ግለሰቡ ተነጥሎ በተዕዬይን አይከፈርም። ቁርአናዊ አንቀፆችና ነቢያዊ ሐዲሦች ተነብበውለት ሑጃ ከደረሰው ከዚያም በሺርኩ ላይ ከዘወተረ ግለሰቡ ካፊር ይሆናል። የዚህ አይነቱ ሰው ሑክም፦ ጃሂል ሆኖና የሚያስታውሰው ባለመኖሩ ምክንያት ሺርኩን ከሚሰራው ሰውዬ ሑክም ይለያል። ጃሂል ሆኖ (ይህን ተግባር) የሚሰራ ሰው ስራው ኩፍር ነው። ነገር ግን ሑጃ ከደረሰው በኋላ እንጂ ካፊር ተብሎ አይተሐከምበትም። ሑጃ ቆሞበት ከዚያ በሺርኩ ላይ ከዘወተረ ግን ላ ኢላሃ ኢለላህ ሙሐመዱን ረሱሉላህ ቢልም፣ ቢሰግድም፣ ዘካ ቢሰጥና በስድስቶቹ የኢማን መሰረቶች

ቢያምንም በርግጥ ካፊር ይሆናል።» (አድ ዱረር አስ ሰኒያ ፊል ኩቱብ አን ነጅዲያ: 13/227)

***** ***** ***** *****

ተከፊሮችና መሰሎቻቸው የሚንጠለጠሉባቸው መነሻዎች

◆ ራሳቸውን ወደ ኢስላም የሚያስጠጉ ሆነው ሽርክ ላይ የሚወድቁ አካላትን ከቀድሞዎቹ የዐረብ ሙሽሪኮች ጋር አንድ ማድረጋቸው

ሙስሊም ወንድሜ ሆይ! ዛሬ አንድን የተከፊሮችንና ሰለፊዮች ውስጥ የበቀሉት ድልድዮቻቸውን ሹበሃ በአላህ ፈቃድ ለመግለፅ እሞክራለሁ። ስለዚህ ቢረዝምም ትእግስት ኖሮህ አንብብ፤ ተጠቀም፤ ለሌሎችም አጋራው።

እሱም፦ እነዚህ አካላት በተለያየ ምክንያት አንዳንድ የሽርክ ተግባራት ላይ የወደቁ የዘመናችን ሙስሊም የሆኑ ማህበረሰቦችንና በጃሂሊያ ዘመን ይኖሩ የነበሩ ሙሽሪኮችን አንድ አድርገው ማየታቸውና አለመለያየታቸው ነው።

"ሑደሣኤል አስናን" የሆኑ ተከፊይሪዮችና ድልድዮቻቸው: «ከቁርአን መውረድና ከረሱል መልላክ በፊት ይኖሩ የነበሩ ዐረቦች ሑጃ ሳይደርሳቸው አላሁ ﷻ ሙሽሪክ ብሎ ሰይሟቸዋል፤ ስለዚህ ዛሬ ጊዜ ሺርክ ላይ ከመውደቃቸው ጋር ሙስሊም ብላችሁ የምትሰይሟቸው አካላትም እንደነዚያው ሙሽሪኮች ናቸው» ይላሉ።

"العبرة بعموم اللفظ لا بخصوص السبب"

የሚለውን ቃሚዳ እንደወረደ በመያዝ ማለት ነው። ለዚህ አቋማቸውም የሚከተሉትን የቁርአን አናቅፆችን ያጣቅሳሉ፦

١ـ وَإِنْ أَحَدٌ مِّنَ الْمُشْرِكِينَ اسْتَجَارَكَ فَأَجِرْهُ حَتَّىٰ يَسْمَعَ كَلَامَ اللَّهِ ثُمَّ أَبْلِغْهُ مَأْمَنَهُ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمْ قَوْمٌ لَّا يَعْلَمُونَ

(التوبة: ٦)

{ከአጋሪዎችም አንዱ ጥገኝነትን ቢጠይቅ የአላህን ቃል ይሰማ ዘንድ አስጠጋው:: ከዚያም ወደ መጠበቂያው ስፍራ አድርሰው:: ይህ እነሱ የማያውቁ ሕዝቦች በመኾናቸው ነው::} (አት - ተውባ: 6)

• አንቀፁ ላይ እነሱ እንደሚሉት: "ሑጃ ሊሆንበት የሚችለውን የአላህን ንግግር ከመስማቱ በፊት ሙሽሪክ ብሎ ገልፆታል"።

٢ـ لَمْ يَكُنِ الَّذِينَ كَفَرُوا مِنْ أَهْلِ الْكِتَابِ وَالْمُشْرِكِينَ مُنفَكِّينَ حَتَّىٰ تَأْتِيَهُمُ الْبَيِّنَةُ

(البينة: ١)

{እነዚያ ከመጽሐፉ ባለቤቶች ከኢጋሪዎቹም የካዱት ግልጹ አስረጅ እስከ መጣላቸው ድረስ (ከነበሩበት ላይ) ተወጋጆች አልነበሩም፡፡} (አል በዩናህ:1)

• እዚህ ላይም እንዲሁ "ማስረጃ ሳይመጣቸው በፊት ሙሽሪክ ብሎ ሰይሟቸዋል" ይላሉ።

በተጨማሪ መልእክተኛው ሙሐመድ ﷺ ለሰው ልጆች ሑጃ አድራሽ የሆኑ መልእክተኞች መልላካቸው ከተቋረጠ በኋላ የተላኩ መሆናቸው እነኚህ አካላቶች ያሉበትን አቋም የሚያጠናክርላቸው አድርገው ያስባሉ። በዚህ ዙሪያ አላህ ﷻ እንዲህ ብሏል:

يَا أَهْلَ الْكِتَابِ قَدْ جَاءَكُمْ رَسُولُنَا يُبَيِّنُ لَكُمْ عَلَىٰ فَتْرَةٍ مِّنَ الرُّسُلِ أَن تَقُولُوا مَا جَاءَنَا مِن بَشِيرٍ وَلَا نَذِيرٍ ۖ فَقَدْ جَاءَكُم بَشِيرٌ وَنَذِيرٌ ۗ وَاللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ

(المائدة: ١٩)

{እናንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! «አብሳሪና አስፈራሪ አልመጣልንም» እንዳትሉ ከመልከተኞች በመቋረጥ ጊዜ ላይ ሲኾን (ሕጋችንን) የሚያብራራ ኾኖ መልከተኛችን በእርግጥ መጣላችሁ፡፡ አብሳሪና አስፈራሪም በእርግጥ መጣላችሁ፡ ፡ አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው፡፡} (አል ማኢዳህ: 19)

እነዚህንና የመሳሰሉ አናቅፆችን መነሻ በማድረግ የቀድሞ ዘመናት የዐረብ ሙሽሪክ ማህበረሰቦች ሁጃ ሳይደርሳቸው ሙሽሪክ መባላቸውን ከድምዳሜ በመድረስ፤ በዘመናችን ያሉ ሽርክ ላይ የወደቁ ሙስሊሞችም ያላቸው ብይን ከእነዚያ ጋር አንድ አይነት ነው ይላሉ፤ በተጨማሪም ዱንያ ላይ ሙሽሪክ ስለሆኑ እነሱን መጋደል እንደሚቻልና በኣኺራ ግን ሁጃ ሳይቆምባቸው እንደማይቀጡ ድምዳሜ የደረሱ የተከፊር ቫይረስ የተጠናወታቸው ከፊል አካላት ቢኖሩም፤ ሌሎች ደግሞ በዱንያ ውስጥ እነሱን መጋደል አይቻልም፤ በኣኺራም ቅጣት አይከተላቸውም፤ ነገር ግን በሽርካቸው ምክንያት ኩፋር (ከሃዲዎችና ሙሽሪኮች) ናቸው የሚሉ አሉ።

ለዚህ አቋማቸው በተለያየ መንገድ መልስ ለመስጠት እሞክራለሁ ኢንሻአላህ።

①ኛ በአላህ ﷻ አንድነትና ትክክለኛ አምላክነት፣ እንዲሁም በሙሐመድ ﷺ መልእክተኛነት ፈፅሞ የማያምኑና በመሰረቱ ጥርት ያሉ ሙሽሪኮች ወይም ኩፋሮች ላይ የተሰጡ የኩፍርና የሺርክ ስያሜዎችን፤ አስላቸው (መሰረታቸው) ከእነዚህ ተቃራኒ በሆኑት ላይ ማለትም፦ በአላህ አንድነትና ትክክለኛ አምላክነት እንዲሁም በሙሐመድ ﷺ መልእክተኛነት በኢጅማል ወይም በጥቅል የሚያምኑ በሆኑ ሙስሊሞች ላይ እነዚህን ስያሜዎች መለጠፍና ሁለቱን አካሎች አንድ አድርጎ መመልከት፦ ከባድ ዙልም ከመሆኑም በላይ በርካታ ሸሪዓዊ መረጃዎች ጋር ይቃረናል።

የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች ሁጃ ሳይቆምባቸው በስተፊት ይህ ስያሜ የተሰጠባቸው ምክንያት፦ የአላህን አንድነትና ብቸኛ የአምልኮ ተገቢነቱን ባለማመናቸውና በርካታ የሽርካሽርክ ተግባራት ውስጥ የተዘፈቁ በመሆናቸው ነው። አስላቸውና ፈስላቸው ሙሽሪክ የሚያሰኟቸው ተግባራት እንጂ ሌላ ምንም የእምነት ወይም የተውሒድ ተግባራት ስለሌላቸው ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች ሁጃ ያልደረሳቸው በመሆኑ "የእሳት ናቸው" ተብሎም አይበየንባቸውም። ምክንያቱም ሁጃ አድራሽ መልእክተኞች በሌሉበት ዘመን የነበሩ ሽርክ ውስጥ የተዘፈቁና በአላህ ያላመኑ ሰዎች በአኺራ እንደሚፈተኑ የሚጠቁሙ መረጃዎች ስለመጡ ማለት ነው።

ነገር ግን በኢስላም ድንጋጌዎች በጥቅል አማኝ የሆኑ ሙስሊሞች በጅህል ወይም ባለማወቅ ምክንያት አንዳንድ የሽርክ ተግባራት ላይ ቢወድቁ ዑዝር ይሰጣቸዋል (አይከፈሩም)፤ በጅህል ሰበብ ያጠፉትም ስህተት ይቅር ይባልላቸዋል። በአኺራም ብዙዎቹ ዑለማዎች እንደሚሉት ጉዳያቸው ወደ አላህ ይመለሳል። ምክንያቱም ይህን እውነታ የሚደግፉ በርካታ መረጃዎች በመኖራቸው ነው። ለምሳሌ ያህል:

ከብዙ ሰሓቢዮች ተወርቶ ቡኻሪ፣ ሙስሊምና ሌሎችም በዘገቡት የነቢዩ ﷺ ሐዲሥ ላይ እንዲህ የሚል አለ፦

[መልካም ስራ የሌለው አንድ (ኢስራኢይሊይ) የሆነ ሰው ሊሞት ሲል ልጆቹን እንዲህ ሲል ተናዘዘ፦ "እኔ ለእናንተ ምን አይነት ወላጅ ነኝ?" እነሱም "ምን ያምር ወላጅ ነህ!" አሉት። "እንግዲያውስ ስሞት አቃጥሉኝና ፍጩኝ። ከዚያም በነፋሻማ ወቅት ባህር ውስጥ አመዱን በትኑት። በአላህ ይሁንብኝ! አላህ እኔን ከሞት ለማንሳት ችሎ ቢቀሰቅሰኝ (እና ቢያገኘኝ) አለማት ላይ ካሉ ፍጡራኖች

ማንኛውንም የማይቀጣውን ቅጣት ይቀጣኛል።" አላቸው። በሞተ ጊዜ ልጆቹ የታዘዙትን ፈፀሙ። ከዚያም አላህ ﷻ ባህሩንም የብሱንም የተበተነውን አመድ እንዲሰበስቡ አዘዘ፤ ሰውየውንም ቀስቀሰውና: "ይህን ለማድረግ ያነሳሳህ ምንድን ነው? " አለው። እሱም: "ጌታዬ! ፈርቼህ ነው" ሲል መለሰ። አላህም ﷻ "በእርግጥ ምሪሃለሁ" አለው።)

قال شيخ الإسلام ابن تيمية رحمه الله تعالى كما في

(مجموع الفتاوى :3/231)

فهذا رجلٌ شكَّ في قُدرةِ الله وفي إعادته إذا ذُرِّيَ، بل اعتقد أنه لا يُعاد، وهذا كُفْرٌ باتِّفاق المسلمين، لكن كان جاهِلاً لا يَعْلَمُ ذلك وكان مُؤمِناً يَخاف الله أن يُعاقِبه، فَغَفَرَ له بذلك

• ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ አላህ ይዘንለትና ሐዲሡን ሲተነትን እንዲህ ይላል፦

«ይህ በአላህ ችሎታ የተጠራጠረ ሰው ነው፤ ፈጭተው ከበተኑት አላህ ወደ ነበረበት ሊመልሰው የማይችል መሆኑንም አምኗል፤ ይህም (ተግባር) ኩፍር ለመሆኑ ሙስሊሞች ይስማማሉ፤ ነገር ግን ሰውየው ይህን የማያውቅ ጃሂል ነበር፤ የአላህን ቅጣት የሚፈራ ሙእሚን ወይም አማኝም ነበር፤ አላህ ﷻ በዚሁ ምክንያት ማረው።» (መጅሙዑል ፈታዋ: 3/231)

(وقال أيضا كما في كتابه "الاستقامة" 1/164) :

فهذا الرجل اعتقد أن الله لا يَقْدِرُ على جَمْعِه إذا فعل ذلك أو شكَّ، وأنه لا يَبْعَثُه وكُلٌّ مِن هَذَين الاعتقادَين كُفْرٌ يَكْفُرُ مَن قامتْ عليه الحُجَّةُ، لكنَّه كان يَجْهَلُ ذلك، ولم يَبْلُغْه العِلْمُ بما يَرُدُّه عن جَهْلِه وكان عنده إيمانٌ بالله وبأمره ونهيِهِ وَوَعْدِهِ وَوَعِيدِه، فخافَ مِن عقابه، فغفر الله له بخشيته

• በድጋሚ ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ (አል ኢስቲቃማ: 1/164) የተሰኘው ኪታቡ ላይ እንዲህ ብሏል፦

«ሰውዬው ይህን ካደረገ አላህ እሱን (ከተበተነበት) መሰብሰብ እንደማይችል እና እንደማይቀሰቅስም እርግጠኛ ሆኖ አምኗል፤ ወይም ሊሰበስበው ቻይ መሆኑን ተጠራጥሯል፤ እነኚህ ሁለት እምነቶች እያንዳንዳቸው ኩፍር (ከህደት) ስለሆኑ

ሑጃ የቆመበት ሰው ይከፍርባቸዋል። ነገር ግን እሱ ጃሂል ነበር፤ ከጅህልናው ሊያቅበው የሚችል እውቀትም አልደረሰውም፤ በአላህ፣ በትእዛዛቱ፣ በክልከላዎቹ፣ ቃል በገባባቸውና በዛተባቸውም ነገሮች አማኝ ነበር፤ ከዚህም የተነሳ የአላህን ቅጣት ፈራ፤ አላህም ለእሱ ባለው ፍርሃት ምክንያት ምህረትን ለገሰው።»

الشاهد من ذلك ـ بارك الله فينا وفيكم ـ

በጀህል ምክንያት ኩፍር ውስጥ ወድቆ የነበረው ይህ "ኢስራኢይሊይ" በስተመጨረሻ አላህ ለእሱ ምህረት ማድረጉ ነው።

በኣኺራ ምህረትን የሚነናፀፍ አካል ደግሞ በዱንያ ሙስሊም የነበረ ሰው ነው። ይህ ሰው በኣኺራ የአላህን ﷺ ምህረት በማግኘት የጀነት ባለቤት መሆኑና ዱንያ ላይ በኩፍር ስያሜ ካፊር ተብሎ መሰየሙ፤ እነዚህ ሁለት ብይኖች እሱ ላይ ሊሰባሰቡበት አይችሉም።

የኣኺራዊ ብይን መለያየት፡- የዱንያዊ ብይኖች መለያየታቸውን ከሚጠቁሙ በጣም ግልፅ ከሆኑ ማስረጃዎች የሚመደብ ነው። ይህ ማለት፡- *በኣኺራ ጀነት ኣይገባም፡- በዱንያ ሙስሊም የነበረ ሰው ቢሆን ኣንጂ!!*

በተጨማሪም ይህ ሰውዬ አማኝ ሆኖ አንድ ኩፍር የሆነ ተግባር ላይ ቢወድቅም፤ በኣኺራ እንደ አህሉል ፈትራ ሰዎች ሳይፈተን፤ በጅህልናው ምክንያት ምህረት ተደርጎለታል።

انظر كتاب: إشكالية الإعذار بالجهل في البحث العقدي للعميري

(ص: ٨٨ ـ ٩٦)

②ኛ ተከፊሪዮችና ድልድዮቻቸው የሚሞግቱት አጉል ሙግት ማለትም "በሺርክ የተሰየሙ የጃሂሊያ ዘመን ሰዎች ሁሉ ሑጃ ያልደረሳቸውና የአህሉል ፈትራ ብይን የሚሰጣቸው ናቸው" የሚለው አባባላቸው፡- ትክክል አይደለም፤ ይልቁንም ኢማም አን - ነወዊና ሌሎችም እንደሚሉት፡- እነኚህ ሰዎች: በዘመነል ፈትራ ውስጥ በመኖራቸው ምክንያት ምንም አይነት ሑጃ ያልደረሳቸው ሆነው በኣኺራ እንደሚፈተኑት ሰዎች አይነት እንዳልሆኑና ሑጃ የደረሳቸው መሆናቸውን ገልፀዋል።

انظر شرح صحيح مسلم للإمام النووي تحت حديث (203)

«إن أبي وأباك في النار»

وسيأتي كلامُه قريبًا مترجَمًا إن شاء الله.

ለዚህም ብዙ አመላካች ነገሮች አሉ። ከእነዚህም መካከል፦

•[1]• ሑጃ ማቆም ወይም ማድረስ የሚባለው ጉዳይ የአላህ መልእክተኛ ብቻ እንጂ ሌላ አካል ሊወሳው የማይችል ሀላፊነት አይደለም፤ ይልቁንም የመልእክተኛውን ተልእኮ ይፋ ማድረግ የሚችል ማንኛውም ግለሰብ ከተገኘ ሑጃውን ለማድረስ በቂ ነው። በዚህ ዙሪያ ኢማም አሽ - ሸውካኒ ሱረቱል ቀሰስ አንቀፅ ቁጥር (47) ላይ ያስቀመጠውን ትንታኔ ተመልከት። (ፈትሑል ቀዲይር)

•[2]• በዚያ ጃሂሊይ በሆነ ዘመን ዘይድ ኢብኑ ዐምር ኢብኑ ኑፈይል እና የመሳሰሉ አላህን ﷻ በብቸኝነት የሚያመልኩና በእሱም የማያሻርኩ መልካም የአላህ ባሮች ነበሩ።

• (ኢማሙል ቡኻሪ: 3826) እና (ኢማም አሕመድ: 5369) ኢብኑ ዑመርን በመጥቀስ ያስተላለፉት ሐዲሥ ላይ እንዲህ የሚል አለ፦

«ነቢዩ ﷺ ወሕይ ሳይወርድላቸው በስተፊት ዘይድ ኢብኑ ዐምር ኢብኑ ኑፈይልን ታችኛው "በልደሕ" የሚባል አካባቢ አገኙት፤ ያን ጊዜ ለነቢዩ ﷺ ስጋ ያለበት የምግብ ማእድ ተቀረበላቸው፤ እሳቸውም መብላትን እንቢ አሉ፤ እሳቸውም ለዘይድ አቀረቡለት፤ ዘይድም እንቢ አልበላም በማለት ቀጥሎ እንዲህ አለ: "እኔኮ እናንተ ለጣኦቶቻችሁ ከምታርዱላቸው ምግብ አልመገብም፤ እኔ የምመገበው የአላህ ስም ብቻ ተወስቶ የታረደን ምግብ ነው።»

• እንዲሁም ኢማሙል ቡኻሪ (3827) በዘገቡት ሐዲሥ ላይ አስማእ ቢንት አቢ በክር ረዲየላሁ ዐንሁማ እንዲህ ብላለች፦

«ዘይድ ኢብኑ ዐምርን ጀርባውን ከዕባ ላይ በማስደገፍ የቆመ ሆኖ ቁረይሾችን: (እናንተ ሰዎች ሆይ! በአላህ ﷻ ይሁንብኝ ከእኔ ሌላ እናንተ መካከል በኢብራሂም ዐለይሂሰላም ሐይማኖት ላይ ያለ ማንም ሰው የለም)።» ይል እንደነበር አስተላልፋለች።

•[3]• ኢማም ሙስሊም (203) ላይ እንደዘገቡት የአላህ መልእክተኛ ﷺ ለሰሓቢዩ: «የእኔም የአንተም አባቶች የእሳት ናቸው» ማለታቸው።

•[4]• በድጋሚ ኢማም ሙስሊም (976) ላይ እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ ﷺ: «ለእናቴ ኢስተኻፋር እንድጠይቅላት አላህን ፈቃድ ብጠይቀውም አልፈቀደልኝም፤ ቀብሯን እንድዘይርም አስፈቀድኩት፤ እሱም ፈቀደልኝ።» ማለታቸው።

ይህ ማለት የረሱል ﷺ ወላጆች የእሳት ናቸው ማለት ነው። አህሉል ጃሂሊያዎችም በኣኺራ ይፈተናሉ የሚባልላቸው አይደሉም ማለት ነው። ምክንያቱም አላህ ﷻ ሑጃን ሳያቆም አይቀጣምና። አህሉል ፈትራዎችም በኣኺራ እንደሚፈተኑ መረጃዎች መጥተዋል፤ ስለዚህ በዚያ ዘመን ይኖሩ የነበሩት የነቢዩ ﷺ ቤተሰቦችና መሰሎቻቸው የእሳት መሆናቸው በረሱል አንደበት መነገሩ፦ እነዚህ ሰዎች በዱንያ ሑጃ የደረሳቸው መሆናቸውንና በኣኺራ የማይፈተኑ መሆናቸውን ይጠቁማል!!

• ኢማም አን ـ ነወዊ "አባቴም አባትህም የእሳት ናቸው" የሚለውን የረሱልን ﷺ ንግግር ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል፦ «በዘመነል ፈትራ ወይም ነቢይ በሌለበት ዘመን ዐረቦች በነበሩበት የጣኦት አምልኮ ላይ ሆኖ የሞተ ሰው በኣኺራ የእሳት ነው፤ ይህ ሲባል የነቢያት ደዕዋ ወይም ሑጃ ሳይደርሳቸው እነሱን ተጠያቂ ማድረግና ተቀጭ ናቸው ማለት አይደለም፤ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች (የተቀጡትና ተጠያቂ የተደረጉት) የነቢዩላህ ኢብራሂምና የሌሎች ነቢያት ደዕዋ በእርግጥ ስለደረሳቸው ነው።)

እንዲሁም ታላቁ የቁርኣን ሙፈሲር ኢማም ኢብኑ ጀሪር አጦበሪ ቀጣዩን አንቀፅ እንዲህ በማለት ይተነትናል፦

وَاذْكُرُوا نِعْمَتَ اللهِ عَلَيْكُمْ إِذْ كُنتُمْ أَعْدَاءً فَأَلَّفَ بَيْنَ قُلُوبِكُمْ فَأَصْبَحْتُم بِنِعْمَتِهِ إِخْوَانًا وَكُنتُمْ عَلَىٰ شَفَا حُفْرَةٍ مِّنَ النَّارِ فَأَنقَذَكُم مِّنْهَا ۗ كَذَٰلِكَ يُبَيِّنُ اللهُ لَكُمْ آيَاتِهِ لَعَلَّكُمْ تَهْتَدُونَ

(آل عمران: ١٠٣)

{ጠበኞችም በነበራችሁ ጊዜ በእናንተ ላይ (የዋለውን) የአላህን ጸጋ አስታውሱ፡፡ በልቦቻችሁም መካከል አስማማ፡፡ በጸጋውም ወንድማማቾች ኾናችሁ፡፡ በእሳት ጉድጓድ አፋፍም ላይ ነበራችሁ፡፡ ከእርስዋም አዳናችሁ፡፡ እንደዚሁ ትመሩ ዘንድ አላህ ለእናንተ አንቀጾቹን ያብራራል፡፡} (አል ዒምራን: 103)

[...እዚህ ላይ አውስና ኽዝረጅን አላህ ወደ ኢስላም ሳይመራቸው በፊት የነበሩበትን የኩፍር ምሳሌ መግለፁ ነው፤ አላህም ﷻ እንዲህ አላቸው: "በእሱ ምክንያት ወንድማማቾች የሆናችሁበትን የኢስላምን ፀጋ በእናንተ ላይ ሳይውልላችሁ በፊት በነበራችሁበት ኩፍር ምክንያት ጀሀነም አፋፍ ላይ ነበራችሁ፤ በእናንተና ጀሀነም በመግባታችሁ መካከልም ያላችሁበት ኩፍር ላይ ሆናችሁ መሞት እንጂ ምንም ነገር አልነበረም፤ ይህ ቢሆን ኖሮ ደግሞ ዘላለም በውስጧ ትኖሩ ነበር፤ ነገር ግን አላህ ﷻ ወደ ኢማን ስለመራችሁ በእሱ ምክንያት አዳናችሁ"።]

ወኹላሰቱል ከላም፦ በኢስላማዊ ሸሪዓ በጥቅል አማኝ ሆኖ በጀህል ምክንያት ሺርክ ውስጥ የሚወድቅን ሰው፤ ጭራሽ መሰረታቸው ኩፍርና ሺርክ ከሆነባቸው ኩፋሩ ቁረይሽ ጋር አንድ አይነት ብይን መስጠት ይህ ትክክል አይደለም፤ "አልዒብረቱ ቢዑሙሚለፍዝ ላ ቢኹሱውሲስሰበብ" የሚለውን ቃዒዳ በመያዝ፤ ለኩፋሩ ቁረይሽ የመጡ አናቅፆችን አስላቸው ሙስሊም ለሆኑ አካላት ማውረድና እነሱን ማክፈርም፤ ከእውነታ የራቀ ከመሆኑም በላይ ከባድ ዙልም ነው።

ታዋቂው የነጅዱ ዓሊም፣ አልዐላመቱ፣ አል ኡሱውሊይ፣ አል ፈቂይህ፣ አል ሙፈሲር፣ አሽ ሸይኽ ዐብደረሕማን አስ ሰዕዲ ረሕመቱላሂ ዐለይህ እንዲህ ይላል፦

فكلُّ مَن كان مُؤمِنًا بالله ورسوله مُصَدِّقًا لهما، مُلتزِمًا طاعتَهما، وأنكر بعضَ ما جاء به الرسول، جهلًا، أو عَدَمَ علمٍ أن الرسول جاء به :فإنه وإن كان ذلك كُفْرًا، ومَن فَعَلَهُ فهو كافرٌ، إلا أنَّ الجهلَ بما جاء به الرسولُ يَمنعُ مِن تكفير ذلك الشخص المعيَّنِ، مِن غير فرقٍ بين المسائل الأصولية والفرعية، لأن الكفر جَحْدُ ما جاء به الرسول أو جحدُ بعضِه مع العلم بذلك

وبهذا عَرفتَ الفرقَ بين المقلِّدين من الكفار بالرسول، وبين المؤمن الجاحد لبعض ما جاء به جهلاً وضلالًا، لا عِلمًا وعِنادًا

"الفتاوى السعدية"

(ص: 443-447)

«በአላህና በመልእክተኛው አማኝ የሆነና፤ ትእዛዛቸውንም አጥብቆ የያዘ ማንኛውም ሰው፤ በጀህል ወይም ባለማወቅ ምክንያት መልእክተኛው ይዘው

የመጡትን ከፊሉን ቢቃወም፤ ይህ ተግባር ኩፍር ነው፤ ሰውየውም ካፊር ነው ተብሎ በኢጥላቅ ቢበየንበትም፤ መልእክተኛው ያመጡትን ነገር አለማወቁ ሰውየውን በተዕዩን ነጥለን ከማከፊር ይከለክለናል። ይህም መሰረታዊ የዲኑን ክፍሎችና መሰረታዊ ያልሆኑትን ባለመለያየት ነው። ምክንያቱም ኩፍር የሚኖረው መልእክተኛው ይዘው የመጡትን ሁሉንም ወይም ከፊሉን እያወቀ ሲክድ ነው፤ ይህ እንግዲህ በመሰረታቸው ጥርት ያሉ በረሱል ከሃዲ በሆኑ ጭፍን ተከታዮች መካከልና ሙእሚን ሆኖ እያወቀና በእምቢተኝነት ሳይሆን፤ ተሳስቶና ሳያውቅ ረሱል የመጡበትን ከፊሉን በሚክድ ሰው መካከል ያለውን ልዩነት ትገነዘባለህ ማለት ነው።» "አል ፈታዋ አስ ሰዕዲያ" : (443 _ 447)

• شَيْخ الإسلام ابن تيمية رحمه الله تعالى يقول:-

قال شيخ الإسلام ابن تيمية رحمه الله تعالى

فهذه المقالات هي كُفْرٌ لكنَّ ثُبُوتَ التكفير في حقّ الشخص المُعيَّن موقوفٌ على قيام الحجةِ التي يَكْفُرُ تاركُها

(بغية المرتاد، ص: 353)

• «...እነዚህ ንግግሮች ኩፍር ናቸው፤ አንድን ሰው ነጥሎ እሱን ለማከፈር ግን እንቢ የሚላት ሰው የሚክፈርባት የሆነችዋ ሑጃ በመድረሱ ላይ ያጠረ ወይም የተንጠለጠለ ነው።» (ቡኻየቱል ሙርታድ: 353)

• وقال" :وليس لأحدٍ أنْ يُكَفِّرَ أحدًا مِن المسلمين وإنْ أخطأ وغَلِطَ حتى تُقَام عليه الحجَّةُ وتُبَيَّنَ له المَحجَّةُ، ومَنْ ثَبَتَ إسْلامُهُ بيقينٍ لم يَزُلْ ذلك عنه بالشَّكّ، بلْ لا يزول إلَّا بعد إقامةِ الحُجَّة وإزالةِ الشُّبْهة

مجموع الفتاوى

(12/466)

«ከሙስሊሞች የሆነ ማንኛውም ሙስሊም ቢያጠፋም ቢሳሳትም ሑጃ እስከሚደርሰውና ቅኑ መንገድ እስኪገለፅለት ድረስ ለማንም አካል ይህን ሰው ማከፈር አይፈቀድለትም። ሙስሊምነቱ በየቂን የተረጋገጠለት ሰው፤ በጥርጥር ሙስሊምነቱን አይነጠቅም፤ ይልቁንም ሑጃ እስከሚደርሰውና ሹብሃው እስኪወገድለት ድረስ ሙስሊምነቱን አይቀማም!!» (መጅሙዑል ፈታዋ 12/466)

• وقال ابنُ تيمية رحمه الله " :التَّكْفِيرُ لَهُ شُرُوطٌ وَمَوَانِعُ قَدْ تَنْتَفِي فِي حَقِّ الْمُعَيَّنِ، وَأَنَّ تَكْفِيرَ الْمُطْلَقِ لَا يَسْتَلْزِمُ تَكْفِيرَ الْمُعَيَّنِ إلَّا إذَا وُجِدَتْ الشُّرُوطُ وَانْتَفَتْ الْمَوَانِعُ

[مجموع الفتاوى)12/487-488(].

• እንዲህም ብሏል፦ «ሰውን ለማከፈር የራሱ የሆነ መስፈርቶችና ከልካይ ነገሮች አሉት፤ (ይህን፣ይህን የተናገረ ወይም የሰራ ካፈር ነው) እየተባለ በልቅ ሰዎችን ማከፈር፤ አንድን ሰው ነጥሎ ማከፈርን አያስይዝም (አያስፈርድም)፤ ነገር ግን (ኩፍር ላይ የወደቀ አካል ላይ) መስፈርቶች ከተሟሉና ለማከፈር የሚከለክሉ ምክንያቶች ከተወገዱ ካፈር ይደረጋል።» (መጅሙዑል ፈታዋ: 12/ 487: 488)

• وقال ابن تيمية رحمه الله كما في الفتاوى مجموع ابن قاسم

(3/229)

إني دائمًا ومَنْ جالسني يعلم ذلك مِنِّي أَنِّي مِن أَعْظَمِ الناسِ نَهْياً عن أَنْ يُنْسَبَ مُعَيَّنٌ إلى تكفيرٍ وتفسيقٍ ومعصية، إلا إذا عُلِمَ أنه قد قامتْ عليه الحُجَّةُ الرِّساليَّة التي مَن خالَفَها كان كافراً تارة ، وفاسقاً أُخرى وعاصياً أخرى

وإني أقرّر أن الله قد غفر لهذه الأمة خطأها وذلك يعمُّ الخطأ في المسائل الخَبَرية القولية والمسائل العملية

وما زال السلفُ يتنازعون في كثيرٍ من هذه المسائل ، ولم يشهد أحد منهم على أحدٍ لا بكفرٍ ولا بفسق ولا بمعصية

• ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ ዐለይሂ ረህመቱላህ እንዲህ ብሏል:

[እኔ ሁልጊዜ አንድን ሰው በተዕዩን ለይቶ ወደ ኩፍር፣ ወደ ፊስቅ እና መዕሲያ ማስጠጋትን በጣም አድርገው ከሚቃወሙ ሰዎች የምመደብ ነኝ፤ ይህን እኔን የሚያቀማምጡ ሰዎችም ያውቃሉ!! ነገር ግን የተቃረናት ሰው እንደ ሁኔታው አንዳንዴ ካፈር፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ፋሲቅ ወይም ወንጀለኛ የሚሆንባት ነቢያዊ ሑጃ ሰውዬው ላይ በእርግጥ መቆሙ ከታወቀ በቀር (ከዚህ ውጭ ሑጃ ሳይቆምበት ካፈር፣ ፋሲቅና ዓሲ እያሉ መበየንን አጥብቀው ከሚያወግዙ ዑለማዎች ነኝ)። አሁንም እኔ ለዚህ ህዝበ ሙስሊም አላህ ስህተታቸውን በእርግጥ ምሯቸዋል በማለት ደጋግሜና አስረግጬ እናገራለሁ!! ስህተቱ ደግሞ ዐቂዳዊም ሆነ አሕካማዊ ጉዳዮችን ያጠቃልላል። ሰለፎች በበርካታ መሳኢሎች

ከመለያየታቸውም ጋር ከውስጣቸው አንዱ በሌላው ላይ በኩፍር ወይም በፊስቅ ወይም ደግሞ በወንጀል ይሐክሙ አልነበረም!!]

إلى أن قال

(وكنتُ أبيّنُ أنَّ ما نُقِلَ عن السلف والأئمة مِن إطلاق القول بتكفير مَن يقول كذا وكذا فهو أيضا حقٌّ؛ لكن يجب التفريقُ بين الإطلاق والتعيين

• ሸይኽል ኢስላም ቀጥሎ እንዲህ አለ:

[ከሰለፎችና ከአኢማዎች "ይህን፣ ይህን መሰል ንግግር የተናገረ ይከፍራል" እያሉ በኢጥላቅ (በልቅ) ተናግረውት ወደኛ የደረሰን ንግግራቸው ሐቅ መሆኑን እገልፅ ነበር፤ ነገር ግን በጥቅል የሚሰሐውንና በተዕዱን (በተናጠል) የሚተሓኽመውን ብይን መለየት ግድ ነው!!]

. . .

إلى أن قال : والتكفيرُ هو من الوعيد ؛ فإنه وإن كان القولُ تكذيبًا لِما قاله الرسولُ ، صلى الله عليه وسلم لكنَّ الرجل قد يكون حديثَ عهدٍ بإسلام، أو نشأ ببادية بعيدة ومِثْلُ هذا لا يُكَفَّر بِجَحْدِ ما يَجْحَدُه حتى تقومَ عليه الحجةُ، وقد يكون الرجلُ لم يسمعْ تلك النصوصَ ، أو سمعها ولم تَثْبُتْ عنده ، أو عَارَضَها عنده معارضٌ آخر أوجبَ تأويلها وإن كان مخطئا (اهـ

• ሸይኹል ኢስላም አሁንም ቀጠለ:

[ተከፊይር (ሰውን ከኢስላም ማስወጣት) ከወሚይድ (ዛቻዊ) ነጥቦች ነው፤ አንድ ንግግር መልእክተኛው ﷺ ከተናገሩት ንግግር ጋር የሚቃረን ቢሆንም ተናጋሪው ሰውዬ ግን አዲስ ሰለምቴ ሊሆን ይችላል፤ ወይም ራቅ ያለ ገጠራማ ስፍራ ሊኖር ይችላል፤ ይህን የመሳሰለ ሰው በሚከደው ከህደት ሑጃ እስካልቆመበት ድረስ አይከፊርም፤ እንዲሁም ይህ ሰው መረጃዎቹን አልሰማቸው ይሆናል፤ ወይም ሰምቷቸው ነገር ግን እሱ ዘንድ አልሠቡለት (አልተረጋጡለት) ይሆናል፤ ወይም መረጃዎቹን የሚቃረንበትና ተእዊል የሚያደርግበት የሆነ (ሹብሃ) እሱ ዘንድ ይኖረው ይሆናል፤ ሰውየው (በትክክለኛ እይታ) ስህተተኛ ቢሆንም።] (አል ፈታዋ: 3/229 - መጅሙዕ ኢብኑ ቃሲም)

***** ***** ***** *****

- **በግልፅ ባየነው እንሓከማለን ማለታቸው**

ወንድሞችና እህቶች!

ዛሬ ደግሞ - ኢንሻአላህ - ተከፊሪዮችና ድልድዮቻቸው ዑዝር ቢልጀህል የለም ለማለትና ሽርክ ላይ ባለማወቅ የወደቀን ሙስሊም ለማክፈር ወይም ከኢስላም ለማስወጣት ከሚደገፉባቸው መነሻዎች ሁለተኛውን ላስነብባችሁ ብቅ ብያለሁ!! ፅሁፉ በዐረብኛ ከተዘጋጀ ሰፋ ያለ ጥናታዊ ፅሁፍ የተወሰደ ስለሆነ በሰብር ይነበብ!!

የሰዎቹ መነሻ፡- "ሺርክ የሰራ ሰው (ጃሂልም ቢሆን) በዚሂር ከምናየው በመነሳት ሙሽሪክና ካፊር ነው ተብሎ ይተሐከምበታል" የሚለው ነው!!

يقولون :لَنا ما ظَهَرَ، فكلُّ مَنْ وقع في الشرك فهو مشركٌ كافر

ይህን ንግግር ተከፊሮችና ድልድዮቻቸው ደጋግመውና በሰፊው ሲያጦዙት የአንዳንድ ዑለማኦችን ንግግር አያይዘው ይጠቅሱ ይሆናል።

ሹብሃቸው ሰፋ ብሎ ሲተነተንም ይህን ይመስላል፡- [በባሮች መካከል ብይን የሚኖረው ከእነሱ በግልፅ በሚታየው ብቻ ነው፤ አንድ ሰው ላይ ሺርክ ወይም ኩፍር በገሃድ ከታየ፡- በገሃድ ካየነው ስራው ጋር የሚስማማ የሆነን ፍርድ እንፈርድበታለን።]

• ዑዝር ቢል ጀህል የለም ለማለትና ለማክፍር ይህን መነሻ ከተጠቀሙ አካላቶች መካከል፡- ሑሰይን እና ዐብደላህ የተባሉት የሸይኽ ሙሐመድ ኢብኑ ዐብዲል ወሃብ ልጆች ይገኙበታል ። (ረሒመሁሙላሁ ጀሚይዓ)

N.B ተከፊሪዮችና ድልድዮቻቸው ሲባል የእውር ድንብር አረማመድ የሚራመዱትን የምታውቋቸውን እንጭጮች እንጂ፤ ለኢጅቲሃድ አህል ሆነው ከኢጅቲሃዳቸው በመነሳት አቋሙን የሚያራምዱትን እነኚህን ዑለማኦችና መሰለኾቻውን የማያካትት መሆኑን ለሙኻፈሎች ልገልፅ እወዳለሁ።

ሁለቱ ግለሰቦች (አዱረር አሰኒያ: 5/154) ላይ እንዲህ የሚል ንግግር ተወስቶላቸዋል:

«ይህ የተውሒድ ደዕዋ ሳይደርሰው የሞተ ሰው የሚበየንበት ብይን (ምንድን ነው ከተባለ)፤ ሺርክ እየሰራና እያመነበት መሞቱ የሚታወቅ ሰው ከሆነ፤ ይህ በዚሂሩ

ከህደት ላይ ሆኖ ሞቷል ነው የሚባለው፤ ዱዓም አይደረግለትም፤ አይሰገድበትም፤ ሰደቃም አይሰደቅለትም»

አንዳንድ በዚህ ዘመን ካሉ ግለሰቦችም ይህን አይነት ድምዳሜ በመያዝ: "የሽርክ ተግባር በገሃድ የታየበት ማንኛውም ሰው ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ፦ ከኢስላም የወጣ ካፊር ነው!!" እስከ ማለት የደረሰ አለ።

• የተከፊሮችና ግልገሎቻቸው መንጠልጠያ ከሆኑት ኪታቦች መካከል (አልጀዋቡል ሙፊድ ፊ ሑከሚ ጃሂል አት ተውሒድ) የተሰኘው ኪታብ ገፅ 119 ላይ እንዲህ የሚል አለ:

«(አንድ ሰው ሺርክ በመስራቱ ብቻ ያለ ቅድመ ሁኔታ) "ኢብቲዳአን" በተዕዩን ወይም ተነጥሎ የሚከፈረው የዲን መሰረት በሆነው በተውሒድ ጉዳዮች ላይ ከሆነ ነው፤ ምክንያቱም ዱንያዊ ብይኖች የሚበየኑት በገሃድ ከታየው በመነሳት ብቻ ነውና፤ ስለዚህ ከኢስላም የሚያስወጣ የሆነውን ትልቁን ኩፍር የሰራ ሰው፦ በተዕዩን ካፊር ነው ይባላል፤ በግልፅ ካየነው ስራው በመነሳት ማለት ነው!!»

• ወንድሞች! አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ ዱንያዊ ብይኖችን በተመለከተ ሰዎች ላይ ግድ ያደረገባቸው፦ በግልፅ በሚያዩት እንዲበይኑና በውስጥ የሚሰራውን ደግሞ ለእሱው እንዲተውት መሆኑ የማያጠራጥር ጉዳይ ነው። ይህ በኢስላማዊ ሸሪዓ የተረጋገጠ መሰረት ነው። ሊደገፉበትና አጥብቀው ሊይዙት የሚገባ ጉዳይ መሆኑ በዑለማዎች መካከል የሚስማሙበት መሆኑን ኢማም አን ነወዊ፣ ኢብኑል ቀዩም፣ ኢብኑ ሐጀርና ሌሎችም በርካታ ዑለማኦች አውስተዋል።

• ኢማም አሽ ሻፊዒይ ከሌሎች ዑለማዎች ይልቅ ይህን ቃዒዳ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት፤ የተለያዩ መረጃዎችን በመጥቀስ ሸሪዓችን ውስጥ ያለውን ደረጃ፣ ከቃዒዳው የተፈለገበትንም እውነታና ወሰኖቹን ልዩ በሆነ ሁኔታ በመግለፅ ከሚታወቁ ቀደምት ኢማም ናቸው።

• (አል ኡም 4/148) የተባለው ኪታባቸው ላይ እንዲህ ብለዋል:

«ብይኖች የሚበየኑት በዚሂር ወይም በግልፅ ከሚታየው በመነሳት ነው፤ በ"ኘይብ" ወይም በውስጥ ስላለውና የማናውቀው የሆነው ነገር ባለቤቱ አላህ ብቻ ነው።... »

(الأُمّ: 4/148 للإمام الشافعي عليه رحمه الله)

እዚህ ቃሚዳ ላይ ዚሂር ሲባል የተፈለገበት፡- ከአንድ ሰው በግልፅ የምናየው ወይም የምንሰማው፡- ንግግር፣ ወይም ተግባር፤ ወይም ደግሞ ያመነበት ነገር፣ ወይም አስረጅና ምስክር የቆመበት ነገር ነው። ይህን በተመለከተ ኢማም አሽ ሻፊዒ እንዲህ ይላሉ፡-

وأحكامُ الله ورسولِهِ تدلُّ على أن ليس لأحدٍ أن يحكم على أحدٍ إلا بالظاهر والظاهرُ: ما أقر به أو ما قامت به بينةٌ تثبت عليه

(كتاب الأم:1/433)

ويقول أيضا :والحكم بالظاهر من القول أو البينة أو الاعتراف أو الحجة

(المرجع السابق :5/187)

«የአላህና የመልእክተኛው አሕካሞች ማንም ሰው በማንኛውም ሰው ላይ በዚሂር በታየው እንጂ የመፍረድ መብት እንደሌለው ይጠቁማሉ። ዚሂር ደግሞ፡- ሰውየው (ስራውን የሰራው መሆኑን) ያመነበት፣ ወይም መስራቱን የሚያረጋግጥ አስረጅ የቀረበበት ነው።» (አል ኡም: 1/433)

እንዲህም ብለዋል: «ፍርድ የሚፈረደው በግልፅ ከተገኘው ንግግሩ፣ ወይም በምስክር፣ ወይም በማመኑ፣ ወይም ማስረጃ በመቅረቡ ነው» (አል ኡም: 5/187)

ይህ ቃሚዳ ትክክል መሆኑን የሚጠቁሙ በርካታ መረጃዎችም አሉ። ለምሳሌ ያህል፡-

• ቁርአን ውሸታምነታቸውን የገለፀ ከመሆኑ ጋር ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ሙናፊቆችን ከእነሱ በግልፅ በሚያዩት ነገር ሙዓመላ ማድረጋቸውና ኢስላማዊ አሕካሞችን ለእነሱ መስጠታቸው ነው።

• እንዲሁም ኡሳመቱ ኢብኑ ዘይድ የተባለው ሰሓቢይ ከሙሽሪኩ ሰውዬ ጋር ጂሃድ ላይ እያሉ የተከሰተውን ክስተት የሚያወራውም ሰሒሕ የሆነ ቂሷ እንደ ምሳሌ ይጠቀሳል።

ይህ ቃሚዳ የተረጋገጠና የፀና ቢሆንም፤ በሺርካዊ ጉዳዮች ዑዝር ቢልጀህል የለም ለሚለው አቋም መደገፊያ ማድረግ ግን ስህተት ነው፤ ትክክል አይደለም!!

የስህተትነቱ መነሻም ከቃሚዳው የተፈለገውን ሙሉ ሀሳብ ጠለቅ ያለ መገንዘብን ካለመገንዘብ የመነጨ ነው።

لأنَّ المقصود بالظاهر الذي في القاعدة إنما هو الظاهرُ المتمحِّضُ الذي لا يُعارِضُهُ ظاهرٌ آخرُ، فإن عارضَه ما هو أقوى منه فإنه يؤخذ بالظاهر الأقْوى؛ ولهذا قال بعضُ الحنفية :البِناءُ على الظاهر واجِبٌ ما لم يَتَّبُتْ خِلافُهُ

)انظر "قواعد الفقه "للمجددي، ص:65 (و"ترتيب اللآلي في سلك المالي

(ناظر زادة :863

ምክንያቱም እዚህ ቦታ ላይ "ዚሂር" ወይም ግልፅ ሲባል የተፈለገበት፡- ሌላ ዚሂር የማይቃረነው ጥርት ያለ (ሷፊ) ዚሂር ነው። በግልፅነት ከእሱ የበለጠ ሌላ ግልፅ ተቀናቃኝ ከተገኘ፤ በግልፅነት በላጭ የሆነው ነው ተቀዳሚነት የሚኖረው። የሐነፊ መዝሀብ አራማጅ ከሆኑት አንዱ: «ዚሂርን መሰረት አድርጎ ብይንን መበየን ዋጂብ ነው፤ ከእሱ ተቃራኒ እስካልተገኘ ድረስ» ያለውም ለዚሁ ነው።

وقد أشار ابن القيم إلى هذا المعنى حيث بيَّن أنَّ الشارع إنما قَبِلَ توبةَ الكافرِ الأصليِّ مِن كُفرِهِ بالشهادتين، لأنه ظاهرٌ لا يُعارِضه ما هو أقوى منه؛ فوجب العمل به

.)3/142(انظر :إعلام الموقعين، لابن القيم.

• ኢብኑ ቀዪሚል ጀውዚያህ ዐለይሂ ረህመቱላህ "ኢዕላሙል ሙወቂዒን: (3/142) ላይ ይህን ሀሳብ የሚጠቁምን ንግግር በሚከተለው መልኩ ተናግሯል፡-

(አንድ አስሊ ካፊር ሽሃደተይንን በማስገኘቱ ምክንያት ከኩፍሩ እንደቶበተ ተደርጎ አላህ ሱብሓሁ ወተዓላ ተውበቱን የተቀበለበት ምክንያት፡- ካስገኘው ሽሃደተይን የበለጠ ሌላ ተቃራኒ ግልፅ ነገር ስለሌለ ብቻ ነው፤ ከዚህም የተነሳ ተውበቱን መቀበልና በዚሁ መስራራት ግድ ሆኗል።)

ፉቀሃዎች ይህን ቃዒዳ በቲዮሪ ደረጃ እንደተነተኑት ሁሉ፤ በዕለት ተዕለት ተግባራቸውም "ተጥቢይቅ" አድርገውታል።

"በግልፅ በታየው ነገር ላይ አሕካምን መገንባት" የሚለውን አስል በተግባር ደረጃ ኢማሙ አሽ ሻፊዒ ይከተሉት የነበረውን አካሄድ አስተውለን ብንመለከት፡-

አሕካሞች የሚገነቡበት ይህ ግልፅ ነገር ጥርት ያለ የሆነውን ግልፅ ብቻ መሆኑን እንረዳለን። ለምሳሌ ይህል አሽ ሻፊዒ እንዲህ ይላሉ:

وإن خطب جالِسًا، ولا يَدْرُون أصحيحٌ هو أو مريضٌ؟ فكان صحيحًا أجزأتهم صلاتهم، لأن الظاهر عندهم ألا يخطب إلا مريض وإنما عليهم الإعادةُ إذا خطب جالسا، وهم يعلمون أنه صحيحٌ

(الأمُّ، للشافعي :1/343)

«ኹጥባ አድራጊው ተቀምጦ ኹጥባ ሲያደርግ ሰወየው ጤነኛ ይሁን ህመምተኛ የማያውቁ ሆነው (ካዳመጡ በኋላ ተከትለውት ቢሰግዱ) ሰውየው ጤነኛነቱ ከሰገዱ በኋላ ቢረጋገጥም ሶላታቸው ታብቃቃቸዋለች፤ (ደግማችሁ ስገዱ አይባሉም)። ምክንያቱም እነሱ ዘንድ በዚሂር የሚታወቀው፦ ቁጭ ብሎ ኹጥባ የሚያደርገው የታመመ ሰው እንጂ ጤነኛ እንዳልሆነ ነው። ሶላታቸው የማታብቃቃቸውና ደግመው እንዲሰግዱ ግድ የሚሆንባቸው፦ ተቀምጦ ኹጥባ ሲያደርግ ጤነኛ መሆኑን እያወቁ ከሆነ ብቻ ነው።» (አል ኡም: 1/343)

• በድጋሚ ከሻፊዒይ ንግግር ሌላ ምሳሌ እንመልከት:

قال الإمام الشافعي رحمه الله :ولو صلى رجلٌ غريبٌ بقومٍ ثم شكُّوا في صلاتهم فلَمْ يَدْرُوا أكان كافرًا أو مسلمًا لم تكن عليهم إعادة حتى يعلموا أنه كافرٌ؛ لأن الظاهر أن صلاتَه صلاةُ المسلمين لا تكون إلا من مسلمٍ

(الأم :1/298)

«አንድ የማይታወቅ እንግዳ የሆነ ሰዎች ሰዎችን ኢማም ሆኖ ቢያሰግዳቸው፤ ከዚያም ይህ ያሰገዳቸው ሰውዬ ካፊር ይሁን ወይም ሙስሊም ባለማወቃቸው ምክንያት በሶላታቸው ቢጠራጠሩ፤ የሰውየውን ካፊርነት በገሃድ እስካላወቁ ድረስ ሶላታቸውን የመድገም ግዴታ የለባቸው፤ ምክንያቱም ከሰውየው በዚሂር የታየው ሶላት የሙስሊሞች ሶላት ነውና፤ ከሙስሊም እንጂ አይገኝም።» (አል ኡም: 1/298)

وانظر مزيدا من الأمثلة عند الشافعي الضوابط والقواعد الفقهية في كتاب الأُمِّ للشافعي، عبد الوهاب الحميد

(181 -185)

ይህ እንዲህ ከሆነ፤ በሌሎች ጉዳዮችም ያለው ሁኔታ እንዲሁ ነው። ማለትም፡- በአንድ ጉዳይ ላይ በዚህር በታየው የሚተሓከመው ከእሱ ጋር የሚቃረን ሌላ ዚህር እስከሌለ ድረስ ነው። ከዚህ በመነሳት ወደ ዋናው ጉዳያችን እንመለስና፤ ትልቅ ሺርክ መስራት በገሃድ የታየበት አንድ ሰው፤ ዚህሩ ከሶስት ሁኔታዎች አይወጣም።

① ሺርኩ ወደ ኢስላም ኢንቲሳብ የሌለውና በኢስላም የማያምን ከሆነ ሰው ሊገኝ ነው። ይህ አይነቱ ሰው ላይ ሌላ ተቀናቃኝ ዚህር ስለሌለ ከእሱ በዚህር በታየው በሺርኩ ነው የሚበየንበት።

② ምንነቱ ከማይታወቅ ሰው ሊገኝ ነው፤ ማለትም፡- ወደ ኢስላም ኢንቲሳብ ማድረጉም ሆነ አለማድረጉ በገሃድ የሚታወቅ ነገር የለም፤ ይህም ሰው እላዩ ላይ በገሃድ ከተገኘው ሺርክ ውጪ ሌላ ተቀናቃኝ ዚህር ስለሌለ ከእሱ በዚህር በታየው በሺርኩ ይበየንበታል።

③ ያ የሺርክ ተግባር እራሱን ወደ ኢስላም ኢንቲሳብ የሚያደርግ ከሆነ ሰው የተገኘ ሊሆን ነው፤ እንዲሁም በአላህ አንድነት ማመኑ፤ በኢስላም መሰረታዊ ጉዳዮች በጥቅል አማኝነቱና በመልእክተኛው ﷺ ላይም ልቅ የሆነ "ተስዲይቅ" በግልፅ የሚታይበት ከሆነ ሰው ሊገኝ ነው።

ففي هذه الحال تعارَضَ عندنا ظاهِرٌ يُوجِبُ ثُبُوتَ الإسلام، وظاهِرٌ يوجبُ ثُبوت الكفر

እዚህ ላይ ሁለት ግልፅ የሆኑ ነገሮች እርስበርስ ተጋጩብን፤ የኢስላም ስያሜ እንዲፀድቅለት ግድ የሚያደርግ ዚህር እና የኩፍር ስያሜ እንዲፀድቅለት ግድ የሚያደርግ ዚህር መሆቸው ናቸው።

والقِسْمةُ العقليةُ تقتضي ثلاثةَ أحوال :إما أن يُقَدَّم الحالُ الذي يُثْبِتُ له وَصْفَ الإسلام وإما أن يقدَّم الحالُ الذي يُثْبِتُ له وَصْفَ الكُفر وإما أن يُتَوَقَّف؛ فلا يُحْكَمُ بإسلامه ولا بكفره

በዚህ ጊዜ ሜንታል ዲቪዥን ወይም አእምሯዊ መከፋፈል የሚባለው ነገር ሶስት አይነት ሁኔታዎች እፊታችን እንዲጋረጡብን ያስፈርዳል።

[1] ወይ የኢስላምን ስያሜ የሚያፀድቀው ሁኔታ ሊቀደም ነው።

[2] ወይም የኩፍርን ስያሜ የሚያፀድቀው ሁኔታ ሊቀደም ነው።

[3] ወይ ደግሞ "ተወቅፍ" ሊደረግ ነው። ማለትም በኢስላምም ይሁን በኩፍር ስያሜ ላይበየንበት ነው።

ከእነዚህ ሶስት ሁኔታዎች ተቀዳሚነት የሚሰጠው ትክክለኛና አመዛኝ የሆነው ነው፤ አመዛኙን ሁኔታ ለመምረጥ የምንመለሰውም ወደ ዐቅል ሳይሆን ወደ ሸሪዓዊ መረጃዎች ነው። መነሻ የምናደርገውም እሱኑ ነው። ወደፊት እንደምናየው ሸሪዓዊ መረጃዎች ከሌሎቹ ሁኔታዎች ይልቅ የኢስላምን ስያሜ የሚያፀድቀውን ሁኔታ ማስቀደም ግዴታ እንደሚኖርብን በጠነከረና ግልፅ በሆነ መልኩ ይጠቁማሉ። በመስአላው ሙሐቂቁን የሆኑ የአህሉስ ሱና ዑለማዎች አቋምም ይኸው። ይህን በተመለከተ አሽ ሸይኽ ሙሐመድ ቢን ሷሊሕ አል ዑሠይሚን እንዲህ ይላሉ፦

فالأصلُ فيمن يَنتسِبُ للإسلام: بقاءُ إسلامِهِ حتى يتحقَّق زوالُ ذلك عنه بمقتضى الدليل الشرعي، ولا يجوز التساهل في تكفيره؛ لأن في ذلك مَحذُورَيْن عظيمين وهما افتراء الكذب على الله وعلى المؤمنين، وعَوْدُ وصفِ الكفرِ على المتساهِل

[«በመሰረቱ አንድ ወደ ኢስላም የሚጠጋ ወይም ሐይማኖቱ ኢስላም ነው የሚል ግለሰብ ሐይማኖቱ ከእሱ መወገዱ ሸሪዓዊ መረጃዎች በሚያስፈርዱት እስኪረጋገጥ ድረስ ሙስሊምነቱ እንዳለ ነው። ሰውየውን ማክፈርን አቅልሎ መመልከት አይፈቀድም፤ ምክንያቱም ሁለት ከባባድ አደጋዎች ስለሚከተሉ ነው። » እነሱም፦ በአላህ ላይና በአማኞች ላይ መቅጠፍ አለበት። እንዲሁም ሰዎችን ማክፈርን አቅልሎ የሚመለከተው ሰውዬ ላይ የክህደት ስያሜ ወደ ራሱ መመለሱ ነው።]

አህሉስ - ሱና ወልጀማዐዎች ከሌሎቹ ሁኔታዎች ይልቅ ኢስላም እንዲፀድቅለት የሚያደርገውን ሁኔታ "ራጂሕነቱን" ወይም አመዛኝነቱን ሲገልፁ ከበርካታ አንግሎች አንፃር ነው።

①ኛ ለአንድ ሰው በተዕዩይን ነጥለን የኢስላምን ስያሜ እንድናፀድቅለት ከሚጠቁሙ ሸሪዓዊ አካሄዶች ጋር ተስማሚ መሆኑ ነው። ሸሪዓዊ መረጃዎች፦ የኢስላምን ስያሜ ለማፅደቅ በጣም ዝቅተኛ ጠቋሚ የሆነ ነገር መገኘቱ በቂ እንደሆነ ያመላክታሉ። እንደ ምሳሌ የኡሳመቱ ኢብኑ ዘይድን ሐዲሥ እንመልከት።

• ኢማሙል ቡኻሪና ኢማም ሙስሊም ኡሳመቱ ኢብኑ ዘይድ የተባለው ሰሓቢይ እንዲህ ማለቱን ዘግበውልናል፦

[የአላህ መልእክተኛ ﷺ ጁሀይና ወደሚባሉ ጎሳዎች ዘመቻ ላኩን፤ እኛም ሄደን ንጋቱ ላይ በመውረር አሸነፍናቸው። የሸሹትም ሸሹ፤ እኔና የሆነ አንሷሪ አንዱን ሰው ተከትለን ደረስንበት፤ ከበብ አድርገን መፍለክለኪያ ስናሳጣው "ላ ኢላሃ ኢለሏህ" አለ። አንሷሪዩ ተወው፤ እኔ ግን በያዝኩት ጦር ወግቼ ገደልኩት፤ ከዚያ (የሰራሁት ስራ) በጣም ከበደኝና ለነቢዩ ነገርኳቸው። (በሌላ ሪዋያ) {ጉዳዩ ደረሳቸው} እና «ኡሳማ ሆይ! ላ ኢላሃ ኢለሏህ ካለ በኋላ ገደልከውን?» አሉኝ። እኔም: "እንዳንገድለው ፈርቶ በእሷ ለመጠበቅ ፈልጎ ነው ቃሏን የተናገራት" አልኳቸው። እሳቸውም: «ይህን የተናገረው ከግድያ ለመጠበቅ ፈልጎ ይሁን አይሁን (ምን አሳወቀህ)፤ ልቡን ሰንጥቀህ አይተኸዋልንዴ!?» አሉኝ። ምነው ከዚህ ቀን በፊት ባልሰለምኩ ብዬ እስከምመኝ ድረስ፤ የአላህ መልእክተኛ ﷺ ይህን መልሳቸውን ከመደጋገም አልተወገዱም።]

• የቁርአን ሙፈሲሮች ሱረቱ አን ኒሳእ አንቀፅ ቁጥር 94 ስር የጠቀሷቸው የኢብኑ ዐባስና የሚቅዳድ ኢብኑል አስወድ ሐዲሦች፤ እንዲሁም በሰሒሑል ቡኻሪ ሐዲሥ ቁጥር: (6865 እና 6866) የተዘገበው የሚቅዳድ ኢብኑል አስወድ ሐዲሥ እንደ ተጨማሪ ምሳሌ ይጠቀሳሉ።

እነዚህ ሐዲሦች ላይ የሰውየው ዚሂር ኡሳማ ኢብኑ ዘይድ እንደተገነዘበው ቃሏን ከግድያ ለመዳን የተናገራት መሆኑን ቢጠቁምም፤ ከዚህ ዚሂርነት የጎላ ሌላ ተቃራኒ ዚሂር ሰውየው ላይ ስለተገኘ የኢስላም ስያሜ "ኢብቲዳእን" (በጅምሩ) ሊፀድቅለት እንደሚገባ ነቢዩ ﷺ ገልፀውልናል።

ይህ ክስተት አንድ ግለሰብ ላይ ሁለት ሁኔታዎች የሚጋጩበት ሆነው ከተገኙበት:- የኢስላምን ስያሜ የሚያፀድቀውን ሁኔታ ማስቀደም እንደሚኖርብን በግልፅ ይጠቁማል!!

②ኛ አሽ ሸሪይዓ አል ኢስላሚያ ከሙናፊቆች ጋር ሙዓመላ ማድረጉ ነው። የኢስላም ሸሪይዓ ከሙናፊቆች በዚሂር ወይም በግልፅ ከሚታይባቸው ነገሮች በመነሳት ከትክክለኛ ሙስሊሞች ጋር ትስስር ያላቸውን አሕካሞች ለእነሱም ሰጥቷል። ይህን በተመለከተ ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ እንዲህ ይላል:-

وقد اتَّفق العلماءُ على أنَّ اسْمَ المسلمين في الظاهر يَجري على المنافقين؛ لأنهم استسلموا ظاهرا، وأَتَوْا بما أتوا به مِن الأعمال الظاهرة، بالصلاة الظاهرة والزكاة الظاهرة والحج الظاهر والجهاد الظاهر، كما كان النبيُّ ﷺ يُجْرِي عليهم أحكامَ الإسلام الظاهر

(مجموع الفتاوى :7/351)

«የሙስሊሞች ስያሜ በዚህር ለሙናፊቆች እንደሚሰጥ ወይም እንደሚውል ዑለማዎች በእርግጥ ተስማምተዋል፤ ምክንያቱም በዚህራቸው ኢስላምን ተላብሰዋልና። እንዲሁም ከሚሰሯቸው ግልፅ ስራዎች፣ ግልፅ ሰላት፣ ግልፅ ዘካ፣ ግልፅ ሐጅና ግልፅ ጂሃድን በገሃድ ይተገብሩ ከነበረው ተግባራቸው በመነሳት (የሙስሊሞች ስያሜ ተሰጥቷቸዋል)። ይህ ማለት ልክ የአላህ መልእክተኛ ﷺ በዚህራቸው ወይም በላያቸው ላይ የሚታየውን የኢስላምን አሕካሞች ይሰጧቸው እንደነበረው ማለት ነው።» (መጅሙዑል ፈታዋ: 7/351)

ይህ እንግዲህ የኢስላምን ስያሜ አፅዳቂ የሆነው ዚህር በሸሪዓችን ጥግ የደረሰ ደረጃና ቦታ እንዳለው ይጠቁማል። ጠንካራ የሆኑ አስረጂ ነገሮች እስካልተገኙም ድረስ እሱን መተላለፍ ትክክል አይሆንም።

③ኛ የኢስላም ስያሜ የፀደቀለትን ግለሰብ ማክፈርንና በዚህ ጉዳይ ላይ መሸቀዳደምን አጥበቀው ከሚያስጠነቅቁ መረጃዎች ጋር ይበልጥ ተስማሚ መሆኑ ነው። በዚህ ጉዳይ ሙተዋቲር ደረጃ የደረሱ በርካታ የረሱል ﷺ ሐዲሦች መጥተዋል።

ከእነዚህ ሐዲሦች መካከል፦

●[1]● ኢማሙል ቡኻሪ አቡ ሁረይራን (ረዲየላሁ ዐንሁ) በመጥቀስ የአላህ መልእክተኛ ﷺ እንዲህ ማለታቸውን ዘግቧል፦

إِذَا قَالَ الرَّجُلُ لِأَخِيهِ :يَا كَافِرُ فَقَدْ بَاءَ بِهِ أَحَدُهُمَا

«ሰውየው ወንድሙን "ያ ካፊር!" ካለ፤ በእርግጥ ከሁለቱ ወደ አንድኛቸው ተመለሰ»

●[2]● ኢማሙ አቡ ዳውድ (4687) ኢብኑ ዑመርን (ረዲየላሁ ዐንሁማ) በመጥቀስ ነቢዩ ﷺ ቀጣዩን ከባድ ዛቻ መናገራቸውን አስተላልፈውልናል፦

أَيُّمَا رَجُلٍ مُسْلِمٍ أَكْفَرَ رَجُلًا مُسْلِمًا، فَإِنْ كَانَ كَافِرًا وَإِلَّا كَانَ هُوَ الْكَافِرَ

ማንኛውም ሙስሊም ሰው ሌላን ሙስሊም የሆነን ሰው ካፊር ካደረገው፤ (እንደሱ ብይን ሰውየው በእርግጥ) ካፊር ከሆነ (ጥሩ ወይም ዳነ!!)፤ ያለበለዚያ ግን ተናጋሪው እሱ ራሱ ካፊር ይሆናል!!»

•³•ኢማሙ ሙስሊም (61) አቡ ዘርዒ (ረዲየላሁ ዐንሁ) በመጥቀስ ነቢዩ ﷺ እንዲህ ማለታቸውን ዘግቦልናል፡-

وَمَنْ دَعَا رَجُلًا بِالْكُفْرِ أَوْ قَالَ: عَدُوَّ اللهِ وَلَيْسَ كَذَلِكَ إِلَّا حَارَ عَلَيْهِ

«አንድን ግለሰብ በከህደት (ስያሜ) ወይም "አንተ የአላህ ጠላት" በማለት የተጣራ ሰው፤ ሰውየው እንደሚለው ካልሆነ ወደ ተጣሪው ይመለስበታል።»

④ኛ አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ "ኢዕዛርን" ወይም ሰዎችን ሳያስጠነቅቅ በፊት አለመቅጣትን መውደዱና ከቅጣትም ይልቅ ለእሱ ቅድሚያ መስጠቱን የሚያመላክቱ በርካታ መረጃዎች መኖራቸው ነው።

ኢማሙል ቡኻሪ (7416) እና ኢማሙ ሙስሊም (1499) ከሙጚረቱ ኢብኑ ሹዕባ (ረዲየላሁ ዐንሁማ) የተያዘን ቀጣዩን ሐዲሥ አስተላልፈውልናል፡-

قَالَ سَعْدُ بْنُ عُبَادَةَ: لَوْ رَأَيْتُ رَجُلًا مَعَ امْرَأَتِي لَضَرَبْتُهُ بِالسَّيْفِ، غَيْرُ مُصْفِحٍ عَنْهُ، فَبَلَغَ ذَلِكَ رَسُولَ اللهِ ﷺ فَقَالَ «أَتَعْجَبُونَ مِنْ غَيْرَةِ سَعْدٍ، فَوَاللهِ، لَأَنَا أَغْيَرُ مِنْهُ، وَاللهُ أَغْيَرُ مِنِّي، مِنْ أَجْلِ غَيْرَةِ اللهِ؛ حَرَّمَ الْفَوَاحِشَ مَا ظَهَرَ مِنْهَا وَمَا بَطَنَ، وَلَا شَخْصَ أَغْيَرُ مِنَ اللهِ، وَلَا شَخْصَ أَحَبُّ إِلَيْهِ الْعُذْرُ مِنَ اللهِ، مِنْ أَجْلِ ذَلِكَ ؛ بَعَثَ اللهُ الْمُرْسَلِينَ مُبَشِّرِينَ وَمُنْذِرِينَ، وَلَا شَخْصَ أَحَبُّ إِلَيْهِ الْمِدْحَةُ مِنَ الله، مِنْ أَجْلِ ذَلِكَ ؛ وَعَدَ الله الْجَنَّةَ

[አንድ ወቅት ሰዕድ ኢብኑ ዑባዳህ እንዲህ አለ፡- "አንድን ሰው ከባለቤቴ ጋር ብመለከተው በሰይፉ ጎን ሳይሆን በስለቱ በኩል እመታው ነበር"፤ ይህም ንግግር መልእክተኛው ﷺ ዘንድ ደረሰና እሳቸውም እንዲህ በማለት ተናገሩ: «በሰዕድ "ኻይራ" ቅናቻ ትጎረማላችሁን!? በአላህ ይሁንብኝ እኔ ከእሱ የበለጠ "ኻይራ" አለኝ፤ አላህ ደግሞ ከእኔ ይበልጥ "አኻየር" ነው፤ ከዚህም የተነሳ በግልፅም ሆነ በድብቅ የሚሰሩ መጥፎ ስራዎችን ሐራም አደረገ። ከአላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ የበለጠ ቅናቻ ያለው አንድም ሰው የለም። ከአላህም የበለጠ "ዑዝር" ወይም ሳይቀጣ በስተፊት ማስጠንቀቅ ወደሱ ይበልጥ ተወዳጅ የሚሆንለት ማንም ሰው የለም ፤ ከዚህም የተነሳ መልእክተኞችን አብሳሪና አስጠንቃቂ አድርጎ ልኳል። ...»]

ይህ ሐዲሥ ኢዕዛር ማድረግ ኢዕዛር ካለማድረግ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ መሆኑን ይጠቁማል፤ እሱም ወደ አላህ ይበልጥ ተወዳጅ ነው። እነዚህ ሁሉ

መረጃዎች ሙስሊም የሆነን አካል ከማክፈር መጠንቀቅ እንደሚኖርብንና ከማክፈር በፊት መረጋጋትና ሊሒኑ የሚገባቸውን ነገሮች ማጤን ግድ መሆኑን፤ እንዲሁም ለማክፈር መሽቀዳደም ሐራም መሆኑን ይጠቁማሉ።

አህሉስ ሱናዎች ከላይ ያለፉትንና የመሳሰሉትን ማእዘኖች መሰረት በማድረግ ከሌላው ይልቅ የኢስላምን ስያሜ የሚያፀድቀውን መሰረት ያስቀድማሉ፤ ይህም ዑለማኦች አንድን ሙስሊም ያለ በቂ መረጃ ማክፈርን አጠንክረው ያስጠነቀቁበትን ሚስጥር ይገልፅልሃል።

ነገር ግን አህሉስ ሱናዎች ይህን እምነት መከፈር ለሚገባውም ሰው ሳይቀር የተከፈርን በር ሙሉ ለሙሉ በሚዘጋ መልኩ ሁል ጊዜ የማይቀየርና የማይለወጥ ነገር አድርገው አያዩትም። ይልቁንም ከዚህ ሁኔታ ወደ ሌላኛው ሁኔታ እንዲሸጋገሩ ግድ የሚያደርግ ግልፅ መረጃ ከተገኘ፤ ማለትም ለሰውየው የኢስላም ስያሜ እንዲፀድቅለት ግድ ከሚያደርግ ዘሂር ይልቅ የክህደት ስያሜ እንዲፀድቅበት ግድ የሚያደርግ ዘሂር ጠንካራና በጣም ግልፅ ከሆነ፤ ያን ትተው ይበልጥ ግልፅ የሆነውን በመያዝ በኩፍር ይሐከሙበታል።

ከዚህም የተነሳ አህሉስ ሱናዎች ከቁርአንና ከሐዲስ መረጃዎች በመነሳት የተከፈር ሹሩጦችና ተከፈርን የሚከለከሉ መዋኒዖች የሚባሉ ማሰሪያዎችን አመጡ።

እነኚህን ነገሮች ያመጡበት ምክንያት፡- በአንዳንድ አስከፋሪ ተግባራት ላይ የወደቀ ወደ ኢስላም የሚጠጋ ግለሰብ፤ በላዩ ላይ ሁለቱ ሁኔታዎች ሲጋጩባቸው በፍትህ አመዛኙን ብይን ለመበየን እንዲያስችላቸው ነው። እነሱ ዘንድ ለብይን ግምት ውስጥ የሚገባው፡- ያለ ምንም አይነት ቅድመ ሁኔታ እንዲሁ አስከፋሪው ነገር በዘሂር ወይም በግልፅ መገኘቱ ብቻ ቢሆን ኖሮ፤ እነኚህን ሹሩጦችና መዋኒዖች ባላመጡ ነበር።

የአህሉስ ሱናዎች መዝሀብ ሸሪዓዊ መረጃዎች የሚያስፈርዷቸውን ነገሮችና የሰው ልጆችን ተፈጥሯዊ ሁኔታ አጣጥሞ በማስኬድ ላይ የተገነባ ነው። ማለትም ወደ ኢስላም ኢንቲሳብ የሚያደርግ የሆነ ግለሰብ ላይ ሁለት ዘሂሮች ሲጋጩባቸው፡- ግለሰቡ ያለበትን ነባራዊ እውነታና ሁኔታን የሚገልፁ ወደ ሆኑ ሙረጂሐቶች ወይም አመዛኝ ወደ ሆኑ ነገሮች ይሄዳሉ። ግለሰቡ ኩፍር ላይ ሲወድቅ እያወቀ በእንቢተኝነትና በአስተባባይነት ከሆነ፤ ወይም ከሐቅ ለማፈንገጥና ሐቁን ለመያዝ ተካሱል በማድረጉና በመሳነፉ ከሆነ፤ አለያም አቅልሎ በማየትም ከሆነ፣ ይህ ሰው ከኢስላም የወጣ ካፊር ተብሎ ይበየንበታል። ኩፍር የሆነውን ተግባር ሲሰራ ከኢስላም እስከ መውጣት እንደሚያደርሰው የማያውቅ ሆኖ ከሆነ ግን፡-

فإنه يبقى على الأصل، وهو ثبوتُ وصفِ الإسلام له

ይህ ሰው በመሰረቱ ላይ እንዳለ ተደርጎ ይታሰባል፤ ማለትም የኢስላም ስያሜ እንደፀደቀለት ይቀራል። ይህ አይነቱ ሁኔታ ብዙውን ጊዜ ሙስሊሞች ዘንድ የሚከሰት ነገር ነው። ምክንያቱም በኢስላምና በነቢዩ አማኝ የሆነ ግለሰብ በርካታ ጉዳዮችን መልእክተኛው የተናገሯቸው ወይም ያዘዙባቸው መሆኑን ሳያውቅ ሊያስተባብልባቸው ወይም ደግሞ ሊቃወማቸው ይችላል፤ መልእክተኛው የተናገሯቸው ወይም ያዘዙባቸው ነገሮች መሆናቸውን ቢያውቅ ኖሮ የሚያስተባብልና የሚቃወም ባልሆነ ነበር፤ ይልቁንም ለንግግራቸው የሚያድር፣ ትእዛዛቸውንም የሚፈፅምና ወደ አላህም ተመላሽ ነበር የሚሆነው።

(انظر مجموع الفتاوى لابن تيمية :7/337)

በዚህ ዙሪያ ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ "መጅሙዑል ፈታዋ" (7/337) ላይ ያወሳውን ተመልከት።

والحاصلُ ممَّا سبقَ أنَّ تكفيرَ المعيَّن المُنتسِبِ إلى الإسلام لا يصحُّ أن يُعْتَمَدَ في تكفيره على مجرَّدِ ما ظهر منه مِن المكفِّرات، وإنما لا بُدَّ فيه مِن التَّحقُّق مِن حاله ومعرفةِ منشإِ أفعاله؛ إذ أنَّ ذلك العبد مُتعارضٌ يحتاج إلى تحقُّقٍ وترجيحٍ وتبيُّنٍ لحقيقة أمره

ያሳለፍነው ሀሳብ ጠቅለል ሲል፦ ወደ ኢስላም የሚጠጋ የሆነን ሰው በተዕዩይን ነጥሎ ለማከፈር፤ ከሰውየው በሂሂር የሚታዩ አስከፋሪዎች መገኘታቸውን ብቻ በመደገፍ ማከፈር ትክክል አይደለም። ይልቁንም የሰውየውን ሁኔታ ማረጋገጥና የስራዎቹንም መንስኤ ማወቅ ግድ ነው። ምክንያቱም ሰውየው፦ ማስረገጥ፣ አመዛኙን መለየትና ትክክለኛ የሰውየውን ሁኔታ ማጣራት የሚያስፈልጋቸው ሁለት የሚጋጩ ሁኔታዎች እላዩ ላይ ስለተገኙ ማለት ነው።

"አል ሑክሙ ቢዞሂር" የሚለውን ቃሚዳ ተደግፈው ሺርክ በሆኑ መሳኢሎች ዑዝር ቢል ጀህል የለም የሚሉ አካላት የተሳሳቱ መሆናቸውን ከሚጠቁሙ ነገሮች መካከል፦ ይህ ንግግራቸው በማንኛውም የሐይማኖቱ መሳኢሎች ወይም ጉዳዮች፦ ሺርካዊ በሆኑትም ይሁን ባልሆኑት፣ መሳኢል ዞሂራም ይሁኑ መሳኢል ኽፊያ፣ በጀህልም ሆነ በተእዊል ዑዝር መስጠት እንዳይኖር የዑዝርን በር ሙሉ በሙሉ መዝጋትን ማስያዙ ወይም (ማስፈረዱ ነው)!!

ምክንያቱም ዑዝር ላለመስጠት ተፅኖ ፈጣሪ ወይም ወሳኝ የሆነው ጉዳይ፦ ከግለሰቡ በዞሂር የታዩት አከፋሪ ተግባራት መገኘታቸው ብቻ ከሆነ፤ ይህን ወሳኝ ነገር በሁሉም ዞሂር በሆኑ ነገሮችም ጭምር ተግባራዊ ሊያደርጉትና ሊያስኬዱት ግድ ይላቸዋል።

فمن أنكر صفةً من صفات الله بالجهل فهو غيرُ معذورٍ؛ بِحُجة أنه ليس لنا إلا الحُكم على الظاهر

ومن أوَّل صفةً من الصفات الإلهية فهو غير معذور؛ لأنه ليس لنا إلا الحكم على الظاهر

ومن أنكر خَلْقَ الله لأفعال العباد فهو غير معذور؛ لأنه ليس لنا إلا الحكم على الظاهر

ومن استحلَّ الخمر بالتأوُّل فهو غير معذور؛ لأنه ليس لنا إلا الحكم على الظاهر

ومن سجد لمخلوقٍ جاهِلًا بالحكم فهو غير معذور؛ لأنه ليس لنا إلا الظاهر

وهذا كله مخالِفٌ لِما دلَّتْ عليه النصوص الشرعية، ولِما عليه العلماءُ المحقِّقون من أهل السنة

ከዚህ በመነሳት፡-

• ከአላህ በርካታ ሲፋቶች አንዷን የተቃወመ ግለሰብ ዑዝር አይሰጠውም (ካፊር ነው)፤ ለምን? ከተባለ

"በዚሂር በታየው መበየን እንጂ ሌላ ነገር ስለሌለን በሚለው ሑጃ"!!

• ከአላህ ሲፋቶች የአንዷን ትርጉም የቀየረ ወይም ተእዊል ያደረገ፤ በግልፅ ባየነው እንጂ ስለማንበይን ሰውየው ዑዝር አይሰጠውም (ካፊር ነው)!!

• አላህ የባሮቾን ስራ የፈጠረ መሆኑን የተቃወመ ዑዝር አይሰጠውም (ካፊር ይሆናል)፤ ምክንያቱም እኛ ያለብን ግዴታ በገሃድ ባየነው መፍረድ ነውና!!

• አስካሪ መጠጦችን በተእዊል ሐላል ያደረገ ሰውም በዚሂር በተገኘው መሐከም እንጂ ሌላ ሀላፊነት ስለሌለብን ዑዝር አይሰጠውም፤ (ካፊር ነው።)፣፣፣

እንዲህ እያሉ መሐከም ግድ ሊላቸው ነው!!

ይህ ሁሉ ብይን ደግሞ ሸሪዓዊ መረጃዎችና ከአህሉስ ሱና የሆኑ ዑለማእ ሙሐቂቁን ከሚያራምዱት አቋም ጋር የሚጋጭ ዋልታ ረገጥ ብይን ነው!!

ይህን ቃሚዳ መነሻ አድርገው ዐዝር የማይሰጡ አካላት ግን በገሃድ ሲተገበሩ በሚታዩ አስከፋሪ በሆኑ በሁሉም ጉዳዮች ላይ ተግባራዊ አላደረጉትም፤ ይልቁንም ሺርካዊ በሆኑ መሳኢሎችና ግልፅ በሆኑ መሳኢሎች ብቻ ነው ቃሚዳውን ገድበው ተግባራዊ የሚያደርጉት።

አንድ ሰው በግልፅ ኩፍር ሲሰራ ከታየ ያ ኩፍር የሆነ ነገር መስአላ ዚሂራ ሳይሆን መስአላ ኸፊያ ከሆነ ወይም ደግሞ ሺርካዊ ጉዳይ ካልሆነ ዐዝር ይሰጡታል። ይህ ደግሞ ሰዎቹ በአካሄዳቸው ተናቁድ እንዳላቸውና በመሰረቱ የተሳሳቱ መሆናቸውን ያሳያል። ስለዚህ "በግልፅ በታየው ይተሓከማል" የሚለውን ቃሚዳ በመያዝ ዐዝር ቢልጀህል የለም በሚሉት ሰዎች አካሄድ ከተጓዝን እፊታችን ሁለት መንገድ እንጂ ሌላ አማራጭ አይኖረንም።

• ወይ፡- በሁሉም አስከፋሪ በሆኑ ጉዳዮች የዐዝር ቢል ጀህልን በር ዝግ ማድረግ፤ ብሎም አስከፋሪ ነገር ላይ ወድቆ የተገኘ ማንኛውንም ሰው ካፊር ነው ብለን መበየን፤ ምክንያቱም በግልፅ በተገኘው መበየን እንጂ ሌላ ሀላፊነት ስለሌለብን፤ የውሰጡ የአላህ ሀላፊነት ነው።

• ወይም ደግሞ፡- ሌሎች በርካታ ሸሪዓዊ መረጃዎች በሚያስፈርዱት መልኩ ቃሚዳው ጋር ተዓሙል ማድረግ ነው። ማለትም፡- የተከፊር ሸርጦች መሟላታቸውንና ከልካዮቹ መወገዳቸውን እርግጠኛ እስከንሆን ድረስ፤ ግለሰቡን ነጥለን የክህደትን ስያሜ ለመለጠፍ በግልፅ እላዩ ላይ የታየውን ዚሂር ነገር መገኘቱን ብቻ በመመርኮዝ ላናከፍር ነው።

ቃሚዳውን በከፊል ርእሶች ተግባራዊ ለማድረግ ተሞርኩዘውበት፤ በሌሎች ርእሶች ላይ ግን ተግባራዊ ላለማድረግ ቃሚዳውን ባለመሞርከዝ መለያየት፤ በዚህ አካሄዳቸው "ተናቁድ መንሀጂይ" ውስጥ የወደቁ ከመሆናቸው ጋር መረጃ የሌለውን መከፋፈልን ከፍለዋል።

ባጠቃላይ እስካሁን በተመለከትነው ሰፋ ያለ ዳሰሳ፡- ይህን ቃሚዳ መነሻ አድርገው ዐዝር ቢል ጀህልን የሚከለክሉ አካለቶች ሶስት አይነት ስህተት ውስጥ የወደቁ መሆናቸው ይገለፅለሃል።

①ኛ ዐለማኦች በዚህ ቃሚዳ ምን እንደፈለጉበት አልተገነዘቡም፤ የሚያዩዝበትን ወይም የሚንጠለጠልበትን ቦታም በደንብ አልለዩም። ምክንያቱም ዚሂር ሲባል መጀመሪያ ላይ እንደተቀደመው፡- ከእሱ ጋር የሚቃረን ሌላ ዚሂር አብሮት ያለ ሳይሆን፤ የሚጋጨው የሌለው ሷፊ ጥርት ያለ ዚሂር ነው የተፈለገበት።

② የኢስላምን ስያሜ ከሚያፀድቀው ዚሂር ይልቅ የኩፍርን ስያሜ የሚያፀድቀውን ዚሂር አስቀድመዋል። ይህም ከላይ እንዳሳለፍነው ሸሪዓዊ መረጃዎች ከሚጠቁሙት እውነታ ጋር ይጣረሳል።

③ ቃዒዳውን በሺርክ ጉዳዮች ብቻ እንጂ በሁሉም አስከፋሪ ነገሮች ላይ ተግባራዊ አላደረጉትም፤ ይህ ደግሞ መረጃ በሌለበት ነገር ብያኔ ሰጭነት ነው።

ስለዚህ ወንድሜ ሺርክ ላይ የወደቀን ሰው ባየህ ቁጥር "ለና ማ ዚሀረ" በሚል ሑጃ ሙስሊሞችን በማክፈር ዱንያ ኣኺራህን እንዳታጠፋ!!

አትቸኩል፤ በረድ ሰክን በል፤ ተረጋጋ፤ የሰውየውን ሁኔታ አስተውል፤ መስፈርቶች መሟላታቸውንና ከልካዮች መወገዳቸውንም እርግጠኛ ሁን፤ ሰለፊዩን የሆኑ ዑለማኦችን አማክር፤ ከዚያ በኋላ አላህ ፊት የማታፍርበትን ሑክም ከእነሱ በመነሳት ትሐከምበታለህ!!

فهذا هو الحقُّ ما به خفاءُ

فَدعْنِي مِن بُنَيَّاتِ الطَّرِيق

***** ***** ***** *****

- **መስአላ ኸፊያ እና ዚሂራ**

ኢኽዋኒ ወኣኽዋቲ! ለዛሬ ይገፍላችሁ የቀረብኩት፦ ባለማወቅ ሺርክ ላይ የወደቀ ሙስሊምን ዑዝር ቢል ጀህል ለመንፈግና ከኢስላም ለማስወጣት ተከፊሮችና መሰሎቻቸው ከሚንጠለጠሉባቸው ነገሮች ከባድ መንጠልጠያና ሁነኛ ምሽግ አድርገው በሚያስቡት መደበቂያቸው ዙሪያ ነው።

እሱም፦ በመሳኢል ዚሂራ እና መሳኢል ኸፊያ መካከል መለያየታቸው ነው።

የፅሁፉ መሰረት ሱዑዲያዊው ሸይኽ የሆነው ሱልጣን ቢን ዐብዲረሕማን አል ዑመይሪ ያዘጋጀው «ኢሽካሊየቱ አል ኢዕዛር ቢል ጀህል ፊል በሕሥ አልዐቀዲይ» (319_330) የተሰኘው ጥናታዊ ኪታብ ነው። በዚሁ አጋጣሚ፤ ኪታቡ እጅግ በጣም የተዋጣለት በመሆኑ ዐረብኛ መረዳት የሚችል እያንዳንዱ ሙስሊም ሰለፊዩም ሆነ ተከፊይሪዩ፣፣፣ እንዲያነቡት እመክራለሁ።

የዛሬው ፅሁፍ በቅድሚያ መስአላ ዚሂራና ኸፊያ የሚሏቸው ነገሮች ምንና እነማን እንደሆኑ ያትታል፤ ከዚያም በመስአላ ኸፊያ እንጂ በመስአላ ዚሂራ ዑዝር

እንደማይሰጥ የተናገሩ ዑለማኦች ንግግር ተወስቶበታል፤ እንዲሁም ሁለቱን መስአላዎች በመለያየት ዑዝርን ውድቅ ማድረግ ትክክል እንዳልሆነ ሰፋ ባለ መልኩ የተዳሰሰበት ረዘም ያለ ፅሁፍ ነው። ስለዚህ ወንድሜ አንብብ፤ ተገንዘብ፤ ተጠቀም፤ እራስህንም አድንና ለሌሎችም መዳን ሰበብ ሁን!! በእርግጥ ዛሬ ላይ ያለ ትውልድ ብዙው ማለት ይቻላል የሂማ ጉዳይ ሆኖ አጫጭር ፖስቶችንና ተሻሪዳቶችን እንጂ ረጃጅም ለሆኑ ዲናዊ ፅሁፎች ትኩረቱን ሰጥቶ ጀምሮ የሚጨርስ መኖሩ አጠያያቂ ሆኗል፤ ማንበብ እንደሚታወቀው ነቢያችን ﷺ ለመጀመሪያ ጊዜ ነቢይ ተደርገው ሊታጩ ሲሉ የታዘዙበት ቁጥር አንድ መለኮታዊ ትእዛዝ ነው። ከሰለፎች አንስቶም እስከ ቅርብ ዘመናት ድረስ ታላላቅ የዲኑ ሰዎች እዚህ ደረጃ የደረሱበትና ዲኑም እኛ ዘንድ የደረሰበት ምክንያት ንባብ ላይ ባላቸው የልፋትና ጥረት ምክንያት ነው።

ተርጓሚው በዚህ የትርጉም ስራው ላይ አንባቢያን በሚፈልጉት መጠንና ደረጃ ያህል ለማቅረብ የማይችል ቢሆንም፤ የአቅሙንና የተቻለውን ለማድረግ ይሞክራል። በዚህም ሆነ በሌላ ምክንያት አብዛኞች ችላ ቢሉትም ዛሬ ላይ አላህ የሻላቸው ይጠቀሙበትና ወደፊት ደግሞ ይበልጥ አንብበው የሚጠቀሙ የሆኑ የተሻሉ ትውልዶች ይፈጠሩ ይሆናል፤ ያንኔ ታድያ ዛሬ የተተከለ ተክል ነው ለእነሱ ከሹቡሃት ሐራራ መጠለያ ወይም ፍሬያማ ሆኖ ሊያገኙት የሚችሉት።

ወደ ጉዳዩ ስገባ

መሳኢል ዚሂራ ማለት፦ ለሁሉም ግልፅ የሆኑ የዲኑ ክፍሎች ሲሆኑ፤ ኽፊያዎቹ ደግሞ ለአንዳንድ ሰዎች ግልፅ ያልሆኑ ኢስላማዊ ጉዳዮች ናቸው።

እንደነሱ አባባል፦ መሳኢል ዚሂራዎቹ ሙስሊሞች መካከል በሰፊው ተሰራጭተው የሚገኙና ከኢስላማዊ ጉዳዮች መሆናቸው በግልፅ የሚታወቅ ስለሆነ፤ ማንኛውም ሰው በየትኛውም ዘመንም ሆነ ቦታ ይኑር፤ በጀህልም ሆነ በተእዊል ዑዝር አይሰጥባቸውም።

• መሳኢል ዚሂራ ከሚባሉት ውስጥ ለምሳሌ ያህል፦ ከተውሒድ አል ኡሉሂያና አር ሩቡቢያ ጋር ትስስር ያላቸው መሳኢሎች፣ ከትልቀኛው ሺርክ ጋር የሚያያዙ መሳኢሎች፣ ከኢስላማዊ ጉዳዮች የሚካተቱ መሆናቸው በገሃድ የሚታወቁ፦ አምስት አውቃት የሚሰገዱ ሰላቶች፣ ዘካ፣ ፆም፣ ሐጅና የመሳሰሉት፤ እንዲሁም የዝሙት፣ የአስካሪ መጠጦችና የመሳሰሉት አፅፀያፊ ተግባራት ሐራምነት፣፣፣ እነኚህ እንግዲህ በግልፅ የሚታወቁ ነገሮች ስለሆኑ አዲስ የሰለመ ሰውና ከዒልም መንደር ራቅ ያለ ስፍራ የሚኖር ሰው ካልሆነ በስተቀር በእነዚህ ግልፅ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በጅህልናም ሆነ በተእዊል ዑዝር አይሰጥም!!

የተከፊሮችና መሰሎቻቸው ወሳኝ ከሆኑ መመለሻዎች አንዱ የሆነው

አቡል ዑላ አራሺድ ያዘጋጀውን "ዓሪዱል ጀህል :39" ላይ ተመልከት።

• መሳኢል ኸፊያ የሚሏቸው ደግሞ፡- ከአላህ ስሞችና ባህሪያት ጋር ተያያዥነት ያላቸው መሳኢሎች፣ የአህሉስ ሱናዎችን ፈለግ የሚቃረኑ የሆኑ አካላት የሚያምኑባቸው ዐቂዳዊ ጉዳዮችና መሰረታዊ ያልሆኑ የኢስላም ከፍሎች እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ። (ዓሪዱል ጀህል: 43)

እነኚህ አካላት ለዚህ አቋማቸው የተደገፉበት ነገር፡- መሳኢል ዚሂራና ኸፊያን መለያየትን በግልፅ የሚያስገነዝቡ ሀሳቦችን ያዘሉ የነጅድ ደዕዋ መሪዎችና የሌሎች ዑለማዎች ተቅሪራቶች ወይም ንግግሮች ናቸው።

ሸይኽ ሙሐመድ ቢን ዐብዲል ወሃብ በአንዳንድ ንግግሩ፣ ሸይኽ ዐብደላህ አቡ ቡጠይን፣ ሱለይማን ቢን ሰሕማን፣ ሐመድ ኢብን ዐቲይቅና ሌሎችም፡- በንግግሮቻቸው ከተደገፉባቸው ዑለማዎች እንደምሳሌ የሚጠቀሱ ናቸው። (አቡል ዑላ ያዘጋጀውን "ደዋቢጡ ተከፊይሪል ሙዐየን": 71 — 74) ላይ ተመልከት።

• ሸይኽ ሐመድ ኢብን ዐቲይቅ (አድ ዱረር አስ ሰኒያ: 10/433) ላይ እንዲህ ይላል፡-

ومسألة تكفير المعين مسألة معروفة، إذا قال قولا يكون القول به كفرا، فيقال :من قال بهذا القول فهو كافر، لكن الشخص المعين إذا قال ذلك لا يحكم بكفره، حتى تقوم عليه الحجة التي يكفر تاركها

وهذا في المسائل الخفية، التي قد يخفى دليلها على بعض الناس، كما في مسائل القدر والإرجاء ونحو ذلك مما قاله أهل الأهواء فإن بعض أقوالهم تتضمن أمورا كفرية، مِن رَدِّ أدلة الكتاب والسنة المتواترة، فيكون القول المتضمن لرد بعض النصوص كفرا ولا يحكم على قائله بالكفر، لاحتمال وجود مانع كالجهل، وعدم العلم بنقض النص، أو بدلالته

«አንድን ሰው ነጥሎ በተዕዪይን ስለ ማከፈር የምታጠነጥነው መስአላ ታዋቂ የሆነች መስአላ ናት፤ ሲናገሩት ኩፍር የሚሆንን ንግግር አንድ ሰው ከተናገረው፤ ይህን ንግግር የተናገረ ሰው (በኢጥላቅ) ካፊር ነው ይባላል። አንድን ሰው ነጥለን ለማከፈር ግን የሚተዋት ሰው ካፊር የሚደረግባት ሑጃ እስካልቆመችበት ድረስ በካፊርነት አይበየንበትም። ይህ የሚሆነው ደግሞ መረጃዎቿ በአንዳንድ ሰዎች

ላይ ልትደበቅባቸው ወይም ግልፅ ላትሆንላቸው በምትችለው በመስአላ ኽፊያ ነው። አህሉል አህዋእ በቀደር፣ በኢርጃእና በመሳሰሉት መሳኢሎች እንደተናገሯቸው ያሉ ንግግሮች ማለት ነው። ምክንያቱም እነዚህ አካላት ከፊል ንግግሮች ውስጥ የቁርአንና ሙተዋቲር የሆኑ የሐዲሥ ማስረጃዎችን የሚመልሱበት ወይም የሚያስተባብሉበት ኩፍር የሆኑ አባባሎች ስለሚገኙ ነው። ስለዚህ አንዳንድ መረጃዎችን መመለስን አካትቶ የያዘው ንግግራቸው ኩፍር ቢሆንም በተናጋሪው ላይ ግን የኩፍር ብይን አይበየንበትም፤ ምክንያቱም፦ ሰውየው በተዕዪይን ተለይቶ እንዳይከፈር የሚከለክሉ ጅህልና እና የመሳሰሉ ከልካይ ነገሮች ሊኖሩ ስለሚችሉ ነው።»

• ሸይኽ ሙላ ዐሊይ ቃሪእንና አል ኢማም ሺሃቡዲን አልቀራፊን የመሳሰሉ የአራቱ መዝሀብ ተከታይ የሆኑ ዑለማኦች፦ "ከኢስላማዊ ጉዳዮች መሆናቸው በግልፅ የሚታወቁ ነገሮችን የሚቃረን ሰው ዑዝር ቢል ጀህል እንደማይሰጠው የገለፁ መሆናቸውን፤ እንዲሁም እነኚሁ መሻዪኾች መስአላ ዚሂራንና መስአላ ኽፊያን ለያይተው እንደሚያዩ የ(ዓሪዱል ጀህል) ባለቤት አቡል ዑላ አራሺድ እዚሁ ኪታቡ ላይ ገልፆል።

ወደነዚህ የመዝሀብ ዑለማዎች ይህን አቋም ሲያስጠጉ የተደገፉበት ነገር፦ "ከኢስላማዊ ጉዳይ መሆኑ በገሃድ የሚታወቅን ነገር መቃወም ከኢስላም የሚያስወጣ ትልቅ ኩፍር ነው" በማለት የገለፁት ንግግራቸው ነው። ("ዓሪዱል ጀህል" ገፅ: 45 ላይ ተመልከት)

ይህ መደገፋቸው ግን ትክክል አይደለም። ምክንያቱም የዑለማኦቹ ገለፃዎች የመጡት የሰራውን ሑክም ለመበየን እንጂ የሚሰራውን ሰው ሑክም ለመበየን አይደለምና!!

• ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያም ከሌሎች ዑለማዎች ይልቅ መስአላ ዚሂራና ኽፊያን ይለያያል ተብሎ ብዙ ጊዜ የሚናፈስለትና መስአላዋን ወደሱ የሚያስጠጉበት ዓሊም ነው።

• በዚህ ዙሪያ ሸይኽ አቡ ቡጠይን እንዲህ ይላል፦

فانظر إلى تفريقه بين المقالات الخفية والأمور الظاهرة، فقال في المقالات الخفية التي هي كفر قد يقال :إنه فيها مخطىء وضال لم تقم عليه الحجة التي يكفر صاحبها، ولم يقل ذلك في الأمور الظاهرة بل قال :ثم تجد كثيراً من رؤوسهم وقعوا في هذه الأمور فكانوا مرتدين، فحكم بردتهم مطلقاً ولم يتوقف في الجاهل

(الدرر السنية :10/355)

[ድብቅ በሆኑ አባባሎችና ግልፅ በሆኑ ነገሮች መካከል (ሸይኽል ኢስላም) መለያየቱን ተመልከት፤ «ኩፍር የሆኑ ኽፊይ አባባሎች ላይ ቢወድቅ ካፊር የሚደረግባት ሑጃ ስላልደረሰችው ጥመትን የፈፀመና የተሳሳተ ሰው ነው ሊባል ይችላል» አለ። ይህን ንግግር ግን ግልፅ ለሆኑ ነገሮች አላለውም። ይልቁንም፦ «ከመሪዎቻቸው ብዙዎቹን እነዚህ ነገሮች ላይ በመውደቃቸው ምክንያት ሙርተዶች ሆነው ታገኛቸዋለህ።» ብሎ ነው የተናገረው። ጃሂል በሆነውም ሰውዬ ጭምር ሳያመናታ ሙርተድ መሆናቸውን ልቅ በሆነ መልኩ በይኖባቸዋል።] (አዱረር አስ ሰኒያ: 10/355)

በድጋሚም ሸይኽ አቡ ቡጠይን የኢብኑ ተይሚያን ንግግር ትርጉም ሲገልፅ እንዲህ ብሏል፦

فهو لم يقل ذلك في الشرك الأكبر، وعبادة غير الله، ونحوه من الكفر، وإنما قال ذلك في المقالات الخفية

(الدرر السنية :10/389)

[(ኢብኑ ተይሚያ ሑጃ ሳይቆምበት በፊት አይከፈርም ያለው) ኽፊይ በሆኑ አባባሎች ላይ እንጂ፤ በሺርከል አክበር፣ ከአላህ ውጪ ያሉ አካላትን በማምለክና በመሳሰሉ የኩፍር ተግባራት ላይ አይደለም።] (አዱረር አሰኒያ: 10/389)

ይህ አቋም ወደ ኢብኑ ተይሚያ መጠጋቱ ትክክል መሆኑን የተደገፉባቸው የኢብኑ ተይሚያ ተቅሪራቶች ወይም ገለፃዎች ሁለት አይነት ናቸው።

①ኛ በጀህል ዑዝር ለመስጠት መሳኢል ዚሂራና መሳኢል ኽፊያ ተለያይተው መታየት እንደሚኖርባቸው ሊያስገነዝቡ የሚችሉ የሸይኹ ንግግሮች ናቸው። ከነዚህም መካከል፦

•[1]• ሸይኹ እንዲህ ማለቱ:

وهذا إذا كان في المقالات الخفية فقد يُقال إنه فيها مخطئ ضال لم تقم عليه الحجة التي يكفر صاحبها، لكن ذلك يقع في طوائف منهم في الأمور الظاهرة التي يعلم الخاصة والعامة من المسلمين أنها من دين المسلمين، بل اليهود والنصارى والمشركون يعلمون أن محمدًا ﷺ بُعث بها، وكفَّر من خالفها؛ مثل أمره بعبادة الله

وحده لا شريك له، ونهيه عن عبادة أحد سوى الله :من الملائكة والنبيين والشمس والقمر والكواكب والأصنام وغيرهم، فإن هذا أظهر شعائر الإسلام، ومثل أمره بالصلوات الخمس وإيجابه لها، وتعظيم شأنها، ومثل معاداة اليهود والنصارى والمشركين، ومثل تحريم الفواحش والربا والخمر والميسر ونحو ذلك ثم تجد كثيرا من رؤسائهم وقعوا في هذه الأمور فكانوا مُرْتَدِّين

(مجموع الفتاوى 4/54)

«ይህም ድብቅ በሆኑ ንግግሮች ነው፤ (አንድ ሰው በነዚህ ላይ ቢወድቅ)፡- ባለቤቷ የሚከፍርባት ሑጃ ያልደረሰችው፣ ጥመት ላይ የወደቀና የተሳሳት ሰው ሊባል ይችላል፤ ነገር ግን ከኢስላማዊ ጉዳዮች መሆናቸውን አዋቂዎቹም ብዙሃኖቹም የሚያውቁት በሆኑና ግልፅ የሆኑ ነገሮች ላይ ከእነሱ መካከል አንዳንዶች ዘንድ ይህ ጥፋት ሊከሰት ይችላል፤ ኧረ እንደውም ነቢዩ ሙሐመድ ﷺ የተላኩበትና የተቃረነውም ሰው የሚከፈርበት ጉዳይ መሆኑን አይሁዶች፣ ክርስቲያኖችና ሙሽሪኮችም ጭምር የሚያውቁት በሆነ ነገር፤ ለምሳሌ፡- አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ ያለ ተጋሪ ብቻውን እንዲመለክ ማዘዛቸው፤ መላእክት፣ ነቢያት፣ ፀሀይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ ጣኦታትና ሌሎችም አካላት ከአላህ ውጪ እንዳይመለኩ መከልከላቸው፤ እነዚህና የመሳሰሉት በጣም ግልፅ የሆኑ የኢስላም መገለጫዎች ናቸው። በአምስት አውቃት ሶላቶችም ማዘዛቸው፣ ግድ ማድረጋቸውና ደረጃዎቿንም ከፍ ማድረጋቸው እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ። እንዲሁም አይሁዶች፣ ክርስቲያኖችና ሙሽሪኮች ጠላት ተደርገው መፆዝ እንዳለባቸው፤ ፀያፍ ተግባራት፣ ወለድ፣ አስካሪ መጠጥ፣ ቁማርና የመሳሰሉት ነገሮች ሐራም መሆናቸው (ግልፅ ከሆኑ የኢስላማዊ ጉዳዮች መሆናቸው በግልፅ የሚታወቁ ነገሮች ናቸው።) ከእነዚያ የቢድዓ ሰዎች ዋና ዋናዎቹ እነዚህን ግልፅ የሆኑ ነገሮች ተቃርነው ኩፍር ውስጥ በመውደቅ ሙርተዶች ሆነዋል።»
(መጅሙዑል ፈታዋ: 4/54)

ይህ የሸይኽል ኢስላም ንግግር መሳኢል ዚሂራንና ኽፊያን መለያየትን ወደሱ የሚያስጠጉ አካላቶች በዋነኝነት ከሚደገፉባቸው ንግግሮቹ የሚመደብ ነው።

•²• ቀጣዩን አባባል መናገሩ፡-

وفي الحقيقة فكلُّ ردٍّ لِخبر الله أو أمره :فهو كُفْرٌ دقَّ أو جلَّ لكن قد يُعْفَى عما خفيتْ فيه طُرقُ العلم، وكان أمرا يسيرا في الفروع .بخلاف ما ظهر أمرُه، وكان مِن دعائم الدين من الأخبار والأوامر

(الدرر السنية: 10/388)

«እውነታው ሲታይ የአላህን ንግግር ወይም ትእዛዝ መመለስ ወይም አለመቀበል መጠኑ ትንሽም ይሁን ትልቅ፡- ኩፍር ነው። ነገር ግን ስለዚያ ነገር ማወቂያ መንገዶቹ ሊደበቁበት የሚችልን ጉዳይ (ቢመልስ) ይቅር ሊባል ይችላል። ቅርንጫፋዊና ቀላል ጉዳይም ከሆነ እንዲሁ። ይህም ከአላህ ንግግሮችና ትእዛዛቶች የሆኑ ግልፅ የኢስላም መሰረቶች ከሆኑት በተቃራኒ ማለት ነው» (አድ ዱረር አስ ሰኒያ: 10/388)

②ኛ ጃሂል የሆነን ሰው ሳያስቀር በኢጥላቅ: "ይህን ተግባር የፈፀመ ካፊር ነው፤ ወይም ሙሽሪክ ነው፤ ወይም ሙርተድ ነው" በማለት የተናገራቸው ንግግሮቹ ናቸው። ለምሳሌ ያህል (መጅሙዑል ፈታዋ: 35/105) ላይ እንዲህ ማለቱ:

من لم يعتقد وُجوبَ الصلوات الخمس والزكاة المفروضة وصيام شهر رمضان وحج البيت العتيق ولا يحرّم ما حرم الله ورسوله من الفواحش والظلم والشرك والإفك: فهو كافرٌ مرتد يستتاب فإن تاب وإلا قتل باتفاق أئمة المسلمين ولا يُغني عنه التكلُّم بالشهادتين

(مجموع الفتاوى :35/105)

«የአምስት አውቃት ሰላቶችን ግዴታነት ያላመነ፣ ፈርድ የሆነውንም ዘካ ዋጅብነት፣ የረመዷን ወር ፆምን ግዴታነትና ጥንታዊውን ቤት መጎብኘት ዋጅብ መሆኑን ያላመነ ሰው፤ እንዲሁም፡- ዙልም፣ ሺርክ፣ ቅጥፈትና የመሳሰሉት አላህና መልእክተኛው ሐራም ያደረጓቸው ነገሮችን ሐራም አድርጎ የማያምን ከሆነ፤ ይህ ሰው ካፊርና ሙርተድ ነው፤ ተውበት ይጠየቃል፤ ከቶበተ ጥሩ፤ ካልሆነ ግን በአኢመቱል ሙስሊሚን ስምምነት ይገደላል። ላ ኢላህ ኢለሏህ፤ ሙሐመዱን ረሱሉላህ ማለቱ አይጠቅመውም»

እነሱ እንደሚሉት ኢብኑ ተይሚያ በዚህና በመሳሰሉት ንግግሮቹ "የሺርክ ተግባራትን የሰራ ሰው ካፊር ነው" በማለት በጥቅል በይኗል፤ በእነዚህ ነገሮች ላይ ለጃሂል ዑዝር መስጠት እምነቱ ቢሆን ኖሮ "ጃሂል ሲቀር" በሚል ከጥቅል ብይኑ ያወጣው ነበር። በዚህ ዙሪያ አቡ ቡጠይን መላኢካዎችን የተገዛ ሰው ካፊርነቱን የበየነበትን የሸይኽል ኢስላምን ንግግር ሲያብራራ እንዲህ ይላል ፡-

فانظر قوله :«فهو كافرٌ بإجماع المسلمين»، فحكم بكفر من هذه حاله، وأنه) إجماع المسلمين، ولم يقل في هذا الموضع لم يمكن تكفيره بذلك حتى يبين له ما جاء به الرسول، وقوله: «فمن جعل الوسائط على هذا الوجه فهو كافر مشرك يجب قتله «فجزم بكفره قبل الاستتابة

(فتاوى الأئمة النجدية :3/307)

[«እሱ በሙስሊሞች ስምምነት ካፊር ነው» ማለቱን ተመልከት፤ እንደምታየው ባህሪው ይህ የሆነን ሰው በኩፍር ሀክሞበታል፤ በዚህም ላይ ሙስሊሞች ኢጅማዕ እንዳላቸው ገልፆል። እዚህ ቦታ ላይ «መልእክተኛው ይዘው የመጡት እስኪገለፅለት ወይም ሑጃ እስኪቆምበት ድረስ ይህን በማድረጉ ብቻ ሰውየውን ማክፈር አይቻልም» አላለም። «በዚህ መልኩ አቃራቢዎችን የያዘ ሰው ካፊር ነው ሙሽሪክም ነው፤...» በማለት የተናገረውንም ተመልከት፤ ተውበት ሳይጠየቅ በፊት ካፊርነቱን ቁርጥ አድርጎ ነው የበየነበት።] (ፈታዋ አል አሊማህ አን ነጅዲያ: 3/307)

• በተጨማሪም የሰሪውና የሰራው ሁክም ኢብኑ ተይሚያ ዘንድ ተለያይቶ የሚታየው በመሳኢል ዚሂራ ሳይሆን በመሳኢል ኸፊያ ብቻ መሆኑን በርካታ የነጅድ ዑለማና አኢማዎች ገልፀዋል። በዚህ ዙሪያ ዐብደላህና ኢብራሂም የተባሉ የሸይኽ ዐብደለጢፍ ልጆችና ሱለይማን ኢብኑ ሰሕማን በአንዳንድ ሙኻሊፎች ላይ ረድ ሲያደርጉ (አድ ዱረር አስ ሰኒያ:10/432) ላይ እንዲህ ብለዋል፦

وأما قوله" :نقول بأن القول كفرٌ، ولا نحكم بكفر القائل"؛ فإطلاق هذا جهل» صِرفٌ، لأن هذه العبارة لا تنطبق إلا على معين، ومسألة تكفير المعين مسألة معروفة إذا قال قولاً يكون به كفراً، فيقال :من قال بهذا القول فهوا كافر، لكن الشخص المعين إذا قال ذلك لا يحكم بكفره حتى تقام عليه الحجة التي يكفر تاركها، وهذا في المسائل الخفية التي قد يخفى دليلها على بعض الناس، كما في مسائل القدر والإرجاء ونحو ذلك مما قاله أهل الأهواء، فإن بعض أقوالهم تتضمن أموراً كفرية، من رد أدلة الكتاب والسنة المتواترة، فيكون القول المتضمن لرد بعض النصوص كفراً، ولا يحكم على قائله بالكفر، لاحتمال وجود مانع كالجهل

(الدرر السنية :10/432)

[«ንግግሩ ኩፍር ነው እንላለን፤ ተናጋሪው ላይ ግን በኩፍር አንሐክምበትም» የሚለው አባባሉን በልቅ መናገሩ፦ ጥርት ያለ ጅህልና ነው፤ ምክንያቱም ይቺ

አባባል ከሙዐየን ወይም ተነጥሎ ከሚተሓከምበት ሰው ጋር እንጂ ተዛማጅነት የሌላት ናትና። አንድን ሰው ነጥሎ በተዕዪይን ስለ ማከፈር የምታጠነጥነው መስአላ ደግሞ ታዋቂ የሆነች መስአላ ናት፤ ሲናገሩት ኩፍር የሚሆንን ንግግር አንድ ሰው ከተናገረው፤ ይህን ንግግር የተናገረ ሰው (በኢጥላቅ) ካፊር ነው ይባላል። አንድን ሰው ነጥለን ለማከፈር ግን የሚተዋት ሰው ካፊር የሚደረግባት ሑጃ እስካልቆመችበት ድረስ በካፊርነት አይበየንበትም። ይህም የሚሆነው መረጃዎቿ በአንዳንድ ሰዎች ላይ ልትደበቅባቸው ወይም ግልፅ ላትሆንላቸው በምትችል በመስአላ ኽፊያ ነው። አህሉል አህዋእ በቀደር፣ በኢርጃእና በመሳሰሉት መሳኢሎች እንደተናገሯቸው ያሉ ንግግሮች ማለት ነው። ምክንያቱም እነዚህ አካላት ከፊል ንግግሮች ውስጥ የቁርኣንና ሙተዋቲር የሆኑ የሐዲሥ ማስረጃዎችን የሚመልሱበት ወይም የሚያስተባብሉበት ኩፍር የሆኑ አባባሎች ስለሚገኙ ነው። ስለዚህ አንዳንድ መረጃዎችን መመለስን አካትቶ የያዘው ንግግራቸው ኩፍር ቢሆንም በተናጋሪው ላይ ግን የኩፍር ብይን አይበየንበትም፤ ምክንያቱም፦ ሰውየው በተዕዪይን ተለይቶ እንዳይከፈር የሚከለክሉ ጅህልና እና የመሳሰሉት ከልካይ ነገሮች ሊኖሩ ስለሚችሉ ነው።»

***** ***** ***** *****

መስአላውን ወደ ኢብኑ ተይሚያ ማስጠጋታቸው ትክክል አለመሆኑን ወደፊት ኢንሻአላህ ራሱን በቻለ ርዕስ እንመለስበታለን፤ ለጊዜው እንደ ጥቅል በሺርክ ጉዳዮች ዑዝር ቢል ጀህል የለም ለማለት መስአላ ዚሂራንና ኽፊያን በመለያየት ላይ መደገፋቸው ትክክል አለመሆኑን ከማየታችን በፊት፤ ሸይኽል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ ዘንድ ሰውን ለማከፈር ወሳኙ ነገር ሰውየው የወደቀበት ሺርክ መስአላ ዚሂራ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ሳይሆን፤ ሰውየው ሑጃው ደርሶታል ወይም አልደረሰውም የሚለው ጉዳይ እንደሆነና፤ እሱ ዘንድ የማከፈሪያ መወጠኛውና ማሰሪያው ይህ መሆኑን እንመለከታለን። ለዚህ ደግሞ የሸይኹን አቋም የሚገልፁ በርካታ ንግግሮች ቢኖሩም ወደ ፊት ሰፋ ባለ ሁኔታ እስከምናያቸው ድረስ ለጊዜው በጉዳዩ ግልፅ ሆኖ የመጣውን አሻሚ ያልሆነውን አንዱን ፈትዋውን ብቻ ላስነብባችሁ።

እንደሚታወቀው ከአላህ ውጪ እሱ እንጂ ማንም በማይችለው ጉዳይ በሙታኖችም ሆነ ህያው በሆኑ አካሎች ኢስቲጃዛ ማድረግ ከኢስላም የሚያስወጣ መስአላ ዚሂራ የሆነና ትልቅ የሆነ ሺርክ ነው፤ ከመሆኑም ጋር ሰዎች ሑጃ ሳይደርሳቸው ባለማወቅ ይህ አይነት ሺርክ ውስጥ የሚወድቁ ከሆነ እንደማይከፈሩና ሑጃ ከደረሳቸው በኋላ ግን እንደሚከፈሩ የተናገረበት ሁኔታ አለ።

ሸይኽል ኢስላም ተጠየቀ:

سئل شيخ الإسلام بن تيمية رحمه الله : ما تقول السادة العلماء أئمة الدين ـ رضي الله عنهم أجمعين ـ في قومٍ يعظِّمون المشايخ بكون أنهم يستغيثون بهم في الشدائد ويتضرعون إليهم ويزورون قبورهم ويقبلونها وتبركون بترابها ...

فأجاب ابن تيمية :الحمد لله رب العالمين من استغاث بميت أو غائب من البشر بحيث يدعوه في الشدائد والكربات ويطلب منه قضاء الحوائج فيقول: يا سيدي الشيخ فلان أنا في حسبك وجوارك أو يقول عند هجوم العدو: يا سيدي فلان يستوحيه ويستغيث به أو يقول ذلك عند مرضه وفقره وغير ذلك من حاجاته: فإن هذا ضال جاهل مشرك عاص لله تعالى باتفاق المسلمين فإنهم متفقون على أن الميت لا يدعى ولا يطلب منه شيء سواء كان نبيا أو شيخا أو غير ذلك ..وهذا الشرك إذا قامت على الإنسان الحجة فيه ولم ينته وجب قتله كقتل أمثاله من المشركين ولم يدفن في مقابر المسلمين ولم يصلَّ عليه وأما إذا كان جاهلا لم يبلغه العلم ولم يعرف حقيقة الشرك الذي قاتل عليه النبي صلى الله عليه وسلم المشركين فإنه لا يُحكم بكفره ولا سيما وقد كثر هذا الشرك في المنتسبين إلى الإسلام ومن اعتقد مثل هذا قربة وطاعة فإنه ضال باتفاق المسلمين وهو بعد قيام الحجة كافر

جامع المسائل

(3/145 – 151)

«መሻዩኾችን ስለሚያልቁ፣ በመከራዎች ጊዜ በእነሱ ኢስቲጃዛ ስለሚያደርጉ፣ ለእነሱም የሚዋደቁ፣ መቃብሮቻቸውንም የሚዘይሩና የሚስሙ፤ ከአፈሩም በረካ የሚፈልጉ ስለሆኑ ሰዎች የዲኑ መሪዎች ዑለማኦቻችንና አለቆቻችን ምን ኢይነት ብይን ይሰጣሉ» በሚል ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ ተጠየቀ !!

ኢብኑ ተይሚያም እንዲህ በማለት መልስ ሰጠ:

«ምስጋና ለአላህ የተገባ ነው፤ በሞተ ወይም ህያው ሆኖ ነገር ግን ሩቅ ስፍራ ባለ ሰው ኢስቲጃዛ የሚያደርግ፤ ማለትም በመከራዎችና አስጨናቂ በሆኑ ከስተቶች ሐጃዎቹን እንዲፈፅምለት: "ያ ሰይዱዲ ሸህ እገሌ ሆይ! እኔ በአንተ ጥበቃና መብቃት ውስጥ ነኝ" በማለት የሚለምን ሰው፤ ወይም ጠላት ሊያጠቃው ሲከብበው፣ ወይም ህመም ሲደርስበት፣ ወይም ደግሞ ድህነት ሲያገኘው "ያ ሰይዱዲ ፉላን ... " እያለ ኢስቲጃዛ የሚያደርግ ይህ አይነቱ ሰው በሙስሊሞች

ስምምነት፡- ዱል፣ጂሂል፣ሙሽሪክና አላህን ያመፀ ነው። ምክንያቱም የሞተ ሰው ነቢይም ሆነ ሸይኽ ወይም ሌላ የሆነ ይሁን እንደማይለመንና ከእሱም ምንም አይነት ሓጃ እንደማይፈለግ ሙስሊሞች ስምምነት አላቸው። ይህ አይነቱን ሺርክ የፈፀመ ሰው ሑጃ ከቆመበትና መረጃ ደርሶት ካለበት ተግባር ካልታቀበ የእሱ አምሳያ ሙሽሪኮች እንደሚገደሉት እሱንም መግደል ግድ ነው፤ ሙስሊሞች መቃብር አይቀበርም፤ አይሰገድበትምም። ነገር ግን እውቀት ያልደረሰው ጂሂል የሆነ ሰው ከሆነና ነቢዩ ﷺ ሙሽሪኮችን የተጋደሉበትን ሺርክ ሐቂቃውን የማያውቅ ከሆነ፤ ይህ አይነቱ ሰው ካፊር ተብሎ አይተሓከምበትም!! በተለይ ይህ አይነቱ ሺርክ ራሳቸውን ወደ ኢስላም የሚያስጠጉ የሆኑ ሰዎች ውስጥ በብዛት እየተከሰተ ባለበት ወቅት (ካፊር ሙሽሪክ እያሉ ከኢስላም የሚወጣበት በሆነ ብይን አይበየንበትም)። ይህ አይነቱን የሺርክ ተግባር ኸይር ስራና ወደ አላህ መቃረቢያ አድርጎ ኢፅቲቃድ የሚያደርግ ወይም የሚያምን ሰው በሙስሊሞች ስምምነት፡- ዱል ነው፤ ሑጃ ከደረሰውም በኋላ ካፊር ይደረጋል!!» (ጀሚዑል መሳኢል:3/145 _ 151)

ስለ ሸይኽል ኢስላም ለመቆያ ያህል ይህን ካየን ወደዚያኞቹ እንመለስ።

ከላይ እንዳሳለፍነው እነዚያ አካላት በሺርክ ጉዳዮች ዑዝር ቢል ጀህል የለም ለማለት መስአላ ያሂራንና ኸፊያን በመለያየት ላይ መደገፋቸው ትክክል አይደለም፤ ስህተት ነው። የስህተቱ መንስኤም፡- ወደ መስአላዋ በሚመለሰው ነገር መካከልና አቅማዳም የደረሰ ሰው በመስአላዋ ላይ ሊኖረው ወደሚችለው የእውቀት መጠን መካከል አለመለየታቸው ነው።

እርግጥ ነው ሸሪዓዊ ጉዳዮች በቀድር፣ በደረጃ፣ ይበልጥ በመታወቅና ባለመታወቅ አንድ አይነት መጠን የላቸውም። ይልቁንም ከፊሉ ከከፊሉ ከፍ ያለ አለ፤ ከፊሉ ደግሞ ከከፊሉ ይበልጥ የሚታወቅና በሙስሊሞች መሀል ተሰራጭቶ የሚገኝ ከመሆኑ የተነሳ ከኢስላማዊ ጉዳዮች መሆኑ አብዛኞች ዘንድ በግልፅ የሚታወቅ የሆነ አለ። ነገር ግን ሁሉም ሙስሊሞች ስለነዚህ ጉዳዮች ትክክለኛ ምንነትና ስለ ብይናቸው እኩል የእውቀት ደረጃና ተመሳሳይ የማስታወስ ብቃት ያላቸው መሆኑን አያስይዝም። በአላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ ዲን ውስጥ ያለች አንዲት ሂጂራ የሆነች መስአላ በአንዳንድ ሙስሊሞች ላይ ሑከሚ ሊደበቅባቸው ይችላል። ምክንያቱ ደግሞ የሰዎች ግንዛቤ ከነገሮች ጋር ወዳለው ትስስራዊ ባህሪ ይመለሳል።

የግንዛቤ መገለጫዎች፡- እንደ እውቀት፣ መሀይምነት፣ እርግጠኝነት፣ ግምት፣ አእምሮ በቀላሉ የሚረዳው፣ የማይረዳው፣ ግልፅ መሆን፣ ድብቅ መሆንና

የመሳሰሉት መገላጫዎች፡- አጠቃላይ ነገሮች ወይም መሳሊሎች ላይ የቆሙና እላያቸው ላይ ተጣብቀው የሚገኙ ባህሪያት አይደሉም፤ እንዲሁም ከነገሮቹ የማይነጠሉና የማይለዩ የሆኑም አይደሉም፤ ይልቁንም ስለ ነገሮች ምንነት ተገንዛቢ በሆኑ ነፍሶች ውስጥ የቆሙና የሚገኙ ባህሪያት ናቸው። ማለትም በሰው ልጆች ላይ የሚገኙ እንጂ መስአላዋ ላይ ተለጥፈው ያሉ ወይም ወደሷ የሚመለሱ አይደሉም። ሰዎች ደግሞ በእውቀቶቻቸውና በግንዛቤዎቻቸው የሚለያዩና የሚበላለጡ መሆናቸው የማያጠራጥር እውነታ ነው። ለዚህም ነው እነኚህ ባህሪያት ሰዎች በብዛት ከሚለያዩባቸው አንፃራዊ ከሆኑ ነገሮች የሆኑት።

ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ "አር ረዱ ዐለል መንጢቂዩን: 13_14) ላይ ይህን ሀሳብ ሲያብራራ እንዲህ ይላል፡-

كَونُ العلمِ بَديهيًّا أو نظريًّا هو مِن الأُمُور النِّسْبِيّة الإضافية مثل كون القضيَّة يَقِينيَّة أو ظَنِّيَّة؛ إذ قد يَتيقَّنُ زيدٌ ما يظنُّه عمرٌو، وقد يبده زيدا من المعاني ما لا يعرفه غيره إلا بالنظر، وقد يكون حِسِّيًّا لزيدٍ من العلوم ما هو خبريٌّ عند عمرو

وإن كان كثير من الناس يحسب أنَّ كونَ العلم المعيَّن ضروريًّا أو كسبيًّا أو بديهيًّا أو نظريًّا هو من الأمور اللَّازمة له بحيث يشترك في ذلك جميعُ الناس وهذا غلطٌ عظيمٌ وهو مخالف للواقع

فان من رأى الأمور الموجودة في مكانه وزمانه كانت عنده من الحِسِّيَّات المُشاهَدات، وهي عند مَن عَلِمَها بالتواتر من المتواترات، وقد يكون بعضُ الناس إنما عَلِمَها بخبرٍ ظنِّيٍّ فتكون عنده من باب الظنِّيات؛ فان لم يسمعها فهي عنده من المجهولات، وكذلك العقليات، فان الناس يتفاوتون في الإدراك تفاوُتًا لا يكادُ يَنضبِطُ طَرَفَاه، ولِبَعضِهم مِن العلم البَديهي عنده والضروري ما يَنفِيه غيرُه أو يشكُّ فيه، وهذا بَيِّنٌ في التصورات والتصديقات

(الرد على المنطقيّين :13_ 14)

«አንድ የሆነ ነገር እንዲሁ "በዲይሂዮን" በቀላሉ መታወቁ ወይም "ነዞሪዮን" ማለትም በቲዮሪቲካል ስለ ጉዳዩ ግራ ቀኙን ተመልክተን ወይም ሌሎች ነገሮችን ካገላበጥን በኋላ የሚታወቅ መሆኑ፤ ይህ "ኒስቢይ" ወይም አንፃራዊ ከሆኑ ጉዳዮች ነው። ለምሳሌ ጉዳዩ የተረጋገጠ ወይም ወደ እርግጠኝነት ያደፋ ግምታዊ የሆነ ሊሆን ይችላል፤ ምክንያቱም ዘይድ (የተባለ ሰው) እርግጠኛ የሆነበትን ጉዳይ፤ ዐምር እርግጠኛ ላይሆንበት ይችላል፤ ሌሎች ሰዎች ነገሮችን አገላብጠውና ተመልክተው እንጂ የማያውቁትን ሀሳብ ዘይድ እንዲሁ በቀላሉ ሊያውቀው

ይችላል። ዘይድ ዘንድ በተጨባጭ የሚታወቀው ነገር ዐምር ዘንድ ላይታወቅ ይችላል። በግልፅ የሚታወቀውም ይሁን፤ ተፈልጎ የሚገኘው፤ በቀላሉ የሚገነዘቡትም ይሁን፤ ነገሮችን ተመልከተው የሚገነዘቡት አንድ የሆነ የተወሰነ እውቀት፡- ሁሉም ሰው በተመሳሳይ የግንዛቤ ደረጃ የሚጋራቸውና ከሰዎቹም የማይነጠሉ እንደውም ሰዎቹ ጋር ተጣብቀው የሚገኙ አድርገው ብዙዎቹ ሰዎች ይህን መገመታቸው፡- ይህ ከባድ የሆነ ስህተት ከመሆኑም በላይ ከነባራዊው እውነታ ጋር የሚቃረን ነገር ነው። ባለበት ቦታና ጊዜ የሚገኙ ነገሮችን በአይኑ የተመለከተ ሰው፤ እነኚህ ነገሮች እሱ ዘንድ በተጨባጭ ያገኛቸውና የሚያውቃቸው ይሆናሉ፤ እነኚህን ነገሮች ከተመለከቱ ከሙተዋቲሮች ወይም ከበርካታ የመረጃ ምንጮች በመነሳት ያወቃቸው ሰው ዘንድ ደግሞ ከሙተዋቲራት ይሆናሉ፤ ማለትም ከማይጠራጠርባቸው በርካታ ምንጮች የተገኙ እውቀቶች ተደርገው ይታሰባሉ፤ አንዳንዱ ሰው ደግሞ ነገሮቹን እርግጠኛ ባልሆነበት መንገድ ብቻ አውቋቸው፤ እሱ ዘንድ ከዘንኒያት ወይም እርግጠኛ ካልሆነባቸው እውቀቶቹ ተደርገው ይቆጠራሉ፤ ስለ ነገሮቹ ያልሰማ (እና መረጃው ያልደረሰው) ሰው ደግሞ ፡- እሱ ዘንድ ከመጅሁላት ወይም ከማያውቃቸው ጉዳዮች ይሆናሉ ማለት ነው። በአእምሯዊ እውቀቶችም ያለው ሂደት እንደዚሁ ነው። ምክንያቱም ሁለቱ ወገኖች ለመጣጣም በማይቀርቡበት መልኩ በአገነዛዘባቸውና በአመለካከታቸው ከፍተኛ የሆነ መለያየትን ይለያያሉ። ከፊሉ ሰው ዘንድ በቀላሉ የሚታወቅና በጣም ግልፅ የሆነ ጉዳይ ተደርጎ የሚታየው ነገር፤ ሌላው ሰው ዘንድ የሚያወግዘው ወይም የሚጠራጠርበት ጉዳይ ሆኖ ሊገኝ ይችላል። ይህ በተሶውራቶችና በተስዲይቃት ጉዳዮች ላይ በግልፅ የሚታይ ነገር ነው»

የዚህ መሰረታዊ ጉዳይ ጥቅል ሀሳብ እንደሚከተለው ይገለፃል፡-

•የተወሰኑ ማህበረሰቦች ዘንድ፣ ወይም የሆኑ አካባቢዎች ወይም ዘመናቶች ላይ አንድ የሆነ ነገር ያሂር የሆነ ጉዳይ መሆኑ፡- ሁሉም ሰዎች ዘንድ እንዲሁም ሁሉም ቦታዎችና ዘመናቶች ላይ ግልፅ መሆኑን አያስይዝም።

•የሶላት ዋጅብነት በሆነ ቦታ፣ በተወሰነ ዘመንና የተወሰኑ ጀማዓዎች ዘንድ በግልፅ የሚታወቅ ጉዳይ መሆኑ፡- ሁሉም ቦታዎችና ዘመናት ውስጥ እንዲሁም እያንዳንዱ በኢስላም ጥላ ስር የሚገኝ አካል ዘንድ ግልፅ የሆነ ነገር መሆኑን አያስፈርድም።

•በሞቱ ሰዎችና በመቃብሮች እስቲጃሣ ማድረግ ሐራምነቱና ሺርክነቱ የተወሰኑ ጀማዓዎች በማይጠራጠሩበት መልኩ እነሱ ዘንድ ግልፅ መሆኑ፡- የዚህ ፀያፍ

ተግባር ሑክም ሁሉም ሰዎች ዘንድ፣ በሁሉም ቦታዎችና ዘመናት ግልፅ መሆኑን አያስይዝም። ይህን በተመለከተ ኢብኑ ተይሚያ ዐለይሂ ረሕመቱላህ (መጅሙዑል ፈታዋ: 23/347፣ 19/211) ላይ እንዲህ ይላል፦

وكونُ المسألةِ قطعيَّة أو ظنيَّة هو مِن الأمور الإضافية، وقد تكون المسألة عند رجلٍ قطعيةً لِظُهور الدليل القاطع له، كمن سمع النصَّ من الرسول، وتيقَّن مُرادَه منه، وعند رجلٍ لا تكون ظنية، فضلاً عن أن تكون قطعية؛ لِعَدَمِ بُلوغِ النصِّ إيَّاه، أو لِعدَمِ ثُبُوتِه عنده، أو لِعَدَمِ تَمَكُّنِهِ من العلم بدلالته

(مجموع الفتاوى

: (23/347) (19/211)

«አንዲት የሆነች መስአላህ "ቀጥዒያ" (እርግጠኛና ቆራጭ የሆነች መሆኗ) ወይም "ዞንኒያ" (ወደ እርግጠኝነት አመዛኝ የሆነ ግምት) መሆና ይህ አንፃራዊ ከሆኑ ጉዳዮች ነው። አንድ ሰው ቆራጭ የሆነ መረጃ ስለተገለፀለት መስአላዋ እሱ ዘንድ "ቀጥዒይያ" ልትሆንለት ትችላለች፤ ለምሳሌ ሰውየው ከመልእክተኛው ﷺ መረጃን ሰምቶና በመረጃው የተፈለገበትን ሀሳብ በደንብ በመገንዘቡ ምክንያት (መስአላዋ እሱ ዘንድ የተረጋገጠች ልትሆን ትችላለች)፤ ሌላው ሰው ደግሞ መረጃው ስላልደረሰው፤ ወይም የሠዐተ (የፀደቀ) አድርጎ ስለማያየው፤ አሊያም ደግሞ የጉዳዩን ሀሳብ በመረጃ ለመገንዘብ የማይችል በመሆኑ ምክንያት ይህ ሰውየ ዘንድ መስአላዋ "ቀጥዒያ" መሆና ይቅርና "ዞንኒያም" ላትሆን ትችላለች።»

ይህን መሰረሰታዊ ጉዳይ ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ በተከፊርም ሆነ በሌሎች መስአላዎች ላይ በርካታ ንግግሮቹን ለመገንባት ተጠቅሞበታል። በዚህ ዙሪያ ከተናገራቸው በርካታ ንግግሮች አሳሳቢ የሆነው ንግግሩ ላይ እንዲህ ይላል፦

وقد يُنْكِر أحدُ القائلين على القائلِ الآخر قولَه إنكارًا يجعلهُ كافرًا أو مبتدعًا فاسقًا يستحق الهجرَ وإن لم يستحق ذلك

وهو ـ أيضا ـ اجتهاد

وقد يكون ذلك التغليظ صحيحا في بعض الأشخاص أو بعض الأحوال لظهور السنة التي يكفر من خالفها؛ ولِما في القول الآخر من المفسدة الذي يبدع قائله؛ فهذه

أمور ينبغي أن يعرفها العاقل؛ فإن القول الصدق إذا قيل :فإن صفته الثبوتية اللازمة أن يكون مطابقا للمخبر

أما كونه عند المستمع معلوما، أو مظنونا، أو مجهولا، أو قطعيا، أو ظنيا، أو يَجِب قبوله أو يحرم، أو يكفر جاحده، أو لا يكفر :فهذه أحكام عملية تختلف باختلاف الأشخاص والأحوال

فإذا رأيت إماما قد غَلَّظَ على قائلٍ مقالته أو كفَّرهُ فيها :فلا يعتبر هذا حُكْمًا عاما في كل من قالها، إلا إذا حصل فيه الشرطُ الذي يستحق به التغليظ عليه، والتكفير له ؛ فإن من جحد شيئا من الشرائع الظاهرة، وكان حديثَ العهدِ بالإسلام، أو ناشئا ببلد جهلٍ :لا يكفر حتى تبلغه الحجة النبوية

وكذلك العكس؛ إذا رأيت المقالة المخطئة قد صدرت من إمام قديم :فاغتُفِرَت ؛ لعدم بُلوغ الحجة له ؛ فلا يغتفر لمن بَلَغَتْهُ الحجة ما اغْتُفِر للأول

(مجموع الفتاوى :6/61)

«ከተናጋሪዎች አንድ የሆነ ተናጋሪ ሌላን ሰው በንግግሩ ምክንያት ካፊር እስከማድረግ በሚያበቃው መልኩ ንግግሩን ይቃወመው ይሆናል። ወይም ደግሞ ለሀጅር ተገቢ የሆነ ሰው ባይሆንም፤ ሀጅር ሊደረግ የሚገባ ሙብተዲዕ ፋሲቅ ያደርገዋል። ይህም ኢጅቲሃድ ነው፤ ተቃራኒዋ የሚከፈርባት የሆነችዋ ሱንና ግልፅ በመሆኗ (ወይም መረጃዋ ለሰዎቹ በመገለፅ) ምክንያትና ተናጋሪው ንግግር ውስጥ ሙብተዲዕ እንዲሆን የሚያስችለው ጥፋት በመኖሩ፡- ይህ ከባድ የሆነ ብይን ለአንዳንድ ሰዎችና በአንዳንድ ሁኔታዎች (ቢሰየን) ትክክል ሊሆን ይችላል። እነዚህን ነገሮች አስተዋይ የሆነ ሰው ሊያውቃቸው የሚገቡ ነገሮች ናቸው። ምክንያቱም አንድ ንግግር እውነተኛ የሚባለው፡- የማትነጠለውና ሁሌ እሱጋ የምትገኘዋ ባህሪው ስለሱ ከሚነገርለት ነገር ወይም ዋቂዑ ጋር ተስማሚ የሆነው ነውና። አድማጩ ዘንድ የሚታወቅ ወይም የሚጠራጠርበት ወይም የማይታወቅ መሆኑ፤ ወይም ደግሞ ቀጥሚይ ወይም ዘንኒይ መሆኑ፤ ሊቀሰሉት ግድ የሆነ ወይም መቀበሉ ሐራም የሆነ መሆኑ፤ ተቃዋሚው የሚከፈርበት ወይም የማይከፈርበት መሆኑ፡- እነዚህ ነገሮች ሁሉ እንደ ሰዎቹና ሁኔታዎች መለያየት የሚለያዩ ተግባራዊ የሆኑ አሕካሞች ወይም ብይኖች ናቸው። ስለዚህ አንድን ኢማም በአንድ ተናጋሪ ላይ (በተዕዩን ነጥሎ) ከበድ ያለ ሑክም ሲሰጥ ወይም ሲያከፍረው ብትመለከት፤ ይህ የኢማሙ ሑክም: ከበድ ያለ ሑክም ሊሰጠውና ሊከፈር ተገቢ የሚያደርገው መስፈርት ካልተገኘበት በስተቀር :- ያን አይነት

ንግግር የተናገረን ሰው ሁሉ የሚያካትትና የሚጠቀልል ተደርጎ አይቆጠርም። ምክንያቱም የእስልምና ጊዜው ቅርብ የሆነ ወይም ጅህልና የተንሰራፋበት ሀገር ያደገ ሆኖ ግልፅ የሆኑ ሸሪዓዊ ጉዳዮችን የሚቃወም ሰው ነቢያዊ ማስረጃዎች እስካልደረሱት ድረስ አይከፈርምና። በዚህ ተቃራኒም እንዲሁ ነው፡- ጥፋተኛ የምታስደርገው ንግግር ከአንድ ቀደም ካለ ኢማም ተገኝታ ብትመለከት፤ መረጃ ስላልደረሰው ምህረት ይደረግለታል፤ መረጃ የደረሰው አካል ግን የመጀመሪያው ያገኘውን ምህረት እሱ ሊያገኝ አይችልም።»

ይህ የኢብኑ ተይሚያ ንግግር "ኒስቢያ" ወይም አንፃራዊነት እውቀትንና መሰል መገለጫዎቹን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን ከመግለፁ አኳያና ሑክም ለመስጠት ወሳኝ የሆነውን የሑክምን ትክክለኛ መወሰኛ ወይም ማሰሪያ ቦታውን ከመግለፁ አንፃር ሙሂም የሆነ የሸይኹ ንግግር ነው።

فكلُّ من بلغتْهُ الحجةُ البلوغَ المُعْتَبَر فإن حكم الفعل ينطبق عليه ولو كان حديثَ عهدٍ بكفرٍ وكل من لم تبلغه الحجة ـ التي يرتفع بها وصفُ الجهالة ـ فإن حكم الفعل لا ينطبق عليه ولو كان يعيش في بلاد المسلمين

«ስለዚህ ማንኛውም ሰው ማስረጃ ተገቢ የሆነ መድረስን ከደረሰው ከኩፍር ወደ ኢስላም የተመለሰበት ጊዜው ቅርብ ቢሆንም የስራው ብይን እላዩ ላይ መሰየኑ ተስማሚነት ይኖረዋል፤ ከላዩ ላይ መሀይምነቱን የምታነሳለት ሑጃ ያልደረሰችው ሰው ሙስሊሞች ሀገር ቢኖርም እሱ ላይ የስራው ብይን ቢሰየን ተስማሚነት አይኖረውም።» (አል ዑመይሪ)

• ይህ መርህ ኢብኑ ተይሚያ ሙኻሊፎች ጋር ተዓሙል ለማድረግ እንዲሁም የፈላሲፋዎችንና የሚልመል ከላም ሰዎች ንግግሮችን ለማፈራረስ የሚያገፍበት ጠንካራ የሆነ መሰረት ነው። ከዚህም የተነሳ ብዙ ቦታዎች ላይ በተደጋጋሚ ሲያወሳው ይታያል። ከዲናዊ ጉዳይ መሆናቸው በግልፅ የሚታወቁ ነገሮች እንደየሰዎቹ ሁኔታ ግልፅነታቸው ሊለያዩ የሚችሉ አንፃራዊ ጉዳዮች መሆናቸውንም ብዙ ጊዜ ደጋግሞ ይናገራል። ለምሳሌ ያህል እንዲህ ይላል፡-

فكونُ الشيء معلومًا من الدين ضرورةً أمرٌ إضافيٌّ ، فحديث العهد بالإسلام ، ومن نشأ ببادية بعيدة: قد لا يعلم هذا بالكلية ، فضلا عن كونه يعلمه بالضرورة .وكثير من العلماء يعلم بالضرورة أن النبي صلى الله عليه وسلم سجد للسهو ، وقضى بالدية على العاقلة ، وقضى أن الولد للفراش ، وغير ذلك مما يعلمه الخاصة بالضرورة ، وأكثر الناس لا يعلمه ألبتة

(مجموع الفتاوى :13/118)

«አንድ ነገር በግልፅ የሚታወቅ ዲናዊ ጉዳይ መሆኑ፤ ይህ አንፃራዊ ነገር ነው። ምክንያቱም አዲስ ሰለምቴ ወይም (ከዒልምና ከዐለማእ) ራቅ ያለ መንደር ያደገ ሰው ጉዳዩን በግልፅ ሊያውቀው ይቅርና ጭራሽ ሙሉ በሙሉ ላያውቀው ሁሉ ይችላልና። ነቢዩ ﷺ የእርሳና ሱጁድ መስገዳቸውን፣ የገዳይ አባት ወገኖች የሟችን ካሳ እንዲከፍሉ መወሰናቸውን፣ የዝሙት ልጅ ልጅነቱ በዝሙት ለወለደው ወላጁ ሳይሆን ዝሙተኛዋ ሴት ባለትዳር ከሆነች ለባሏ፤ ባሪያ ከሆነች ደግሞ የአሳዳሪዋ መሆኑን መወሰናቸውንና አዋቂዎች በግልፅ የሚያውቋቸው የመሳሰሉትን ነገሮች ብዙዎቹ ዑለማኦች ቢያውቋቸውም አብዛኛዎቹ ሰዎች ግን ፈፅሞ አያውቋቸውም።» (መጅሙዑል ፈታዋ: 13/118)

ኢብኑ ተይሚያ ረሕመቱላሂ ዐለይህ እዚህ መሰረት ላይ መደገፈያውን በግልፅ አብራርቷል፤ እሱም የግንዛቤ መገለጫዎች፡- እንደ እውቀት፣ መሀይምነት፣ እርግጠኝነት፣ ወደ እርግጠኝነት አመዛኝ የሆነ ግምት፣ ግልፅ መሆንና ድብቅ መሆን የሚባሉ መገላጫዎች፡- አጠቃላይ ነገሮች ላይ የቆሙና እላያቸው ላይ የሚገኙ ባህሪያት አለመሆናቸውን፤ እንዲሁም ከነገሮቹ የማይነጠሉና የማይለዩ እንዳልሆኑም ገልፆል፤ ይልቁንም ስለ ነገሮች ምንነት ተገንዛቢ በሆኑ ነፍሶች ውስጥ የቆሙና የሚገኙ ባህሪያት ናቸው፤ አንድ ነገር ዐምር የተባለ ግለሰብ ዘንድ የተረጋገጠና በግልፅ የሚታወቅ ጉዳይ ሊሆን ይችላል፤ እንዲህ አድርጎ እንዲገነዘብ የሚያስችሉት አስባቦች በመገኘታቸው ምክንያት ማለት ነው። ነገር ግን ዘይድ የተባለ ሰው ዘንድ ጉዳዩ "መዝኑን" አጠራጣሪ ወይም ለእርግጠኝነት ቀረብ ያለ ግምታዊ ጉዳይ ሊሆን ይችላል፤ እሱም እንዲህ አድርጎ እንዲገነዘብ የሚያስችሉት አስባቦች በመገኘታቸው ምክንያት ነው። (የኢብኑ ተይሚያን መጅሙዑል ፈታዋ: 19/211) ላይ ተመልከት።

እስካሁን ከተጠቀሰው በመነሳት ሀሳቡ ጠቅለል ሲል:

•አንዲት መስአላ ከፊል ሰዎች ዘንድ ሂሂራ መሆኗ ከእነሱ ሌላ ያለ እያንዳንዱ ሰው ሁሉ ዘንድ ሂሂራ መሆኗን አያስይዝም፤ ይህ ሲባል "የሆነች መስአላ ፡- ሂሂራ ናት፤ ወይም ሙተዋቲራ ናት ብሎ መሐከም አይቻልም" ማለት አይደለም፤ ነገር ግን መስአላዋን ሂሂራ ናት ብለን ከሐከምን በኋላ፤ ይህ ሑክም ሁሉም ሰው ዘንድ የፀና እና ሁሉም ሰው ዘንድ የሚገኝ አድርገን ማመናችን ትክክል አይደለም። ይልቁንም ከእውቀት ማግኛ ስፍራ በመራቃቸው አሊያም ደግሞ ትክክለኛ ባልሆነ

ተእዊልና በመሳሰሉት ምክንያቶች ይህ ባህሪ ከነሱ እንዲወገድ ግድ የሚያደርጉ የተለያዩ የሰዎች ሁኔታዎች ግምት ውስጥ መግባታቸው ግድ ይላል።

መስአላ ዚሂራና ኸፊያን በመለያየት ዑዝር ቢል ጀህል የለም ለማለት እንደ መደገፊያ መጠቀምን ስህተት መሆኑን ከገለፁ ዑለማኦች መካከል ሸይኽ ሙሐመድ ኢብን ሷሊሕ አል ዑሠይሚን አንዱ ናቸው።

እሳቸውም (ሊቃኣቱል ባቢል መፍቱሕ: (48) (3/45) የተሰኘው ኪታባቸው ላይ እንዲህ ይላሉ:

تجب إقامة الحجة قبل التكفير، وذلك في كل المسائل التي يمكن أن يجهلها الناس، فلا نقسِّم المسائل إلى مسائل ظاهرة ومسائل خفية؛ لأن الظهور والخفاء أمرٌ نِسبيٌّ، قد تكون المسألة ظاهرة عندي وخفية عند غيري، فلا بد إذًا من إقامة الحجة وعدم التسرع في التكفير؛ لأن إخراج رجل من ملة الإسلام ليس بالأمر الهين

(لقاءات الباب المفتوح)

وانظر، (3/45)، (48):

(الشرح الممتع: 2/25)

«ሰውን ከማከፈር በፊት ሑጃን ማቆም ግድ ነው። ይህም ሰዎች ላያውቁት በሚችሉት ነገር ሁሉ ነው። መሳኢል ዚሂራ (እነሱ እንደሚሉት: ለማከፈር ሑጃ ማቆም መስፈርት የማይሆንበት) እና መሳኢል ኸፊያ (ለማከፈር ሑጃ ማቆም መስፈርት የሚሆንበት) በማለት አንከፋፍልም። ምክንያቱም ግልፅነትና ድብቅነት "ኒስቢይ" ወይም አንፃራዊ ነገር ነውና፤ መስአላዋ እኔ ዘንድ ግልፅ ሆና ከእኔ ሌላ ያለ ሰው ዘንድ ግን ድብቅ ልትሆን ትችላለች። ስለዚህ ሑጃን ማቆምና ለማከፈርም አለመቸኮል አይቀሬ የሆነ ጉዳይ ነው። ምክንያቱም አንድን ሰው ከኢስላም ማስወጣት ቀላል ነገር አይደለምና።»

ወደኋላ መለስ ብሎ ኢስላማዊ ዘመናትን የሚቃኝ ሰው የዚህን መሰረት እውነታ ማለትም ግልፅ መሆንና ድብቅ መሆን አንፃራዊ መሆናቸውን ይገነዘባል።

የኢብኑ ተይሚያ ዘመን ደርሶ አላህ ይህን በሕር የሆነ ዓሊምና መሰል ዑለማኦችን ለዚች ኡማ እስኪያመጣላት ድረስ የአህሉስ ሱናዎች መዝሀብ ጥቂት ሰዎች እንጂ

የማያውቁት ድብቅ ነገር ሆኖና ለሐቅ ተቃራኒ የሆኑ መዛሂቦች ደግሞ ግልፅና ታዋቂ ሆነው የቆዩባቸው በርካታ ዘመናት በዚህች ኡምማ ላይ አልፈውባታል።

እነኚህ ዑለማኦች ሲመጡ ግን አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ የአህሉሱናዎችን መዝሀብ በዑለሞቹ ሰበብ ዳግም እንዲያብብና እንዲሰራጭ አደረገው። እንዲሁም የሺርክ ጉዳዮችና ኢስቲጃሣ ቢኻይራላህ በገሃድ ተንሰራፍቶ፤ የተውሒድና ዒባዳን ለአላህ ብቻ ጥርት አድርጎ የማዋል ጉዳይ በጣም የተደበቀበት ዘመናትም በኡማዋ ላይ አልፈዋል።

ሸይኽ ሙሐመድ ኢብን ዐብዲል ወሃብና የተባረከች ደዕዋውን አራማጅ የሆኑት ተከታዮቹ መጥተው፤ ለሰዎች የሺርክና የተውሒድ ጉዳዮችን አብራርተው መግለፅን የተያያዙት ጊዜ ግን የተውሒድ መንሰራፋትና ይፋ መሆን ዳግም ሊያብብና ግልፅ ሊሆን ቻለ። ሸይኹ ራሱ በሱ ዘመንና ከእሱ ቀደም ብሎ በነበረው ዘመን የተውሒድ እንግድነትና ድብቅነት እንዲሁም የሺርክ መንሰራፋት ምን ያህል አሳስቦት ስሞታ ያቀርብ እንደነበር የታሪክ መዛግብቶች ይዘውት ያለ እውነታ ነው።

ይህ ሁሉ የታሪክ ክስተት:

• አንዲት የሆነች መስአላ በሆነ ዘመን ዚሂራ ሆና መቆየቷ፤ በሁሉም ዘመናትም ዚሂራ መሆኗን እንደማያስፈርድ ያረጋግጥልናል።

• አንዲት ጀማዓ ዘንድ ግልፅ መሆኗም ሁሉም ጀማዓዎች ዘንድ ግልፅ የሆነች መስአላ መሆኗን አያስይዝም።

• እንዲሁም የሆነ አካባቢ ላይ ቀጥዒያ መሆኗ በሁሉም ቦታዎችና አካባቢዎች ቀጥዒያ መሆኗን አያስፈርድም ማለት ነው።

ግልፅነትና ድብቅነት አንፃራዊ መሆኑን ከሚጠቁሙ መረጃዎች መካከል አንዱ ቀጣዩ የሰሓቢዩ ሑዘይፋ ሐዲሥ ነው።

عَنْ حُذَيْفَةَ بْنِ الْيَمَانِ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «يَدْرُسُ الْإِسْلَامُ كَمَا يَدْرُسُ وَشْيُ الثَّوْبِ، حَتَّى لَا يُدْرَى مَا صِيَامٌ، وَلَا صَلَاةٌ، وَلَا نُسُكٌ، وَلَا صَدَقَةٌ، وَلَيُسْرَى عَلَى كِتَابِ اللهِ عَزَّ وَجَلَّ فِي لَيْلَةٍ فَلَا يَبْقَى فِي الْأَرْضِ مِنْهُ آيَةٌ، وَتَبْقَى طَوَائِفُ مِنَ النَّاسِ ؛ الشَّيْخُ الْكَبِيرُ وَالْعَجُوزُ يَقُولُونَ: أَدْرَكْنَا آبَاءَنَا عَلَى هَذِهِ الْكَلِمَةِ: لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ، فَنَحْنُ نَقُولُهَا»، فَقَالَ لَهُ صِلَةُ: مَا تُغْنِي عَنْهُمْ: لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ، وَهُمْ لَا يَدْرُونَ مَا صَلَاةٌ، وَلَا صِيَامٌ، وَلَا نُسُكٌ، وَلَا صَدَقَةٌ ؟

فَأَعْرَضَ عَنْهُ حُذَيْفَةُ، ثُمَّ رَدَّهَا عَلَيْهِ ثَلَاثًا، كُلُّ ذَلِكَ يُعْرِضُ عَنْهُ حُذَيْفَةُ، ثُمَّ أَقْبَلَ عَلَيْهِ فِي الثَّالِثَةِ، فَقَالَ :يَا صِلَةُ، تُنْجِيهِمْ مِنَ النَّارِ .ثَلَاثًا

[ሑዘይፈቱ ኢብኑል የማን የአላህ መልእክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል አለ፡- «ልብስ ላይ ያለ ዲዛይን አሮጌ ሆኖ እንደሚጠፋው ሁሉ፡- ፆም፣ ሶላት፣ እርድ (አምልኮ) እና ሰደቃ መታወቅ የማይችሉበትና የሚረሱበት ደረጃ እስሚደርሱ ድረስ ኢስላምም ይጠፋል (ፋናው ይታበሳል)፤ የአላህ መፅሀፍ (ቁርአንም) ምድር ላይ አንዲት አንቀፅ እንኳ እስከማትቀር ድረስ በአንድ ምሽት ይነሳል። "እኛኮ አባቶቻችንን ላ ኢላህ ኢለሏህ በምትለዋ ቃል ላይ ስላገኘናቸው እኛም (በምላሳችን) እንላታለን" የሚሉ ሽማግሌዎችንና ባልቴቶችን ጨምሮ ከሰዎች የተወሰኑ ጀማዓዎች ይቀራሉ።» ብለዋል አለ። በዚህ ጊዜ ሲለህ የተባለው የሐዲሡ ዘጋቢ ሰው ለሑዘይፋ: "እነኚህ ሰዎች ፆም፣ ሶላት፣ እርድ (አምልኮ ወይም ሐጅ) እና ሰደቃ የሚባሉት ዒባዳዎች ምን እንደሆኑ የማያውቁ ሆነው ሳለ፤ ላ ኢላሃ ኢለሏህ ምን ትጠቅማቸዋለች!?" አለው። ሑዘይፋም መልስ ሳይሰጠው ትቶት ዞረ። አሁንም ደግሞ ሲጠይቀው ትቶት ይዞራል፤ ለሶስተኛ ጊዜ ሲጠይቀው ግን ወደ ሲለህ በመዞር ቀጣዩን ንግግር ሶስት ጊዜ ደጋግሞ የሚናገር ሲሆን "ሲለህ ሆይ! ከእሳት ታድናቸዋለች" ብሎ መለሰለት።]

[ሐዲሡን፡- ኢብኑ ማጀህ "ሱነኑ" ውስጥ ኪታቡል ፊተን (4049) ላይ ዘግቦታል፣ ሓኪም "ሙስተድረክ" ውስጥ ኪታቡልፊተን ወልመላሒም (4/473) ላይ ዘግቦት: "ቡኻሪና ሙስሊም ባይዘግቡትም በኢማም ሙስሊም ሸርጥ ሰሒሕ የሆነ ሐዲሥ ነው" ብሎታል፤ ቡሰይሪ ዘዋኢድ ላይ (3/254) ኢስናዱ ሰሒህ ነው ብሎታል፤ ኢማሙል አልባኒም "አስ ሰሒሓ": (87/1/171) እና "ሰሒሕ ኢብን ማጀህ" ላይ ሐዲሡን ሰሒሕ አድርገውታል።]

እንደሚታወቀው ሶላት፣ ዘካና ፆም አሳሳቢ ከሆኑት የኢስላም መገለጫዎችና ከሌሎች ዒባዳዎች ይልቅ በሙስሊሞች መካከል በሰፊው ተሰራጭተውና በገሃድ የሚታወቁ ሆነው የሚገኙ ዒባዳዎች ናቸው። ከመሆኑም ጋር ግን ይህ ሀዲሥ እንደሚጠቁመን ግልፅነታቸውና መንሰራፋታቸው ጠፍቶ፤ ያኔ ሙስሊሞች የማያውቋቸውና የማይተገብሯቸው ከሆኑት ከመሳኢል ኸፊያ (ከድብቅ ሀይማኖታዊ ጉዳዮች) የሚሆኑበት ዘመን ይመጣል።

ይህ ሐዲሥ ደግሞ ስለ ሰለምቴዎች ወይም ከኩፍር ወደ ኢስላም የተመለሱበት ጊዜያቸው ቅርብ ስለሆኑ ሰዎች የሚተርክ ሳይሆን፤ ዒልም ጥቂት በሆነበትና ጅህልና በተንሰራፋበት ዘመን ስለሚገኙ ሰዎች ብቻ ነው የሚያትተው።

Nb: ሙኻሊፎች: "ይህ ሐዲሥ ሰዎቹ ሺርክ ላይ ስላልወደቁ ከመስአላችን ጋር አይሄድም" ሊሉ ይችላሉ። ይህ ኢዕቲራድ ትክክል አይደለም፤ ምክንያቱም ሀዲሡ እነኚህ ሰዎች ከኢስላም መገለጫ በጣም ግልፅና ከፍ ያለ ደረጃ ያላቸው የሆኑ ጉዳዮችን እስከመቃረን ያቢቃቸው ሀይለኛ የሆነ ጅህልና ላይ መሆናቸውን ያረጋግጥልናልና። ይህ እንዲህ ከሆነ በግልፅነት የእነዚህ መገለጫዎች አምሳያ የሆኑ ነገሮች ላይ መውደቃቸው አይቀሬ ነው። በተጨማሪም ሰዎቹ እነዚህን ግልፅ የዲኑ መገለጫዎችን ትተው ባለማወቃቸው ምክንያት ዑዝር ከተሰጣቸው፤ እነኚህን ጉዳዮች በግልፅነት በሚጋሩ ሌሎች የኢስላም መሰረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይም ጀህል ዑዝር የሚያሰጥ ከልካይ ምክንያት መሆኑን ይጠቁማል ማለት ነው።

"ዙሁውር" እና "ኽፋእ" ወይም ግልፅነትና መደበቅ አንፃራዊ መሆኑንና "ኒስቢይነት" ሰዎች ላይ ሑክም ከመስጠት ጋር የጠበቀ ትስስር እንዳለው ከሚጠቁሙ መረጃዎች መካከል ሁለተኛ:

በዑመር ኢብኑል ኸጧብ የኺላፋ ዘመን "ሚነስ ሳቢቂነል አወሊን" (ከመጀመሪያዎችና ቀዳሚ ከነበሩት ሙስሊሞች) አንዱ የነበረው፤ እንዲሁም በድር ዘመቻ የተሳተፈው ቁዳመቱ ኢብኑ መዝዑንና ጓደኞቹ ሙተአውዊሎች ሆነው አስካሪ መጠጥን (ኽምርን) መጠጣት ሐላል ባደረጉ ጊዜ ሶሓቦች ከእነሱ ጋር ያደረጉት ሙዓመላ ነው።

እንደሚታወቀው ኽምርን መጠጣት ሐራም መሆኑ በኢስላም ግልፅ ከሆኑ መሳኢሎች ነው። ሐራምን ሐላል፤ ሐላልን ሐራም ማድረግ ደግሞ ከኢስላም የሚያስወጣ ትልቅ የሆነ ኩፍር ነው። ከመሆኑም ጋር ግን ሶሓቦች አላከፈሯቸውም፤ ይልቁንም በተእዊላቸው ምክንያት ዑዝር ሰጥተዋቸዋል። ቁዳመቱ ኢብኑ መዝዑን አዲስ ሰለምቴ አልነበረም፤ እውቀት ካለበት ስፍራም የራቀ አልነበረም። ይልቁንም በነቢዩ ﷺ ዘመን በድር ዘመቻ ከተሳተፉትና በኢስላማቸው ቀዳሚ ከነበሩ ሶሓቦች ነበር።

ይህ እንግዲህ ሶሐቦች ዘንድ በሰው ላይ ሑክም ለመስጠት ግምት ውስጥ የሚገባው፦ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሑጃ ደርሶታል፤ ወይስ አልደረሰውም የሚለው ነጥብ እንጂ፤ ሙኻለፋ የተከሰተባት የመስአላዋ አይነት እንዳልሆነ በገሃድ ያረጋግጥልናል ማለት ነው!!

ልክ እንደዚሁ ወደ ኢስላም ቀደም ብለው ከገቡት ሶሓቦች አንዱ የነበረው አቡ ጀንደል ኢብን ሱሀይል የተባለው ሰሓቢይና ጓደኞቹ በዑመር ዘመን ሻም ሀገር ላይ የማኢዳን አንቀፅ (93) ተእዊል አድርገው እንደመረጃ በመጠቀም ኽምርን ሐላል ባደረጉና በጠጡ ጊዜ ሶሐቦች አላከፈሯቸውም፤ ይልቁንም ስህተተኞች መሆናቸውን አሳውቀዋቸው ለጠጡበት ጥፋት ሀድ ገርፈዋቸዋል፤ እነሱም ቶበተዋል። ቂሷውን ዐብደረዛቅ አስ ሰንዓኒ "ሙሶነፍ": (9/244) ላይ፣ ኢብኑ ዐብዲል በሪ "አል ኢስቲይዓብ": (4/1622) አውስተውታል።

ይህ የቁዳማና የአቡ ጀንደል ቂሷ እንዲሁም ሶሓቦች ከእነሱ ጋር ያደረጉት ሙዓመላ፤ ሽይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ በመሳኢል ዚሂራም ይሁን በሌሎች መሳኢሎች ላይ በጀህልና በተእዊል ዐዝር ሲሰጥ መዝሀቡ ከቆመባቸው አሳሳቢና ወሳኝ ከሆኑት መደገፊያዎቹ የሚመደብ ነው።

ይህም ሽይኹ ቂሷውን ብዙ ጊዜ ደጋግሞ የሚያወሳበትንና እንደመረጃ የሚጠቀምበትን ሚስጥር ይገልፅልናል።

ሶስተኛ: ባለማወቅ ዝሙትን ሐላል ያደረገ ሰው ጋር ኽሊፋው ዑመር ረዲየላሁ ዐንሁ ያደረገው ሙዓመላ ነው።

በዚህ ጉዳይ በርካታና ትክክለኛ የሆኑ አኽባሮች ተዘግበዋል። ከነዚህም መካከል:-

١- عن ابن المسيب قال: ذكروا الزنا بالشام، فقال رجلٌ: زنيتُ، قيل: ما تقول؟ قال: أَوَ حرَّمَهُ اللهُ، ماعلمتُ أن الله حرَّمه، فَكُتِبَ إلى عمرَ بنِ الخطاب، فَكَتَبَ: إنْ عَلِمَ أن الله حرَّمه فحدُّوه، وإن كان لم يعلم فعلِّموه، وإن عاد فحدُّوه

صحيح

أخرجه عبد الرزاق

(7/ 403) عن ابن عيينة عن عمرو بن دينار عن ابن المسيب به

•[1]• ዐብደረዛቅ አስ ሰንዓኒ "ሙሶነፍ": (7/403) ላይ ከሰዒድ ኢብኑል ሙሰየብ የተያዘን አሠር ትክክለኛ በሆነ ሰነድ እንዲህ ሲል ዘግቧል:

«ሻም ሀገር አንድ ወቅት ስለ ዚና ሲወራ የሰማ የሆነ ሰው (ሳይሸማቀቅ ዘና ብሎ): "እኔ ሰርቻለሁ!" አላቸው። አብረውት ያሉት ሰዎችም: "ምን እያልክ ነው?" አሉት። እሱም "አላህ ሐራም አድርጎታልንዴ!? እኔኮ አላህ ሐራም ማድረጉን

አላውቅም!" አላቸው። ከዚያ ጉዳዩ ወደ ዑመር ተፅፎ ተላከ፤ ዑመርም: «አላህ ሐራም ማድረጉን የሚያውቅ ከሆነ የዝሙተኛን ሀድ (ቅጣት) ቅጡት፤ የማያውቅ ከሆነም አስተምሩት፤ ዳግመኛ ከሰራ ግን ሀድ (ቅጣትን) ቅጡት።» የሚልን መልስ በፅሁፍ ላከላቸው።

ኢብኑል ሙለቂን ያዘጋጁትን "አል በድሩል ሙኒር"(8/637) እና ሷሊሕ አሉሸ ሸይኽ ያዘጋጀውን "አት ተከሚል ሊማ ፋተሁ ተኽሪይጁሁ ሚን ኢርዋኢል ጀሊል": (170) ላይ ተመልከት።

ይህ አሠር በገሃድ እንደሚያሳየን ሰውየው በሸሪዓ ሐራምነቱ ዚሂር የሆነን ጉዳይ ሐላል አድርጎ እንኳ ዑመር ረዲየላሁ ዐንሁ አላከፈረውም፤ "ሐድ" ቅጣትም እንዲቀጣ አላደረገውም!!

٢ـ ومن ذلك ما رواه يحيى بن عبد الرحمن عن أبيه قال :توفِّي حاطبٌ، فأعتق من صلى من رقيقه وصام، وكانت له أمة نوبية قد صلت وصامت، وهي أعجمية لم تفقه، فلم ترعه إلا بحبلها، وكانت ثيبًا، فذهب إلى عمر رضي الله عنه فحدثه .

فقال :لأنت الرجل لا تأتي بخير

فأفزعه ذلك

فأرسل إليها عمر رضي الله عنه فقال أحبلت ؟

فقالت :نعم، من مرعوش بدرهمين

فإذا هي تستهل بذلك لا تكتمه

قال: و صادف عليًّا، وعثمان، وعبد الرحمن بن عوف رضي الله عنهم، فقال: أشيروا عليَّ

وكان عثمان رضي الله عنه جالسًا فاضطجع

فقال علي، وعبد الرحمن :قد وقع عليها الحد

فقال :أشر عليَّ يا عثمان

فقال :قد أشار عليك أخواك

قال :أشر عليَّ أنت

قال :أراها تستهل به كأنها لا تعلمه، وليس الحد إلا على من علمه

فقال :صدقت، والذي نفسي بيده ما الحد إلا على من علمه

فجلدها عمر ـ رضي الله عنه ـ مائة، وغربها عامًا

أخرجه عبد الرزاق في المصنف

(١٣٦٤٤)

والبيهقي في السنن ،

: (١٦٨٤٢)

وهو صحيح الإسناد، انظر :التكميل لما فاته تخريجه من إرواء الغليل

(١٧٠)

للشيخ صالح آل الشيخ

•[2]• የሕያ ኢብኑ ዐብዲረሕማን ከአባቱ ይዞ ባወራው አሠር እንዲህ ይላል፦ «አያቴ ሓጢብ ሲሞት አባቴ ዐብዱረሕማን ከሓጢብ ባሮች መካከል የሚሰግዱትንና የሚፆሙትን ነፃ አወጣቸው፤ ነፃ ከወጡት መካከልም ዐረብ ያልሆነች አንዲት እውቀት የሌላት ጥቁር ሴት ነበረች፤ እሷንም ድንገት እርጉዝ ሆና አይታት ደነገጠ፤ እሷ ደግሞ አግብታ የምታውቅ ናት፤ እናም ወዲያው ወደ ዑመር ረዲየላሁ ዐንሁ በመሄድ ጉዳዩን ነገረው። ዑመርም: "አንተ እንደው በመልካም ነገር የማትመጣ ሰው ነህ" አለው። ይህ አባባል ታድያ ዐብዱረሕማንን አስደነገጠው፤ ዑመርም ወዲያው ሰው ልኮባት ቀረበችና: "አርግዘሻል ወይ?" ሲል ጠየቃት፤ እሷም ከምንም ሳትቆጥረው፤ ምንም ሳትደብቅና ጉዳዩን ቅልል አድርጋ: "አዎ አርግዣለሁ፤ ያውም ከመርዑሽ በሁለት ዲርሃም" ብላ መለሰችለት።

በዚህ ሁኔታ ላይ ሳለ ድንገት ዐሊይን፣ ዑሥማንንና ዐብዱረሕማን ኢብኑ ዐውፍን በማግኘቱ "እስኪ ስለዚህ ጉዳይ ምን ትሉኛላችሁ?" በሚል ሀሳባቸውን እንዲያጋሩት ጠየቃቸው። ዑሥማን ቁጭ ብሎ ነበርና ገደም አለ፤ ዐሊይና

ዐብዱረሕማንም: "ይህቺ ሴት ሀድ (ተቀጥቅጦ መገደል) ተረጋግጦባታል" አሉት። ዑመር "አንተሳ ዑሥማን ምን አይነት ምክረ ሀሳብ ትሰጠኛለህ?" አለው። ዑሥማንም "በእርግጥ ሁለት ወንድሞችህ ሀሳባቸውን ለግሰውሃል" አለው። በዚህጊዜ: "(ያ እንዳለ ሆኖ) አንተም ሀሳብ ስጠኝ" አለው ዑመር። ይህኔ ዑሥማን እንዲህ አለ: "እኔ መቼም ሴትየዋ ጉዳዩን ቅልል አድርጋ ስታወራ ነው የማያት፤ (ሐራምነቱን) የማታውቀው ትመስላለች፤ ሀድ ደግሞ በሚያውቅ ሰው ላይ እንጂ (በማያውቅ ላይ) አይፈፀምም።" ዑመርም "እውነትህን ነው፤ ነፍሴ በእጁ በሆነው ጌታ ይሁንብኝ ሀድ በሚያውቅ ሰው ላይ እንጂ (በማያውቅ ላይ) የለም።" በማለት የዑስማንን ሀሳብ መደገፉን አረጋገጠ። ከዚያም ዑመር ረዲየላሁ ዐንሁ አንድ መቶ ግርፋት እንድትገረፍና ለአንድ አመት ያህል ከሀገሯ ርቃ እንድትኖር ወሰነባት።»

[ዐብዱረዛቅ አስ ሰንዓኒ "ሙሶነፉ" (13644) ላይ እና በይሀቂይ "ሱነኑ" (16842) ላይ ትከክለኛ በሆነ የዘገባ ሰንሰለት ዘግበውታል። ሷሊሕ ላሉሽ ሸይኽ ያዘጋጀውን "አት ተከሚል ሊማ ፋተሁ ተኽሪይጁሁ ሚን ኢርዋኢል ኘሊል": (170) ላይ ተመልከት።]

ይህ አሠር በግልፅ እንደሚጠቁመን ሴትየዋ ከባርነት ነፃ የወጣች አግብታ ምታውቅ ዝሙተኛ በመሆኗ የእሷ ሀድ ወይም የቅጣት ወሰን ተቀጥቅጦ መገደል ነበር፤ ነገር ግን ዑመር ረዲየላሁ ዐንሁ በጅህልናዋ ምክንያት ይህን ቅጣት አነሳላት፤ ለ"ተዕዚይር" ወይም ለመቀጣጫና አደብ ማስያዣ የሚሆናትን መቶ ግርፋትና አመት ያህል ከሀገሯ መርራቅንም ወሰነባት። ይህ የዑመር ውሳኔ መቀጣጫ የሆነ "ተዕዚይር" እንጂ "ሀድ" አለመሆኑንና "ሀድዱን" በጅህልናዋ ሰበብ ያነሳላት መሆኑን ኢማሙል በይሀቂ "ሱነኑ" (8/238) ላይ ተንቢህ አድርጓል።

ባጠቃላይ እነዚህ ሁሉ ኣሣሮች ሶሓቦች ዘንድ በጀህል ዑዝር ለመስጠት ግምት ውስጥ የሚገባው የሑጃው መድረስ ወይም አለመድረስ እንጂ የመስአላዋ አይነት ብቻ እንዳልሆነ ያረጋግጥልናል።

በዚህ ዙሪያ ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ እንዲህ ይላል፦

وقد زنتْ على عهد عمر امرأةٌ، فلما أقرَّتْ به، قال عثمان: إنها لتستهل به استهلالَ مَن لم يعلم أنه حرام

فلما تبين للصحابة أنها لا تعرف التحريم لم يحدُّوها، واستحلال الزنى خطأٌ قطعًا مجموع الفتاوى"

(19/210)

وانظر "منهاج السنة

(5/51)

«በዑመር ዘመን የሆነች ሴት ዝሙት ሰርታ፤ መስራቷንም ባመነች ጊዜ ዑሥማን እንዲህ አለ: "ኧረ ይቺ ሴትዮ ሐራምነቱን የማያውቅ ሰው አቅልሎ እንደሚያየው እሷም ጉዳዩን ቅልል አድርጋ የምታይ ናት!!" አለ። ሴትየዋ የዝሙትን ሐራምነት የማታውቅ መሆኗ ለሰሓቦች በተገለፀላቸውም ጊዜ (አግብቶ የሚያውቅ ዝሙተኛ የሚ፡ሰውን) ሀድ ሳያቆሙባት ቀርተዋል። ዝሙትን ሐላል ማድረግ ደግሞ በእርግጠኝነት ከባድ የሆነ ስህተት ነው» "መጅሙዑል ፈታዋ" : (19/210)፣ "ሚንሃጅ አስ ሱንና" ሊብኒ ተይሚያ: (5/51) ላይ ተመልከት።

***** ***** ***** *****

ኢብኑ ተይሚያ በመስአላ ኸፊያ እንጂ በመስአላ ዚሂራ ዑዝር አይሰጥምን?

إخواني وأخواتي

ባለፈው ፅሁፍ ላይ መስአላ ዚሂራና ኸፊያን መለያየትን ወደ ኢብኑ ተይሚያ ማስጠጋት ትክክል እንዳልሆነ ራሱን በቻለ ርእስ እንደምመለስበት ቃል በገባሁት መሰረት ዛሬ በአላህ ፈቃድ ይዤ መጥቻለሁ።

በሙኻሊፍ ላይ ሑክም ለመበየንና ዑዝር ቢልጀህልን ላለመስጠት መስአላውን ወሳኝ ጉዳይ አድርጎ ማየት፤ እንዲሁም ይህን መስአላ ወደ ሸይኽል ኢስላም ማስጠጋት ትክክል አይደለም። ትክክል ያልሆነበት ምክንያትም ከብዙ አንግሎች አንፃር ነው።

①ኛ ኢብኑ ተይሚያ ዐለይሂ ረሕመቱላህ ትልልቅና ግልፅ የሺርክ መስአላ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በጀህል ምክንያት ዑዝር እንደሚሰጥ በርካታ ቦታዎች ላይ የገለፀ መሆኑ ነው። ለምሳሌ ያህል፦

•[1]• ወደ ኢስላም የሚጠጉ የሆኑ ሰዎች አላህ እንጂ ማንም በማይችለው ጉዳይ ከእሱ ውጭ በሙታኖችም ሆነ ህያው በሆኑ አካሎች ኢስቲጃዛ በማድረግ ሺርክ ውስጥ ቢወድቁ እንደማይከፈሩ ተናግሯል። ሸይኽል ኢስላም ተጠየቀ

سئل شيخ الإسلام ابن تيمية رحمه الله

ما تقول السادة العلماء أئمة الدين - رضي الله عنهم أجمعين - في قومٍ يُعظِّمون المشايخ بكون أنهم يستغيثون بهم في الشدائد ويتضرعون إليهم، ويزورون قبورهم ويُقبّلونها

ويتبركون بترابها ويوقدون المصابيح طول الليل ويتخذون لها مواسم يقدمون عليها من البعد يسمونها ليلة المحيا فيجعلونها كالعيد عندهم ويَنْذُرُون لَها النُّذور ويُصَلُّون عندها

فهل يحل لهؤلاء القوم هذا الفعل، أم يحرم عليهم، أم يكره؟ وهل يجوز للمشايخ تقريرُهم على ذلك، أم يجب عليهم منعُهم من ذلك وزجرُهم عنه؟، وما يجب على المشايخ مِن تعليم المُريدين وما يُوصَون به؟ وهل يجوز تقريرهم على أخذ الحيَّات والنار وغير ذلك أم لا؟ وماذا يجب على أئمة مساجد يحضرون سَماعَهم ويُوافِقونه هذه الأشياء؟ وما يجب على وليّ الأمر في أمرهم هذا؟ أفتونا مأجورين

فأجاب ابن تيمية رحمه الله تعالى

الحمد لله رب العالمين من استغاث بميّتٍ أو غائب من البشر بحيث يدعوه في الشدائد والكربات ويطلب منه قضاء الحوائج فيقول: يا سيدي الشيخ فلان أنا في حسبك وجوارك أو يقول عند هجوم العدو: يا سيدي فلان يستوحيه ويستغيث به أو يقول ذلك عند مرضه وفقره وغير ذلك من حاجاته: فإن هذا ضال جاهل مشركٌ عاصٍ لله تعالى باتِّفاق المسلمين؛ فإنهم متفقون على أن الميت لا يُدعى ولا يطلب منه شيءٌ سواء كان نبيا أو شيخا أو غير ذلك .. وهذا الشرك إذا قامت على الإنسان الحجة فيه ولم يَتُبْهِ وجب قَتْلُهُ كقتل أمثاله من المشركين ولم يُدفَن في مقابر المسلمين ولم يُصَلَّ عليه، وأما إذا كان جاهلًا لم يبلغه العلمُ ولم يعرفْ حقيقةَ الشرك الذي قاتل عليه النبيُّ صلى الله عليه وسلم المشركين فإنه لا يُحْكَمُ بِكُفْرِهِ ولا سيّما وقد كَثُرَ هذا الشرك في المنتسبين إلى الإسلام، ومن اعتقد مثل هذا قربةً وطاعةً فإنه ضالٌّ باتفاق المسلمين وهو بعد قيام الحُجَّة كَافِرٌ

جامع المسائل

(3/145 – 151)

«መሻዪኾችን ስለሚያልቁ፣ በመከራዎች ጊዜ በእነሱ ኢስቲጅሣ ስለሚያደርጉ፣ ለእነሱም የሚዋደቁ፣ መቃብሮቻቸውንም የሚዘይሩና የሚስሙ፤ ከአፈሩም በረካ የሚፈልጉ፤ እዚያው ሌሊቱን ሙሉ ጧፍ ሲያበሩ የሚያድሩ፤ ቀናት አድርገውላት ከሩቅ ስፍራ ወደሷ የሚመጡባት፤ ህያው መሆኛ ብለው የሚሰይሟትና እንደ ዒድ (አመት በዓል) አድርገው የሚቆጥሯት ምሽት ያለቻቸው፤ ለመቃብሮቹም ስለት የሚስሳሉ፤ መቃብሮቹም ዘንድ የሚሰግዱ ስለሆኑ ሰዎች፤ የዲኑ መሪዎች ዑለማኦቻችንና አለቆቻችን ምን አይነት ብይን ይሰጣሉ? ይህን ተግባር እነኚህ ሰዎች ሊፈፅሙት ይፈቀድላቸዋልን? ወይስ ሊሰሩት ሐራም ወይም መከሩህ የሆነ ነገር ነው? ስራውን ሲሰሩ የሚመለከቷቸው መሻዪኾችስ ሰዎቹን ባሉበት ሁኔታ ሊተውዋቸው ወይም ይሁንታ ሊሰጧቸው ይፈቀድላቸዋልን? ወይስ ደግሞ ከዚህ ፀያፍ ተግባራቸው ሊከለክሏቸውና ሊቆጧቸው ግድ ይሆንባቸዋል? እነኚሁ መሻዪኾች ሙሪዶችን (ተማሪዎችን) ምን አይነት ት/ት ማስተማር አለባቸው? በምንስ ነው አደራ ሊሏቸው የሚገባቸው? እባቦችንና እሳትን የሚጨብጡትንስ ዝም ማለት አለባቸው፤ ወይስ መናገር አለባቸው? የሰዎቹን "ሰማዕ" (መንዙማና ነሺዳ) ተገኝተው ይሁንታ የሚሰጡ የመስጊድ ኢማሞችስ ምን አይነት ግዴታ አለባቸው? እነኚህ ሰዎች በሚፈፅሟቸው ተግባራት ላይ የሀገሩ መሪ ሚናስ ምን ሊሆን ይገባል? እባክዎትን ምንዳዎን አላህ ይስጥልንና በጉዳዩ ያለዎትን ፈትዋ ለግሱን!!» በሚል ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ ተጠየቀ ።

ኢብኑ ተይሚያም በተጠየቀው ጥያቄ ዙሪያ ሰፊ የሆነና ረዘም ያለ መልስን መለሰላቸው፤ በውስጡም የኢስቲጅሣ ቢኻይሪላህን ሑክም እንዲህ ሲል በማያሻማና ግልፅ በሆነ ማብራሪያ መልሶላቸዋል :

«ምስጋና ለአላህ የተገባ ነው፤ በሞተ ወይም ህያው ሆኖ ነገር ግን ሩቅ ስፍራ ባለ ሰው ኢስቲጅሣ የሚያደርግ፤ ማለትም በመከራዎችና አስጨናቂ በሆኑ ክስተቶች ሐጃዎቹን እንዲፈፅምለት: "ያ ሰይዱዲ ሸህ እገሌ ሆይ! እኔ በአንተ ጥበቃና መብቃት ውስጥ ነኝ" በማለት የሚለምን ሰው፤ ወይም ጠላቱ ሊያጠቃው ሲል፣ ወይም ህመም ሲደርስበት፣ ወይም ደግሞ ድህነት ሲያገኘው "ያ ሰይዱዲ ፉላን … " እያለ ኢስቲጅሣ የሚያደርግ ይህ አይነቱ ሰው በሙስሊሞች ስምምነት፡- ዲል፣ ጃሂል፣ሙሽሪክና አላህን ያመፀ ነው። ምክንያቱም የሞተ ሰው ነቢይም ሆነ ሸይኽ

ወይም ሌላ የሆነ ይሁን እንደማይለመንና ከእሱም ምንም አይነት ሓጃ እንደማይፈለግ ሙስሊሞች ስምምነት አላቸውና። ይህ አይነቱን ሺርክ የሚሰራ ሰው ሑጃ ከቆመበትና መረጃ ደርሶት ከተግባሩ የማይታቀብ ከሆነ የእሱ አምሳያ ሙሽሪኮች እንደሚገደሉት እሱንም መግደል ግድ ነው፤ ሙስሊሞች መቃብር አይቀበርም፤ አይሰገድበትምም። ነገር ግን እውቀት ያልደረሰው ጃሂል የሆነ ሰው ከሆነና ነቢዩ ﷺ ሙሽሪኮችን የተጋደሉበትን ሺርክ ሐቂቃውን የማያውቅ ከሆነ፤ ይህ አይነቱ ሰው ካፊር ተብሎ አይተሓከምበትም!! በተለይ ይህ አይነቱ ሺርክ ራሳቸውን ወደ ኢስላም የሚያስጠጉ የሆኑ ሰዎች ውስጥ በብዛት እየተከሰተ ባለበት ወቅት (ካፊር ሙሽሪክ እያሉ ከኢስላም የሚወጣበት በሆነ ብይን አይበየንበትም)። ይህ አይነቱን የሺርክ ተግባር ኸይር ስራና ወደ አላህ መቃረቢያ አድርጎ ኢዕቲቃድ የሚያደርግ ወይም የሚያምን ሰው በሙስሊሞች ስምምነት፡- ዱል ነው፤ ሑጃ ከደረሰውም በኋላ ካፊር ይደረጋል!!» (ጀሚዑል መሳኢል:3/145 _ 151)

ይህ የሸይኽል ኢስላም ፈትዋ እጅግ በጣም ወሳኝ የሆነ ፈትዋ ነው። ምክንያቱም፡-

(ሀ) በአንድ ጥቅል በሆነ ጉዳይ ዙሪያ ነገሩን በመሀል አስገብቶ "ዐለጥሪይቅ" የሚያወራለት ሳይሆን በአንድ ውስንና ልዩ በሆነ ጉዳይ ስለሰዎቹ ግልጽና ትክክለኛ የሆነ መልስ ተፈልጎ በተጠየቀ ጊዜ የሰጠው መልስ ስለሆነ ነው። በእንዲህ አይነት ሁኔታ ተጠይቆ የሚሰጠው መልስ፤ የፈትዋው ባለቤት በጉዳዩ ላይ የሚያምንበትን ትክክለኛ አቋም ይበልጥ የሚያንፀባርቅና የሚገልፅ ነገር ነው ማለት ነው። ስለዚህ ይህን የማያሻማና ግልጽ የሆነ የሸይኹን ንግግር ትተን ወደ ሌላ ልንሄድ እንዴት ያስችለናል?!

(ለ) ኢስቲኟሣ ቢኻይሪላህ የሚያደርጉ ሰዎችን ሑክም በዝርዝር የሚዳስስ ፈትዋ ስለሆነ፤ በውስጡም፡- ሳያውቅ ሺርኩ ላይ የወደቀ ሰውና እያወቀ ሺርኩን የሚተገብር ሰው ሑክማቸው መለያየቱን ግልፅ የሆነ የሸይኹን ትንታኔ ይዟል።

(ሐ) ጥያቄው የሚያጠነጥነው አዲስ ስለምቴ ስለሆኑ ሰዎች ወይም ሙስሊሞች ከሚገኙበት አካባቢ ራቅ ያለ ስፍራ ስለሚኖሩ ሰዎች ሳይሆን (ሙስሊሞች መንደር፣ ቁርአን የሚነበብበትና የሚደመጥበት፣ ኧረ እንደውም) ፈትዋ የሚሰጡ ዑለማኦች፣ መሻዪኾችና የመሳጂድ አኢማዎች በሚገኙበት ሀገር ውስጥ ኢስቲኟሣ ስለሚያደርጉ ሙስሊሞች ሁኔታ የሚያጠነጥን በመሆኑ ነው።

•[2]• በከሪ የተባለው የሱፍያ ሸይኽ ላይ ረድ ሲያደርግበት እንዲህ ብሏል፡-

فإنا بعد معرفة ما جاء به الرسول ، نعلم بالضرورة أنه لم يَشْرَعْ لأُمَّتِهِ أن تدعو أحدًا من الأموات ، لا الأنبياء ولا الصالحين ولا غيرهم، لا بلفظ الاستغاثة ولا بغيرها، ولا بلفظ الاستعاذة ولا بغيرها، كما أنه لم يشرع لأمته السجود لميت ، ولا لغير ميت ونحو ذلك؛ بل نعلم أنه نهى عن كل هذه الأمور ، وأن ذلك من الشرك الذي حرمه الله ورسوله

لكن لغلبة الجهل ، وقلة العلم بآثار الرسالة في كثير من المتأخرين؛ لم يمكن تكفيرهم بذلك، حتى يتبيَّن لهم ما جاء به الرسول ممَّا يخالفه، ولهذا ما بيَّنت هذه المسألة قط لمن يعرف أصل الدين ؛ إلا تفطن، وقال هذا أصل دين الإسلام...

الرد على البكري

(ص: 411)

«እኛኮ መልእክተኛው ይዘው የመጡትን ዒልም ከተረዳን በኋላ፤ ከሙታኖች ነቢያትንም ይሁን ሷሊሖችን ወይም ሌሎች አካላትን ኢስቲጃዛ ማድረጊያ በሆነ ቃል ድረሱልን በማለትም ይሁን ጠብቁን በማለት ወይም በሌላ የመማፀኚያና የመለመኚያ ቃላቶች ማንንም መለመንን ለኡመታቸው ያልደነገጉ መሆናቸውን በግልፅ እናውቃለን። እንዲሁም ለሞተም ይሁን ህያው ለሆነ አካል ሱጁድ ማድረግን አለመደንገጋቸውንም እናውቃለን። ይልቁንም እነኚህን ነገሮች ባጠቃላይ መከልከላቸውንና አላህና መልእክተኛው ሐራም ያደረጓቸው የሺርክ ተግባራት መሆናቸውን ነው የምናውቀው። ነገር ግን ከኋላ ዘግይተው የመጡ ብዙዎቹ የኡማው ክፍሎች ዘንድ ጅህልና ስለተንሰራፋና ስለሀየለ፣ እንዲሁም ስለ ነቢያዊ ፋናዎች ያላቸው የእውቀት መጠንም ጥቂት ስለሆነ፤ መልእክተኛው ይዘውት የመጡት ዲንና የእሱ ተቃራኒ የሆነው (ሺርክና ኩፍር) እስኪብራራላቸው ድረስ ያለፉትን የሺርክ ተግባራት በመስራታቸው ብቻ ሰዎቹን ልናከፍራቸው አይቻለንም፤ ለዚህም ነው መሰረታዊ የዲኑን ክፍሎች የሚያውቅ ለሆነ ሰው ጉዳዩን (በደንብ) ሳብራራለት ወዲያው ይነቃና ተረድቶ "አዎ እውነትህን ነው!! ይህ የዲን መሰረት ነው" የሚለው። » "አር ረዱ ዐለል በከሪ" (ገፅ: 411)

እዚህ ላይ ኢብኑ ተይሚያ፡- ኢስቲጃዛ ቢሻይራላህ ትልቅ ሺርክ ወይም ኩፍር መሆኑን ቢያወሳም፤ ይህ አይነትን ሺርክ የፈፀመ ሰው ሁሉ ግን ሑጃ ካልደረሰው በስተቀር እንደማይከፈር አጠንክሮ ገልፆል።

ይህና ከላይ ያሳለፍነው የሸይኹ ፈትዋ እንደሚጠቁሙት፡- ይህ አይነት ሺርክ ላይ ባለማወቅ የወደቁ ሰዎች አዲስ ሰለምቴዎች ባይሆኑም ሑጃ (እውቀት) እስካልደረሳቸው ድረስ ዑዝር የሚሰጣቸው መሆኑን በይፋ ይገልፃሉ።

•³• አላህ እንጂ ማንም በማይችለው ነገር በመልእክተኛው ﷺ ኢስቲጃዛ ያደረገ ሰው ሑጃ ካልደረሰው በስተቀር ካፊር እንደማይደረግም ገልፆል።

ሸይኹል ኢስላም እንዲህ በሚል ተጠየቀ:

سئل شيخ الإسلام رحمه الله تعالى :ما تقول السادة العلماء أئمة الدين وفقهم الله لطاعته فيمن يقول :لا يستغاث برسول الله صلى الله عليه وسلم هل يحرم عليه هذا القول وهل هو كفر أم لا؟ وإن استدل بآيات من كتاب الله وأحاديث رسوله ﷺ هل ينفعه دليله أم لا؟ وإذا قام الدليل من الكتاب والسنة فما يجب على من يخالف ذلك؟ أفتونا مأجورين

(የዲኑ መሪዎች የሆኑት ዑለማእቻችን አላህን ለመታዘዝ እሱው ይወፍቃቸውና "በአላህ መልእክተኛ ﷺ ኢስቲጃዛ ማድረግ አይቻልም ስለሚል ሰው ምን ይላሉ? ይህን መናገሩ ሐራም ይሆንበታልን? የንግግሩስ ፍርድ ኩፍር ነው ወይስ ምንድን ነው? የአላህን ቁርአናዊ አናቅፆችና የነቢዩ ﷺ ሐዲሦችን እንደመረጃ ቢያቀርብ መረጃው ይጠቅመዋል ወይስ አይጠቅመውም? በጉዳዩ ከቁርአንና ከሐዲሥ የሆነ ትክክለኛ መረጃ ቢቀርብ ይህን የሚቃረነው አካል ያለበት ግዴታ ምንድን ነው? አላህ ይመንዳዎትና እባክዎ ፈትዋዎን ይስጡን?)

ኢብኑ ተይሚያም በጥያቄው ዙሪያ ረዘም ያለ መልስ ሰጣቸው፤ መልሱ መጀመሪያ ላይም፡- የነቢዩ ﷺ ሸፋዓ በቂያማ እለት የተረጋገጠ መሆኑን ሰፋ ያለ ማብራሪያ ካስቀመጠ በኋላ አንዳንድ የሚፈቀዱ የኢስቲጃዛ አይነቶችን ገለፀ፤ ከዚያም እንዲህ አለ፡-

والاستغاثة بمعنى أن يُطْلَبَ من الرسول ﷺ ما هو اللائق بمنصبه لا ينازع فيها مسلم ومن نازع في هذا المعنى فهو إما كافر إن أنكر ما يكفر به وإما مخطئ ضال

وأما بالمعنى الذي نفاه رسول الله صلى الله عليه وسلم فهو أيضا مما يجب نفيها، ومن أثبت لغير الله ما لا يكون إلا لله فهو أيضا كافر إذا قامت عليه الحجة التي يكفر تاركها مجموع الفتاوى

:(1/108 – 112)

«ለመልእክተኛው ﷺ ክብር ተስማሚ በሆነ ነገር ወይም እሳቸው ሊያደርጉት በሚችሉት ነገር ኢስቲጅሣ ማድረግና ከእሳቸው መፈለግ፤ ይህ ማንኛውም ሙስሊም የሆነ ሰው የማይቃረነው ጉዳይ ነው፤ ይህን የሚቃረን ሰው፡- ቢቃወመው ሊያከፍረው የሚችልን ነገር ከተቃወመ ካፊር ይሆናል፤ ወይም ዲል እና የተሳሳተ ሰው ይሆናል። መልእክተኛው ﷺ የነፈዩት ወይም የከለከሉት የኢስቲጅሣ አይነት ከሆነ ደግሞ እኛም ልንከለክለው ግድ ይለናል፤ ከአላህ ውጪ ካለ አካል ይህን የማይቻልን (የኢስቲጅሣ አይነት) መጠየቅ እንደሚቻል የሚያሠብት ወይም የሚያፀድቅ ሰው፤ የሚተዋት ሰው የሚከፈርባት የሆነችዋ ሑጃ ደርሳው ከሆነ ካፊር ይሆናል።» "መጅሙዑል ፈታዋ" (1/108_ 112)

እነኚህ የኢብኑ ተይሚያ ንግግሮች ኢስቲጅሣ ቢሻይሪላህና የመሳሰሉ ግልፅ የሆኑ ሺርኪያቶች፤ አላህ ሐራም ያደረጋቸው ከባባድ ወንጀሎች መሆናቸውን ሳያውቅና በዚሁ ጉዳይ ትክክለኛ የሆነ ዒልም ወይም ሑጃ ሳይደርሰው ተግባራቱን የሚሰራ ሰው እንደማይከፈር በግልፅ ይጠቁማሉ።

•⁴• ሲናገሩት የሚያከፍር የሆነን ንግግር የተናገረ ሰው እሱን ለማከፈር የሚከለክሉ ነገሮች እላዩ ላይ ሊኖሩ ስለሚችሉ ንግግሮቹን በመናገሩ ብቻ እንደማይከፈር እንዲህ ሲል ተናግሯል፡-

وهكذا الأقوال التي يَكْفُرُ قائلُها قد يكون الرجل لم تبلغْهُ النصوص المُوجِبَةُ لمعرفة الحق، وقد تكون عنده ولم تثبت عنده، أو لم يتمكن مِن فَهْمِها، وقد يكون قد عرضتْ له شبهات يعذره الله بها، فمن كان من المؤمنين مجتهدا في طلب الحق وأخطأ فإن الله يغفر له خطأه كائنا ما كان، سواء كان في المسائل النظرية أو العملية هذا الذي عليه أصحاب النبي صلى الله عليه وسلم وجماهير أئمة الإسلام مجموع الفتاوى.

(23/346)

«ተናጋሪው ሲናገራቸው የሚያከፍሩት የሆኑ ንግግሮችም እንደዚሁ (ማለትም፡- ንግግሮቹን በመናገሩ ብቻ ካፊር አይደረግም)፤ ምክንያቱም ወይ ሐቅን እንዲያውቅ የሚያስችሉት መረጃዎች ያልደረሰው (ጃሂል የሆነ) አካል ሊሆን ይችላል፤ ወይም መረጃዎቹ ደርሰውት ነገር ግን እሱ ዘንድ ያልሠበቱ (ያልተረጋገጡ) አድርጎ የሚያያቸው ሊሆን ይችላል፤ አሊያም መረጃዎቹን ለመገንዘብ ባለመቻሉ፤ ወይም ደግሞ አላህ በእሷ ምክንያት ለእሱ ዑዝር የሚሰጥበት (መረጃዎቹን የሚመልስባቸው) ሹቡሃቶች ገጥመውት ይሆናልና።

ከሙእሚኖች ሆኖና ሐቅን ለማግኘት ጥረት አድራጊ ሆኖ፤ በዐቂዳዊም ይሁን በአሕካማዊ ጉዳዮች ላይ ማንኛውንም አይነት ስህተት ቢሳሳት አላህ ምህረቱን ይሰጠዋል፤ ይህ የነቢዩ ﷺ ሶሓቦችና አብዛኞቹ የዲኑ አኢማዎች ያሉበት አቋም ነው።» "መጅሙዑል ፈታዋ" (23/346)

ይህና መሰል የሸይኹ ንግግሮች በጀህል ወይም በተእዊል ሺርክ ወይም ኩፍር የሆነን ስራ የሚሰራ ሰው እንደማይከፈር በግልፅ ይጠቁማል፤ እንዳይከፈር የሚከለከለው ምክንያት እስካልተወገደለት ድረስም በኢስላም ጥላ ስር ያለ መሆኑንም ይገልፃሉ።

ይህ ንግግሩ ቀጣዮቹን አሳሳቢ ነገሮች ይጠቁማል።

(ሀ) ዑዝር ከመስጠት አኳያ ጀህል እና ተእዊል ኢብኑ ተይሚያ ዘንድ ባባቸው ወይም መግቢያቸው አንድ መሆኑንና እኩል የሆነ እይታ እንደሚታዩ።

(ለ) ባለማወቅ ወይም በተእዊል ሺርክ የሆነን ተግባር የሰራ ሰው መሰረታዊ የሆነ ስያሜውን (ኢስላምን) አለመነጠቁን ይጠቁማል፤ ለዚህም ነው ኢብኑ ተይሚያ ያለፈው ፈትዋው ላይ: «ከሙእሚኖች ሆኖና ሐቅን ለማግኘት ጥረት አድራጊ ሆኖ በዐቂዳዊም ይሁን በአሕካማዊ ጉዳዮች ማንኛውንም አይነት ስህተትን ቢሳሳት አላህ ምህረቱን ይሰጠዋል» ያለው። የአላህን ምህረት ደግሞ ኢስላም ጥላ ስር ያለ አካል እንጂ አያገኘውም!!

(ሐ) ዑዝር በአህካማዊም ሆነ በዐቂዳዊ ጉዳዮች የሚሰጥ መሆኑንም ይጠቁማል።

•[5]• በሁሉም የዲኑ ክፍሎች ማለትም መሰረታዊ ወይም ዐቂዳዊ በሆኑትም ይሁን መሰረታዊ ባልሆኑ የዲኑ ክፍሎች በጀህል ዑዝር እንዳለና ሑጃ መድረሱ እስካልተረጋገጠ ድረስ አንድም ሰው በተዕዩይን የማይከፈር መሆኑን የአቋም መግለጫ በሆነው ንግግሩ ላይ እንዲህ በማለት በተእኪድና በይፋ አስቀምጧል፦

إني دائمًا ومَنْ جالسني يعلم ذلك مِنِّي، أنِّي مِن أَعْظَمِ الناسِ نَهْياً عن أنْ يُنْسَبَ مُعَيَّنٌ إلى تكفيرٍ وتفسيقٍ ومعصية، إلا إذا عُلِمَ أنه قد قامتْ عليه الحُجَّةُ الرِّساليَّة التي مَن خالَفَها كان كافراً تارة ، وفاسقاً أُخرى ، وعاصياً أخرى

وإني أقرّر أن الله قد غفر لهذه الأمة خطأها وذلك يعمُّ الخطأ في المسائل الخَبَرية القولية والمسائل العملية

مجموع الفتاوى

(3/229)

«እኔ ሁልጊዜ አንድን ሰው በተዕዩን ነጥሎ ወደ ኩፍር፣ ወደ ፊስቅ እና ወደ መዕሲያ ማስጠጋትን በጣም አድርገው ከሚቃወሙ ሰዎች የምመደብ ነኝ፤ ይህን ጉዳይ እኔን የሚያቀማምጡ ሰዎችም ያውቃሉ!! የተቃረናት ሰው እንደ ሁኔታው አንዳንዴ ካፊር፤ ሌላ ጊዜ ፋሲቅ ወይም ደግሞ ወንጀለኛ የሚደረግባት ነቢያዊ ሑጃ ሰውዬው ላይ በእርግጥ መቆሙ ካልታወቀ በስተቀር (ከዚህ ውጭ ሑጃ ሳይቆምበት ካፊር፣ ፋሲቅና ዓሲ እያሉ መበየንን አጥብቀው ከሚያወግዙት ነኝ)። ለሙስሊሙ ማህበረሰብ አላህ ስህተታቸውን በእርግጥ ምሯቸዋል በማለትም ደጋግሜና አስረግጬ እናገራለሁ!! ስህተቱ ደግሞ ዐቂዳዊም ሆነ አሕካማዊ ጉዳዮችን ያጠቃልላል።» "መጅሙዑል ፈታዋ" (3/229)

ሸይኽል ኢስላም እዚህ ንግግሩ ላይ ዑዝር የማይሰጥባትን አንዲትንም መስአላ ሳያስቀር፤ በማንኛውም የዲኑ ክፍሎች ዑዝር ቢል ጀህል መኖሩን ገልፆል፤ መስአላ ያሂራ በሆነ ሺርክ ላይ ዑዝር መኖሩን የማያይ ቢሆን ኖሮ፤ ትክክለኛ አቋሙንና በሙኻሊፎች ላይ ሑክም ሲሰጥ የሚከተለውን መሰረታዊ መርሁን የገለፀበት እንዲህ አይነት ወሳኝ የሆነ ቦታ ላይ "መስአላ ያሂራና ሺርካዊ ጉዳይ ሲቀር በሌሎች መሳኢሎች ዑዝር አለ፤ በመስአላ ያሂራ ግን የለም" በማለት ከጥቅል ሑክሙ ያወጣቸው ነበር፤ ነገር ግን አላደረገውም።

ስለዚህ ሸይኽል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ ከዚህ ካረጋገጠው ጥቅል ብይን ላይ መስአላ ያሂራ ትወጣለች የሚል እይታ የለውም ማለት ነው።

በመስአለተል ዑዝር ቢልጀህል ላይ የኢብኑ ተይሚያን አቋም ተሕሪር እናደርጋለን በማለት ጥናታዊ ፅሁፍን የፃፉ አንዳንድ አካላት እነዚህን ንጥር ብጥር ያሉ የሸይኽል ኢስላምን ግልፅ ንግግሮች ተሕሪር የሚሉት መጣጥፋቸው ላይ ባላየ ማለፋቸው በጣም አድርጎ የሚገርም ነው!!

“ሐረከት ሐማስ” ከምትባለው የዳዒሽ፣ የአል ቃዒዳ፣ የራፊዲ፣ የኢኽዋኒያ፣ የሱፊያ፣፣፣ ጥርቅም ከሆነችዋ አንጃ ዲፋዕ እንደሚያደርግ ዩሱፍ አልጀዛኢሪ የተናገረበት፤ "ዓሪዱል ጀህል" እና "ደዋቢጡ ተከፊይሪል መዐየን" የተባሉ ኪታቦችን የፃፈው አቡል ዑላ አር ራሺድ የሸይኹን ንግግሮች ባላየ ከሚያልፉት አንዱ ነው፤ ይባስ ብሎ በኢስቲጃሣ ቢሻይሪላህና በመሳሰሉ ግልፅ በሆኑ የሺርክ ተግባራት ላይ ሸይኹ ዑዝር የማይሰጥ መሆኑን በመደምደም፤ በጉዳዩ መረጃ ይሆኑኛል ብሎ የገመታቸውን የሸይኹን ንግግሮች ጠቅሶ፤ በመሳኢል ያሂራ

ሳይቀር ዑዝር እንዳለ የሚናገርባቸውን የኢብኑ ተይሚያን ንግግሮች ግን ምንም አለመጥቀሱ ልብ ያለው ሰው ትዝብት ይወስድበታል!!

ሰውየው የሸይኹን አቋም እውነተኛ ተሕሪር አድራጊ ቢሆን ኖሮ "ረድ" ለማድረግ ወይም ሙኻሊፎቹ የሚያመጧቸውን የሸይኹን ፈታዋዎች ተውጂህ ለመስጠት በሚል እንኳ ንግግሮቹን ማውሳት ነበረበት። ላኪ፦ አል ሀዋ፤ አላደረገውም።

ፍትሃዊ የሆነ ባሒሥ ወይም ሙሐሪር ሊቃረኑኝ ይችላሉ የሚላቸውን የሙኻሊፎቹን ንግግሮች ይጠቅሳል፤ እሱ መረጃ ይሁኑኛል ከሚላቸው ንግግሮች ጋር ለማስማማት ወይም ተውጂህ ለመስጠትም ይጥራል። ካልሆነ ግን ኢብኑ ተይሚያ በመሳኢል ዚሂራ ላይ ዑዝር የማይሰጥ መሆኑን የሚያስገነዝቡ ንግግሮች እንጂ ከዚህ ውጭ በእነኚሁ መሳኢሎች ላይ ዑዝር መስጠቱን በግልፅ የሚጠቁሙ ሌሎች በርካታ ንግግሮች የሌሉት መሆኑን ለአንባቢዎች ጎዶሎ የሆነ እውቀት ማስጨበጥ ነው የሚሆንበት። ታድያ የኢብኑ ተይሚያን አቋም ተሕሪር አድራጊነቱ ምን ላይ ነው!?

ምንም እንኳ ዛሬ ላይ ቢሸውዱለትም ነገ ወይም ከነገ ወዲያ ዒልሚይ የሆነ ጥናታዊ ፅሁፍ ተብየው ምን ያህል በጎዶሎነት፣ በኺያና ዒልሚያና በተድሊስ የታጨቀ መሆኑ ለአንባቢያን ይገለፅላቸዋል።

②ኛ መስአላውን ወደ ሸይኽል ኢስላም ማስጠጋት ትክክል ያልሆነበት ሁለተኛው ምክንያት፦ መስአላ ዚሂራና ኽፊያ በሚለው ዙሪያ የተፃፈው ያለፈው ፅሁፍ ላይ እንደተመለከትነው፤ እሱ ራሱ ግልፅነትና ድብቅነት ከሰው ሰውና ከቦታ ቦታ የሚለያይ ኒስቢይ የሆነ ጉዳይ መሆኑንና ይህ ኒስቢይነት መሰረታዊ የሆኑትንም ሆነ መሰረታዊ ያልሆኑትን የዲኑን ክፍሎች ባጠቃላይ የሚጠቀልል መሆኑን ስለገለፀ ነው።

③ኛ ኢብኑ ተይሚያ ሰዎች ላይ በኩፍር መሐከምን በመስአላዋ ግልፅነት ላይ የተንጠለጠለ ወይም ያጠረ ነገር አድርጎ አይቆጥረውም፤ ይልቁንም ሑጃው በመድረሱ ላይ ያጠረ መሆኑን ነው ሁልጊዜ ደጋግሞ የሚገልፀው። ቀጥሎም መሳኢል ዚሂራ የሚባሉትን እንደምሳሌ ይጠቅሳቸዋል። ለምሳሌ ያህል፦

የሶላትና የዘካን ዋጅብነት የካደ ወይም የተቃወመ ሰው ሑጃ እስካልቆመበት ድረስ የማይከፈር መሆኑን እንዲህ ሲል ገልፆል፦

وأما الفرائض الأربع؛ فإذا جحد وجوبَ شيءٍ منها بعد بلوغ الحجة فهو كافرٌ، وكذلك من جحد تحريم شيء من المحرمات الظاهرة المتواتر تحريمها؛ كالفواحش

والظلم والكذب والخمر ونحو ذلك .وأما من لم تقم عليه الحجة مثل أن يكون حديث عهد بالإسلام أو نشأ ببادية بعيدة لم تبلغه فيها شرائع الإسلام ونحو ذلك، أو غلط فظن أن الذين آمنوا وعملوا الصالحات يستثنون من تحريم الخمر كما غلط في ذلك الذين استتابهم عمر ، وأمثال ذلك؛ فإنهم يستتابون وتقام الحجة عليهم، فإن أصروا كفروا حينئذ ولا يحكم بكفرهم قبل ذلك؛ كما لم يحكم الصحابة بكفر قدامة بن مظعون وأصحابه لما غلطوا فيما غلطوا فيه من التأويل

مجموع الفتاوى

:(7/609)

«ከአራቱ ኢስላማዊ ግዴታዎች የአንዱን ግዴታነት የተቃወመ ሰው ማስረጃ ከደረሰው በኋላ ካፊር ይሆናል። አፀያፊ ስራዎች፣ ዙልም፣ ውሸት፣ አስካሪ መጠጥና የመሳሰሉት ግልፅ የሆኑ የሐራም ተግባራትና ሐራምነታቸው ሙተዋቲር ወይም የተረጋገጠ ከሆኑ ነገሮች የአንድኛውን ሐራምነት የሚቃወም ሰውም እንዲሁ (ማስረጃ ከደረሰው በኋላ ካፊር ይደረጋል)። አዲስ የሰለመ በመሆኑ፤ ወይም ኢስላማዊ ህግጋቶች ሊደርሱት በማይችሉበት ራቅ ያለ መንደር ያደገ በመሆኑ፤ አሊያም በመሳሰሉት ሆኔታዎች ላይ ሆኖ መረጃ ያልቆመበት ሰው፤ ወይም ደግሞ ይህን አይነት ስህተት ፈፅመው ዑመር ረዲየላሁ ዐንሁ ተውበት እንዲያደርጉ እንደጠየቃቸው ሰዎች፤ እሱም በስህተት "የአስካሪ መጠጥ ሐራምነት እነዚያን ያመኑትንና መልካም ሰሪዎችን አያካትትም" የሚል እሳቤ ወይም ድምዳሜ ላይ የደረሰ ሰውና የመሳሰሉት አካላት፡- ተውበት እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ፤ ሑጃም እንዲቆምባቸው ይደረጋል፤ (መረጃው ደርሷቸው) በአቋማቸው ላይ የሚቀጥሉ ከሆነ ግን ካፊር ይደረጋሉ፤ ተውበትን ከመጠየቅና ሁጃ ከማድረስ በፊት ግን በካፊርነት አይተሓከምባቸውም፤ ቁዳመቱ ኢብኑ መዝዑንና ጓደኞቹ በዚህ አይነት ስህተት በተእዊል በተሳሳቱ ጊዜ ሶሓቦች እንዳላከፈሯቸው ሁሉ (እነኚህም ሰዎች ሑጃ ሳይደርሳቸው በፊት አይከፈሩም)። » "መጅሙዑል ፈታዋ" (7/609)

ኢብኑ ተይሚያ እዚህ ንግግሩ ላይ ሰውን ማክፈር የሚባለውን ጉዳይ በመረጃ መድረስ ላይ ነው ያንጠለጠለው ወይም ያሳጠረው። እሱ ዘንድ ሰውን ለማክፈር ወሳኙ መወጠኛውና ማሰሪያው የመስአላዎቹ ግልፅ መሆን ቢሆን ኖሮ እንዲህ አይልም ነበር።

የቁዳመቱ ኢብኑ መዝዑን ቂሷና የመሳሰሉት ኣሣሮች ላይ ደጋግሞ ጉዳዩን ኣጠንክሮ እንደሚያወሳው ሁሉ፤ ይህን አካሄዱን በሌሎች በርካታ ጉዳዮች ላይም ተመሳሳይ አካሄድን ነው የሚሄደው።

ኧረ እንደውም ሙስሊሞች መንደር ያደገ ወይም የኖረ ሰው ሑጃ የደረሰው መሆኑን በርግጠኝነት እስካላወቅን ድረስ የዲን መገንቢያ የሆኑትን አራቱን መሰረታዊ ነገሮች በመተዉና ባለመቀበሉ እንደማይከፈር የገለፀበትም ሁኔታ አለ።

ሸይኹ አራቱን ህግጋት የተቃወመን ሰው ሑክም ከጠቀሰና ዑዝር እንደሚሰጠውም ከገለፀ በኃላ እንዲህ አለ፦

فأما الناشئ بديار المسلمين ممَّن يُعْلَمُ أنه قد بلغتْهُ هذه الأحكام، فلا يُقْبَلُ قولهُ، أي لم أعلم ذلك" «شرح عمدة الفقه ـ شروط الصلاة

ص:51,لابن تيمية

«ሙስሊሞች የሚገኙባቸው መንደሮች ያደገ ወይም የሚኖር ግለሰብ፤ የእነዚህ ጉዳዮች ብይን በርግጠኝነት የደረሳቸው መሆኑን ከምናውቃቸው ሰዎች ሆኖ፤ "እኔ ስለማላውቅ ነው" ብሎ ምክንያት ቢያቀርብ ምክንያቱ ተቀባይነት የለውም።» "ሸርሑ ዑምደቲል ፊቅህ _ ሹሩጡሶላት" (ገፅ: 51)

ይህ የኢብኑ ተይሚያ ንግግር እሱ ዘንድ ግምት የሚገባው ሰውየው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሑጃውን አውቋል ወይስ አላወቀም የሚለው ብቻና ብቻ መሆኑን ይገልፅልናል።

በመሳኢል ዟሂራዎች ዑዝር ቢልጀህል መኖሩን የማያይ ቢሆን ኖሮ እዚህ ቦታ ላይ «የእነዚህ ጉዳዮች ብይን በርግጠኝነት የደረሳቸው መሆኑን ከምናውቃቸው ሰዎች ሆኖ» አይልም ነበር። እንደውም "ይህ ሰው በጭራሽ ዑዝር ቢልጀህል የማይሰጠው ካፊር ነው" ነበር ማለት የነበረበት፤ ነገር ግን አላለም። ኧረ እንደውም በተዋቱር ወይም በኢጅማዕ የታወቀና የተረጋገጠ የሆነን ነገር የተቃወመ ሰው ሑጃ ሳይቆምበት በፊት እንደማይከፍር እንዲህ በማለት ገልፆል፦

وأما مَن أنكر ما ثبت بالتواتر والإجماع فهو كافرٌ بعد قيام الحجة. مجموع الفتاوى (1/109)

«በኢጅማዕና በሙተዋቲር (ታማኝ ከሆኑ ምንጮች የተገኘን) የተረጋገጠ እውነታን የተቃወመ ሰው፡- ሑጃ ከቆመበት በኋላ ካፊር ይሆናል» "መጅሙዑል ፈታዋ" (1/109)

ስለዚህ እሱ ዘንድ ግምት የሚገባው የሑጃው መድረስ ብቻ ነው፤ መስአላዋ ሙተዋቲራም (ያሂራም) ትሁን ኸፊያ!!

ሀሳቡ ጠቅለል ሲል:

•እነኚህ ሁሉ የሸይኽል ኢስላም ንግግሮች አንድ ሰው ላይ በኩፍር ለመሐከም ግምት ውስጥ የሚገባው ነገር፡- ሰሪው ሰውዬ እውቀት የደረሰው መሆኑ ብቻ እንደሆነና የእውቀት አለመድረስ ሙስሊሞች መንደር ለሚኖሩ ሰዎችም ጭምር ሊከሰት እንደሚችል ይጠቁማሉ።

④ኛ ኢብኑ ተይሚያ ራሱ አንዳንድ መሳኢሎችን ያሂራ መሆናቸውንና እጅግ በጣም ግልፅ የኢስላም ተቃራኒ መሆናቸውን የገለፀ ከመሆኑ ጋር፤ በእነዚህ ወንጀሎች የወደቁ አንዳንድ ሰዎችን ባለማወቃቸው ምክንያት ዑዝር ሰጥቷቸዋል። መጀመሪያ ጀህሚያዎች የፈበረኳቸውን ቢድዓዎች "መጅሙዑል ፈታዋ" (12/485) ላይ እንዲህ ሲል ይገልፃቸዋል፡-

قَولُهُم صريحٌ في مُناقضة ما جاءتْ به الرسلُ مِن الكتاب، وحقيقةُ قولِهم جُحودُ الصانع، ففيه جحودُ الرب، وجحودُ ما أخبر به عن نفسه على لسان رُسُلِهِ

«ንግግራቸው መልእክተኞች ይዘው የመጡትን የአላህን መፅሀፍ ግልፅ የሆነ መቃረንን ይቃረነዋል፤ የንግግራቸው ሐቂቃ፡- ፈጣሪና የአለማት ጌታ በሆነው መካድን ያዘለ ነው፤ በመልእክተኞች አንደበት ስለራሱ የተናገረበትንም ሀቅ መካድንም የያዘ ነው»

እነሱ ዘንድ ስለሚገኙ ከባባድና ግልፅ ኩፍሪያት እንዲህ በማለት የገለፀ ሸይኽ፤ እሱ ራሱ እነኚሁ ጀህሚያዎች በጀህላቸው ምክንያት በተዕዪይን ወይም በተናጠል የማይከፈሩ መሆናቸውን "አል ኢስቲጃሠቱ ፊርረዲ ዐለል በከሪ" (2/494) የተሰኘው ኪታብ ላይ እንዲህ ሲል ገልፆል፡-

كنتُ أقول للجهمية مِن الحُلوليّة والنُّفاة الذين نفوْا أن يكون الله تعالى فوق العرش لمّا وقعت محنتُهم :أنا لو وافقتُكم كُنْتُ كافرًا؛ لأني أعلم أنَّ قولكم كفرٌ، وأنتم عندي

«لا تكفرون لأنكم جُهَّال، وكان هذا خطابًا لعلمائهم وقضاتهم وشيوخهم وأمرائهم "الاستغاثة في الرد على البكري"

(2/494)

«አላህን ሱብሓነሁ ወተዓላ በየቦታው አስፋሪዎች ለሆኑና ከዐርሽ በላይነቱን አውጋዥ ለሆኑት ጀህሚያዎች ፈተናቸው በተከሰተ ጊዜ እንዲህ እላቸው ነበር፡- እኔ እናንተ የምትሉት አይነት ንግግር ብናገር: ካፊር እሆን ነበር፤ ምክንያቱም የናንተ ንግግር ኩፍር መሆኑን ስለማውቅ። እናንተ ግን እኔ ዘንድ አትክፈሩም፤ ምክንያቱም የማታውቁ ጁሃል ናችሁና። ይህ ለዑለማኦቻቸው፣ ለቃዲዎቻቸው፣ ለመሻይኾቻቸውና ለሀገር መሪዎቻቸው እናገረው የነበረ ነው።» መጅሙዑል ፈታዋውም (12/489) ላይ ኢማሙ አሕመድ ኢብን ሐንበል ጀህሚያዎችን በተዕዩን የማያከፍር መሆኑንም አጠንክሮ ተናግሯል።

⑤ኛ ኢብኑ ተይሚያ ሰውን ለማከፈር አስፈላጊ የሆኑ ደዋቢጦችን የሚያወሳባቸው ንግግሮቹን የሚከታተል ወይም የሚያስተውል ሰው በመሳኢል ዚሂራና ኽፊያ መካከል ባለው መለያየት ሊፈጠር የሚችለውን ውጤት መጥቀስን ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል መልኩ ችላ ያለው ወይም ቦታ የማይሰጠው ሆኖ ነው የሚያገኘው።

ስንትና ስንት ቦታዎች ላይ የተከፈርን ደዋቢጦች እስከ መረጃቸው አውስቷል፤ ስንትና ስንት ቦታዎች ላይም ሹሩጦቹንና መዋኒዖቹን ጠቅሷል፤ ብዙ ቦታዎች ላይ የተከፈርን ምሳሌ ፕራክቲካሊ አሳይቷል፤ የሚያስከፍሩ ተግባራት ላይ የወደቁ በርካታ ጀማዓዎች መኖራቸውንም ተናግሯል፤ ይህ ከመሆኑ ጋር በእነዚህ ቦታዎች ላይ የመስአላዋን ዚሂራነት ወይም ኽፊይነት ምንም አይነት ሑክም የማያንጠለጥልባት ሆኖ ነው የሚታየው፤ በጀህል ወይም በተእዊል መስአላ ዚሂራ ላይ ዑዝር የሌለ መሆኑንም ሲያወሳ አይታይም።

ይህን ያህል ለጉዳዩ ቦታ አለመስጠቱና ችላ ማለቱ ነገርየው እሱ ዘንድ ለተከፈር ወሳኝ የሆነ ነገር እንዳልሆነ ይጠቁማል ማለት ነው። ይልቁንም በሰውየው ላይ ሑጃ መድረሱ ብቻና ብቻ ነው እሱ ዘንድ በጉዳዩ ወሳኝ የሆነው ነገር!!

***** ***** ***** *****

ኢብኑ ተይሚያ መስአላ ዚሂራና ኽፊያን ይለያያል በማለት የተደገፉባቸው ንግግሮቹ ተውጂህ ሲደረጉ

ሙስሊም ወንድሞቼ! በዛሬው ፅሁፍ ኢንሻአላህ ተከፊሪዮችና መሰሎቻቸው ኢብኑ ተይሚያ መስአላ ያዚራና ኸፊያን ይለያያል በማለት የተደገፉባቸው ንግግሮቹን "ኢሽካሊየቱል ኢዕዛር ቢልጀህል" የተሰኘው ኪታብ ባለቤት የሆነው (ሱዑዲያዊው ዶክተር ሱልጧን አል ዑመይሪ) በምን መልኩ ተውጂህ እንዳደረጋቸው እንመለከታለን።

ሸይኽል ኢስላም ይለያያል በሚል የተደገፉባቸው ንግግሮቹ እነሱ የተገነዘቡትን ነገር በግልፅ አይጠቁሙም። ይህ ሲተነተንም እንደሚከተለው ይገለፃል፡-

ቀጣዩ ንግግር ሙኻሊፎች ከሚንጠለጠሉባቸው የሸይኹ ንግግሮች የመጀመሪያው ነው፡-

وهذا إذا كان في المقالات الخفية فقد يُقال إنه فيها مخطئ ضال لم تقم عليه الحجة التي يكفر صاحبها، لكن ذلك يقع في طوائف منهم في الأمور الظاهرة التي يعلم الخاصة والعامة من المسلمين أنها من دين المسلمين، بل اليهود والنصارى والمشركون يعلمون أن محمدًا ﷺ بُعث بها، وكفَّر من خالفها؛ مثل أمره بعبادة الله وحده لا شريك له، ونهيه عن عبادة أحد سوى الله :من الملائكة والنبيين والشمس والقمر والكواكب والأصنام وغيرهم، فإن هذا أظهر شعائر الإسلام، ومثل أمره بالصلوات الخمس وإيجابه لها، وتعظيم شأنها، ومثل معاداة اليهود والنصارى والمشركين، ومثل تحريم الفواحش والربا والخمر والميسر ونحو ذلك .ثم تجد كثيرا من رؤسائهم وقعوا في هذه الأمور فكانوا مُرْتَدِّين

(مجموع الفتاوى 4/54)

«ይህም ድብቅ በሆኑ ንግግሮች ነው፤ (አንድ ሰው በነዚህ ላይ ቢወድቅ)፡- ባለቤቷ የሚከፍርባት ሑጃ ያልደረሰችው፣ ጥመት ላይ የወደቀና የተሳሳት ሰው ሊባል ይችላል፤ ነገር ግን ከኢስላማዊ ጉዳዮች መሆናቸውን አዋቂዎቹም ብዙሃኖቹም የሚያውቁት በሆኑና ግልፅ የሆኑ ነገሮች ላይ ከእነሱ መካከል አንዳንዶች ዘንድ ይህ ጥፋት ሊከሰት ይችላል፤ ኧረ እንደውም ነቢዩ ሙሐመድ ﷺ የተላኩበትና የተቃረነውም ሰው የሚከፈርበት ጉዳይ መሆኑን አይሁዶች፣ ክርስቲያኖችና ሙሽሪኮችም ጭምር የሚያውቁት በሆነ ነገር፤ ለምሳሌ፡- አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ ያለ ተጋሪ ብቻውን እንዲመለክ ማዘዛቸው፤ መላእክት፣ ነቢያት፣ ፀሀይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ ጣኦታትና ሌሎችም አካላት ከአላህ ውጪ እንዳይመለኩ መከልከላቸው፤ እነዚህና የመሳሰሉት በጣም ግልፅ የሆኑ የኢስላም

መገለጫዎች ናቸው። በአምስት አውቃት ሶላቶችም ማዘዛቸው፣ ግድ ማድረጋቸውና ደረጃዎቿንም ከፍ ማድረጋቸው እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ። እንዲሁም አይሁዶች፣ ክርስቲያኖችና ሙሽሪኮች ጠላት ተደርገው መጾዝ እንዳለባቸው፤ ፀያፍ ተግባራት፣ ወለድ፣ አስካሪ መጠጥ፣ ቁማርና የመሳሰሉት ነገሮች ሐራም መሆናቸው (ግልፅ ከሆኑ የኢስላማዊ ጉዳዮች መሆናቸው በግልፅ የሚታወቁ ነገሮች ናቸው።) ከእነዚያ የቢድዓ ሰዎች ዋና ዋናዎቹ እነዚህን ግልፅ የሆኑ ነገሮች ተቃርነው ኩፍር ውስጥ በመውደቅ ሙርተዶች ሆነዋል።» (መጅሙዑል ፈታዋ: 4/54)

ይህ የሸይኽል ኢስላም ንግግር መሳኢል ዟሂራንና ኽፊያን መለያየትን ወደሱ የሚያስጠጉ አካላት በዋነኝነት ከሚደገፉባቸው ንግግሮቹ አንዱ ነው።

ሆኖም ንግግሩ መስአላ ዟሂራንና ኽፊያን መለያየት በዐዝር ቢልጀህል ጉዳይ ላይ ግምት ውስጥ የሚገባ መሆኑን በጭራሽ አያመላክትም። ይህም ከሁለት ምክንያቶች በመነሳት ነው።

•[1]• የንግግሩን "ሲያቅ" ወይም አጎባብ አስተውሎ የሚመለከት ሰው፡- ኢብን ተይሚያ ይህን ሲል በጀህል ዐዝር ለመስጠት መስአላ ዟሂራና ኽፊያ ተለያይተው መታየት ያለባቸው መሆኑን ሊያፀድቅ እንዳልሆነ ይገነዘባል። የሚልመል ከላም አኢማዎች ላይ ሑክምን በተዕዪይን ወይም በተናጠል ለመሐከምም የተናገረው አይደለም። ይልቁንም ይህ አባባሉ የቢድዓና የከላም ሰዎች ትልልቅ ሽሪዓዊ ሙኻለፋት ውስጥ የሚወድቁ መሆናቸውን የሚገልፅበት ሲያቅ ነው። ሊከፍርበት የሚችል ንግግር ያለው ቢሆን እንጂ ከአኢማዎቻቸው አንድም ኢማም የሌለ መሆኑን ሸይኽል ኢስላም አውስቷል። ይህ አይነቱን ገለፃ ከኪታቦቹ በርካታ ቦታዎች ላይ የተጠቀመው ገለፃ ነው። ከዚያም የሚልመል ከላም አኢማዎች የወደቁባቸው ኩፍሪያቶች ድብቅ የሆኑ ነገሮች አለመሆናቸውን ጠቀሰ፤ በነሱ ቢሆን ኖሮ ጉዳዩ ቀለል ይል ነበር። የነገሮቹን ሑክም ለማወቅ ስላልቻሉም ዐዝር ይሰጣቸዋል እጎል ነበር። ነገር ግን እነኚህ ኩፍሪያቶች የሁዳዎችና ነሷራዎች እንኳ ሳይቀሩ ለአላህ ዲን ተቃራኒነታቸውን እያንዳንዱ ሰው የሚያውቃቸው ግልፅ የሆኑ ነገሮች ናቸው አለ። ኢብኑ ተይሚያ ይህን ንግግሩን የፈለገበት የአኢማዎቹን ሁኔታና በዲኑ ላይ ያላቸው ጀህል ግልፅ የሆኑ የዲኑን ክፍሎች እስከመቃረን ድረስ እንዳደረሳቸው ለመግለፅና የአህሉስ ሱናዎች ሁኔታ ከእነዚህ አካላቶች ሁኔታ የተሻለ መሆኑን ለመግለፅ ብቻ ነው። እንጂ መሳኢሎችን ዟሂራና ኽፊያ በሚል ለመለያየት ወይም ሰዎቹ ላይ በኩፍር የሐከመበትን ሰበብ ለመሐደድ ወይም ለመወሰን አይደለም።

የንግግሩ "ሲያቅ" ወይም የፊትና የኋላው አገባብም ይህንኑ ነው የሚጠቁመው።
ምክንያቱም ላይ ካሳለፍነው ንግግሩ በስተፊት እንዲህ ብሏልና፡-

المخالفون لأهل الحديث هم مظنة فساد الأعمال :إما عن سوء عقيدة ونفاق وإما عن مرض في القلب وضعف إيمان .ففيهم مِن ترك الواجبات واعتداء الحدود والاستخفاف بالحقوق وقسوة القلب ما هو ظاهر لكل أحد، وعامة شيوخهم يرمون بالعظائم وإن كان فيهم من هو معروف بزهد وعبادة ففي زهد بعض العامة من أهل السنة وعبادته ما هو أرجح مما هو فيه .

ومن المعلوم أن العلم أصل العمل، وصحة الأصول توجب صحة الفروع، والرجل لا يصدر عنه فساد العمل إلا لشيئين :إما الحاجة، وإما الجهل فأما العالم بقبح الشيء الغني عنه فلا يفعله اللهم إلا من غلب هواه عقله واستولت عليه المعاصي فذاك لونٌ آخر وضربٌ ثانٍ

وأيضا فإنه لا يعرف من أهل الكلام أحد إلا وله في الإسلام مقالة يكفر قائلها عموم المسلمين حتى أصحابه وفي التعميم ما يغني عن التعيين فأي فريقٍ أحقّ بالحشو والضلال من هؤلاء ؟ وذلك يقتضي وجود الردة فيهم كما يوجد النفاق فيهم كثيرا وهذا إذا كان في المقالات الخفية فقد يقال :إنه فيها مخطئ ضال لم تقم عليه الحجة. التي يكفر صاحبها ;لكن ذلك يقع في طوائف منهم في الأمور الظاهرة التي تعلم العامة والخاصة من المسلمين أنها من دين المسلمين، بل اليهود والنصارى يعلمون :أن محمدا صلى الله عليه وسلم بعث بها وكفر مخالفها، مثل أمره بعبادة الله وحده لا شريك له ونهيه عن عبادة أحد سوى الله من الملائكة والنبيين والشمس والقمر والكواكب والأصنام وغير ذلك؛ فإن هذا أظهر شعائر الإسلام ومثل أمره بالصلوات الخمس وإيجابه لها وتعظيم شأنها ومثل معاداته لليهود والنصارى والمشركين والصابئين والمجوس ومثل تحريم الفواحش والربا والخمر والميسر ونحو ذلك .

ثم تجد كثيرا من رؤسائهم وقعوا في هذه الأمور فكانوا مرتدين، وإن كانوا قد يتوبون من ذلك، ويتوبون إلى الإسلام

«የአህሉል ሐዲሥ ተቃራኒ የሆኑ አካላት ወይ በመጥፎ እምነትና ኒፋቅ፣ ወይም ደግሞ ልቦናቸው ውስጥ ባለ በሽታና የኢማን ድክመት የተነሳ የብልሹ ተግባራት መገኛ ናቸው፤ እላያቸው ላይ የሚገኘው፡- ዋጂባቶችን መተው፤ ክልከላዎችን መተላለፍ፤ ሑቁውቆችን አቅልሎ ማየትና የልብ መድረቅ ማንኛውም ሰው በገሃድ

የሚያየው ነገር ነው። ብዙዎቹ መሻዪኾቻቸው በከባባድ ነገሮች ይወርረፋሉ፤ ከመካከላቸው በዙህድ እና በዒባዳ የሚታወቅ ቢኖርም፤ ከእነሱ ይልቅ ከአህሉስ ሱናዎች መካከል ተራ ከሆኑት ሰዎች ውስጥ የአንዳንዱ ዙህድ እና ዒባዳ የተሻለ ነው። እውቀት የተግባር መሰረት መሆኑ የሚታወቅ ነገር ነው፤ የመሰረቶች መስተካከልም የቅርንጫፎችን መስተካከል የሚያስከትል መሆኑም ይታወቃል። ከአንድ ሰው ብልሹ የሆነ ተግባር የሚገኘው ወይ መስራቱን ስለፈለገው ነው አሊያም ብልሹነቱን ስላላወቀው ነው። የአንድን ነገር መጥፎነት አዋቂ የሆነና ለመፈፀም ፍላጎቱ የሌለው ሰው ይህን መጥፎ ነገር አይሰራውም። ምናልባት ህሊናውን ስሜቱ ያሸነፈበትና ወንጀሎች የተቆጣጠሩት ሰው ብልሹውን ተግባር ሊፈፅመው ይችል ይሆናል፤ ይህ ግን ሌላ ጉዳይ ነው። በተጨማሪ ከአህሉል ከላሞች፡- ተከታዮቹን ጨምሮ ሙስሊሞችን ባጠቃላይ የሚያከፍርበት ንግግር የተናገረ ቢሆን እንጂ (ከዚህ የፀዳ እውስጣቸው) አንድም ሰው አይታወቅም። በጥቅል የሚነገረው ንግግር በዝርዝር ወይም በተዕዪይን ከሚወሳው የሚያብቃቃ ሀሳብን ይዟል። ታዲያ ከእነሱ የበለጠ ለሐሸውና ለጥመት የተገባ ማን አለ?! ይህ ባህሪያቸው እውስጣቸው "ኒፋቅ" በብዛት እንዳለ ሁሉ "ሪድዳህ" መኖሩንም ያስይዛል። ይህም ድብቅ በሆኑ ንግግሮች ነው፤ (አንድ ሰው በነዚህ ላይ ቢወድቅ)፡- ባለቢቷ የሚከፍርባት ሑጃ ያልደረሰችው፣ ጥመት ላይ የወደቀና የተሳሳት ሰው ሊባል ይችላል፤ ነገር ግን ከኢስላማዊ ጉዳዮች መሆናቸውን አዋቂዎቹም ብዙሃኖቹም የሚያውቁት በሆኑና ግልፅ የሆኑ ነገሮች ላይ ከእነሱ መካከል አንዳንዶች ዘንድ ይህ ጥፋት ሊከሰት ይችላል፤ ኧረ እንደውም ነቢዩ ሙሐመድ ﷺ የተላኩበትና የተቃረነውም ሰው የሚከፈርበት ጉዳይ መሆኑን አይሁዶች፣ ክርስቲያኖችና ሙሽሪኮችም ጭምር የሚያውቁት በሆነ ነገር፤ ለምሳሌ፡- አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ ያለ ተጋሪ ብቻውን እንዲመለክ ማዘዛቸው፤ መላእክት፣ ነቢያት፣ ፀሀይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ ጣኦታትና ሌሎችም አካላት ከአላህ ውጪ እንዳይመለኩ መከልከላቸው፤ እነዚህና የመሳሰሉት በጣም ግልፅ የሆኑ የኢስላም መገለጫዎች ናቸው። በአምስት አውቃት ሶላቶችም ማዘዛቸው፣ ግድ ማድረጋቸውና ደረጃዎቿንም ከፍ ማድረጋቸው እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ። እንዲሁም አይሁዶች፣ ክርስቲያኖችና ሙሽሪኮች ጠላት ተደርገው መያዝ እንዳለባቸው፤ ፀያፍ ተግባራት፣ ወለድ፣ አስካሪ መጠጥ፣ ቁማርና የመሳሰሉት ነገሮች ሐራም መሆናቸው (ግልፅ ከሆኑ የኢስላማዊ ጉዳዮች መሆናቸው በግልፅ የሚታወቁ ነገሮች ናቸው።) ከእነዚያ የቢድዓ ሰዎች ዋና ዋናዎቹ እነዚህን ግልፅ የሆኑ ነገሮች ተቃርነው ኩፍር ውስጥ በመውደቅ ሙርተዶች ሆነዋል። ከጥፋታቸው ቶበተው ወደ ኢስላም ሊመለሱም ይችላሉ»

ኢብኑ ተይሚያ እዚህ ንግግሩ ላይ በመሳኢል ያሂራ ዑዝር ቢልጀህል የለም ለማለት ፈልጎ አይደለም፤ ወይም ደግሞ እነዚህ ሰዎች ሙርተድ የሆኑበት ምክንያት መሳኢል ያሂራን በመቃረናቸው ብቻ ነው ለማለትም አይደለም። ይልቁንም ሁኔታቸውንና ለአላህ ዲን ያላቸውን መቃረን ሊገልፅ ፈልጎ ነው ይህን የተናገረው።

ይህን ነው የንግግሩ ሲያቅ የሚያመላክተው፤ ስለዚህ መሳኢል ያሂራና መሳኢል ኽፊያን ለመለያየት ይህን መሰል በሆኑ ንግግሮቹ ላይ መንጠልጠልና በጉዳዩ ትክክለኛ አቋሙን በግልፅ የሚጠቁሙ ንግግሮቹን መተው ትክክል አይሆንም።

ለዚህ አይነት አገላለፁ ሌላ ተመሳሳይ ምሳሌ ከተፈለገ "በያን ተልቢስ አልጀህሚያ" (3/472) የተሰኘው ኪታቡ ላይ የተናገረውን ማየት ይቻላል።

•²• ኢብኑ ተይሚያ እዚህ ያወሳቸውን የሚልመል ከላም ሰዎችን በተዕዪይን የኩፍርን ሑክም በይኖባቸዋል የሚለውን ሀሳብ "ኢፍቲራደን" መላምታዊ በሆነ መንገድ (ወርደን) እንቀበለው እንበልና፤ ኢፍቲራደን ብንቀበለውም፤ ሰዎቹ ላይ በኩፍር የሐከመባቸው በእነዚህና በመሳሰሉት መሳኢሎች ላይ ዑዝር ቢልጀህል የለም ስለሚል አይደለም።

ይልቁንም የማያውቁ ጃሂሎች መሆናቸው የማይታሰብና በጉዳዩ የመጡ መረጃዎችንና የዑለማኦችን ንግግሮች በዝርዝር እውቀቱ ያላቸው የሆኑ እነኚህ አይነት ሰዎች በጀህል ዑዝር ስለማይሰጣቸው በኩፍር ሐክሞባቸዋል፤ ወይም ሰዎቹ ላይ የተከፊር ሹሩጦች ተሟልተው መገኘታቸውና ከልካዮቹም መወገዳቸው እሱ ዘንድ ስለተረጋገጠና እንዲህ አይነት ሰዎችን በተዕዪይን ማከፊር ስለሚቻል አክፍሯቸዋል እንላለን።

ስለዚህ ሰዎቹን ያከፈራቸው፡- ሹሩጦች በመሟላታቸውና ከልካዮቹም በመወገዳቸው ምክንያት እንጂ በእነዚህ መሳኢሎች ሙሉ በሙሉ በጀህል ዑዝር መስጠትን የማያይ ሆኖ አይደለም ማለት ነው።

ይህ አይነቱ አገላለፅ ኢብኑ ተይሚያ የኢማሙ አሕመድን ንግግሮች ሲገነዘብ የተጠቀመው አገላለፅ ነው።

ኢማሙ አሕመድ "ቁርአንን መኽሉቅ ያለ ሰው ካፊር ነው" ማለቱ በአሠር ተወርቷል። ከመሆኑም ጋር ይህን ንግግር የተናገረ ጀህሚይን ሁሉ በተዕዪይን እንደማያከፍር ግልፅ የሆኑ ንግግሮች አሉት። አንዳንድ ጀህሚዮችን በተዕዪይን ያከፈረበት ንግግርም ከእሱው ነቅል ሆኖ ተወርቷል። ኢብኑ ተይሚያ ይህ

አይነቱን የኢማሙ አሕመድን ሑክም በሚከተለው መልኩ ነው ሀሳቡን ተገንዝቦ የገለፀው:

"ኢማም አሕመድ አንዳንዶችን በተዕዪይን ያከፈረው ለማከፈር የሚያስችሉ ሹሩጦች ስለተሟሉባቸውና ከልካዮቹም ከሰዎቹ ላይ ስለተወገዱ ነው" በሚል ግንዛቤ ነበር የገለፀው። እንጂ ከኢማም አሕመድ ብይን ቁርአን መኽሉቅ ነው በሚለው ንግግር በተዕዪይን ዑዝር የማይሰጥ መሆኑን አልተገነዘበም።

ምክንያቱም እራሱ ኢብኑ ተይሚያ "መጅሙዑል ፈታዋ" (12/489) ላይ እንዲህ ብሏልና፡-

وقد نُقِلَ عن أحمد ما يدلُّ على أنه كَفَّر به قومًا مُعَيَّنِين .فأما أن يُذْكَرَ عنه في المسألة روايتان ففيه نظرٌ، أو يُحْمَلُ الأمرُ على التفصيل؛ فيقال :مَن كَفَّره بعينه، فَلِقِيام الدليل على أنَّه وُجِدَتْ فيه شروط التكفير وانتفتْ موانعه، ومَن لم يُكَفِّر بعينه فَلِانْتِفاء ذلك في حقِّه

«የጀህሚያዎችን ንግግር የሚናገሩ የተወሰኑ ሰዎችን በተዕዪይን ያከፈራቸው መሆኑን የሚያመላክት ወሬ በርግጥ ከአሕመድ ተዘግቧልኝ፤ በዚህ ጉዳይ (ሁለት አይነት አቋም እንዳለው ተደርጎ በሚታሰብ መልኩ) ሁለት አይነት ዘገባዎች ከእሱ መውሳቱ፤ ይህ ችግር አለበት (ትክክል አይደለም)። ወይም ደግሞ በተፍሲል ለያይተን ልናየው ይገባል፤ ማለትም፡- በተዕዪይን ያከፈረው ሰው ሹሩጦች መሟላታቸውንና መዋኒዖች መወገዳቸውን የሚጠቁም መረጃ ስለተገኘበት ነው ይባላልኝ፤ በተዕዪይን ያላከፈረው ሰው ደግሞ መስፈርቶቹ ስላልተሟሉበትና ከልካዮቹ ከላዩ ላይ ስላልተወገዱ ነው ይባላል ማለት ነው»

***** ***** ***** *****

መኻሊፎች ከተደገፉባቸው የኢብኑ ተይሚያ ንግግሮች ሁለተኛው ይህ የሚከተለው ነው፡-

وفي الحقيقة فكلُّ ردٍّ لِخبر الله أو أمره فهو كُفْرٌ دقَّ أو جلَّ لكن قد يُعْفَى عما خفيتْ فيه طُرقُ العلم، وكان أمرا يسيرا في الفروع .بخلاف ما ظهر أمرُه، وكان مِن دعائم الدين من الأخبار والأوامر

(الدرر السنية 10/388)

«እውነታው ሲታይ የአላህን ንግግር ወይም ትእዛዝ መመለስ ወይም አለመቀበል መጠኑ ትንሽም ይሁን ትልቅ፡- ኩፍር ነው። ነገር ግን ስለዚያ ነገር ማወቂያ መንገዶቹ ሊደበቁበት የሚችልን ጉዳይ (ቢመልስ) ይቅር ሊባል ይችላል። ቅርንጫፋዊና ቀላል ጉዳይም ከሆነ እንዲሁ። ይህም ከአላህ ንግግሮችና ትእዛዛቶች የሆኑ ግልፅ የኢስላም መሰረቶች ከሆኑት በተቃራኒ ማለት ነው።» (አድ ዱረር አስ ሰኒያ: 10/388)

ይህም እንደ ፊተኛው፡- ሙኻሊፎች የተገነዘቡትን አይጠቁምም። ኧረ እንደውም ዚሂራና ኸፊያን ይለያያል በሚል ንግግሩን ወደ ኢብኑ ተይሚያ አስጠግቶ መደገፍ ከበድ ያለ ችግር አለበት።

ችግሩም በሚከተሉት ምክንያቶች ይብራራል፡-

① የንግግሩ ምንጭ ተደርጎ የተጠቀሰው ኪታብ ላይ ይህ አባባል አለመኖሩ ነው። የነጅዱ ዓሊም ሸይኽ አቡ ቡጠይን እንደሚለው ንግግሩ "ሸርሑል ዐምዳ" የተሰኘው የሸይኽል ኢስላም ኪታብ ላይ ስለ ታሪከሰላት ኩፍር የሚናገርበት ውስጥ ተወስቷል። ወደዚህ ቦታ ስንመለስ ግን ኢብኑ ተይሚያ ንግግሩን ያላወሳው ሆኖ ነው የምናገኘው።

ሰርች ማድረጊያ በሆኑ በራሚጆች ለመታገዝ ብሞክርም ኢብኑ ተይሚያ ንግግር ውስጥ መገኘቱን የሚያረጋግጥልኝ ውጤት አላገኘሁም። ይህ ሁኔታ እንግዲህ ንግግሩ የኢብኑ ተይሚያ ነው ብለን ድምዳሜ ላይ እንዳንደርስ አስገዳጅ የሆነ ምክንያት ነው ማለት ነው።

ታዲያ የንግግሮቹ ሲያቅ (የፊትና ኋላ አገባባቸው) ግልፅ በሆነ መልኩ በጀህል ዑዝር መኖሩንና አንድ ሰው ሺርክ ወይም ኩፍር ውስጥ ቢወድቅ ሑጃ ካልደረሰው በስተቀር ካፊር እንደማይደረግ የተናገረባቸው ግልፅና የማያሻሙ ንግግሮቹን ትቼ ፊትና ኋላው የማይታወቅ በሆነና ለጉዳዩም ግልፅ የሆነ አመላካችነት በሌለው ንግግር ላይ ለመንጠልጠል እንዴት ይቻለኛል!?

② ይህ ንግግር ሀሳቡ ያልተሟላና መጨረሻውም ላይ ጉድለት ያለው በመሆኑ ነው። ይልቁንም ሸይኽ አቡ ቡጠይን ነው :-

«يعني: فإنه لا يقال قد يعفى عنه»

«ይህ ከሆነ ይቅርታ ይደረግለታል አይባልም ማለቱ ነው» በሚል ያሟላው። ሆኖም ይህ የአቡ ቡጠይን ማሟያ፡- ደሊል የሌለው ማሟያ ነው።

فلماذا لا يكون الإكمال هو:«بخلاف ما ظهر أمره، وكان من دعائم الدين من الأخبار والأوامر فإنه لا يعذر فيه إلا من علمنا جهله

أو يكون الإكمال «فإنه لا يعذر فيها كل من ادعى الجهل بها، بل لا بد أن يحتاط فيها أو نحو ذلك من العبارات التي تدل على الإعذار، فما الذي يرجح ذلك الإكمال على هذا الإكمال؟

ሀሳቡ ለምን በዚህ በቀጣዩ አባባል አይሟላም!?

«ግልፅ ከሆኑ ከአላህ ንግግሮችና ትእዛዛቶች የዲኑ መሰረቶች ከሆኑት በተቃራኒ፤ በነዚህ ነገሮች ላይ ግን ጃሂልነቱን የምናውቀው የሆነ ሰው ካልሆነ በስተቀር ዑዝር አይሰጠውም»

ወይም ደግሞ፡-

«ስላላወቅኩ ነው እያለ ጅህልናን ለሞገተ ሰው ሁሉ በእነዚህ ነገሮች ዑዝር አይሰጥም፤ ይልቁንም ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ ነው ሊሰጠው ወይም ላይሰጠው የሚጎሳው»

ወይም በነዚህንና በመሳሰሉት በጀህል ዑዝር እንዳለ በሚጠቁሙ ማሟያዎች ቢሟላ ምን ችግር አለ!? ያን የአቡ ቡጠይንን ማሟያ ከነዚህ ማሟያዎች የሚረጅህው ወይም ይበልጥ ሚዛን ደፊ የሚያደርገው ምክንያት ምንድን ነው?!

③ ይህ ንግግር እነሱ የተገነዘቡትን ሀሳብ በተሟላ መልኩ አይጠቁምም፤ ይልቁንም ከተገነዘቡት ሀሳብ ጋር ሙሉ በሙሉ ይቃረናል። ንግግሩ እንደሚያረጋግጠው፡- በጀህል ዑዝር የሚኖረው ድብቅ በሆኑ ነገሮች፣ ቀላል በሆኑና ቅርንጫፋዊ በሆኑ የዲኑ ክፍሎች ብቻ መሆኑን ነው። እነኚህ ሙኻሊፎች መስአላ ኸፊያ የሚሏቸው ነገሮች ደግሞ፡- ቀላልና ቅርንጫፋዊ የሆኑ የዲኑ ክፍሎች አይደሉም። ይልቁም ከዚህ በላይ የሚሰፉና የሚለጠጡ ናቸው።

ምክንያቱም መሳኢል ኸፊያዎች እነሱ ዘንድ፡- ኢስቲዋእ፣ ሩእየቱላህና የመሳሰሉ ከአላህ ሲፋቶች ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ የሚከሰቱ ቢድዓዎችን እንዲሁም የሙርጂአዎችን፣ የኸዋሪጆችን፣ የቀደሪያዎችንና የሌሎች አህሉል አህዋአችን፡- ቢድዓዎች ጭምር የሚያካትት ነው። [የአቡል ዑላ አርራሺድን "ደዋቢጡ ተክፊር አል ሙዐየን:43" እና "አድ ዱረር አስ ሰኒያ" (10/433) ላይ የነጅድ ዑለማአችን ንግግር ተመልከት።]

ታዲያ ንግግሩ በእነዚህ ነገሮች ላይ ዑዝር ቢልጀህል መኖሩን ይጠቁማል ይሉ ዘንድ፡- እነኚህ ቢድዓዎች ቀላልና ቅርንጫፋዊ በሆኑ የዲን ክፍሎች ላይ የተከሰቱ ቢድዓዎች ናቸውን!?

የዚህን ንግግር ሀሳብ በደፈናው ብንወስደው፡- የኢብኑ ተይሚያን ንግግር ለመገንዘብ በዚህ ንግግር ላይ የሚደገፉ ሰዎች ለሚቀርፉት (ለሚያረጋግጡት) ሀሳብ ተቃራኒ የሆነን ነገር የሚጠቁም ሆኖ ነው የምናገኘው። ምክንያቱም በንግግሩ ላይ የሚደገፍ ሰው፡- ከአላህ ሲፋቶች በሆኑት እንደ ሩእየቱላህና የመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ፤ እንዲሁም በመሳኢለል ኢማንና በመሳኢለል ቀደር ላይ ኢብኑ ተይሚያ ሙሉ በሙሉ ዑዝር የማይሰጥ መሆኑን ወደሱ ማስጠጋቱን ያስይዝበታልና። ይህ ደግሞ ኢብኑ ተይሚያ በነዚህ መሳኢሎች ዑዝር እንደሚሰጥ በግልፅ ከሚቀርርባቸው ሌሎች በርካታ ንግግሮቹ ጋር የሚቃረን ነገር ነው።

④ «ንግግሩ የራሱ የኢብኑ ተይሚያ ንግግር ነው፤ በመሳኢል ዚሂራም ማከፈር እንዳለ ይጠቁማል» ብለን (ኢፍቲራዶን) ወይም መላምታዊ በሆነ መንገድ ብንቀበለውም፤ ንግግሩ፡- ሸይኽል ኢስላም በተዕዪን ነጥሎ ግለሰቦችን የሚያከፍር መሆኑን የሚጠቁም ሳይሆን፤ በኢጥላቅ ወይም በጥቅል ከሚያከፍርባቸው ንግግሮቹ የሚካተት ብቻ ነው። በተዕዪን ነጥለው ለመሐከም በኢጥላቅ ሑከሙ ላይ መደገፋቸው ደግሞ ቂልነት ነው።

ሁለቱ የሑከም አይነቶች የሚለያዩ መሆናቸውንና በመስአላው ትክክለኛ አቋሙን ለማወቅ ሊረዱን ስለሚችሉ ቀጣዮቹን የሸይኽል ኢስላም ሁለት አባባሎች እንመልከት፡-

قال ابن تيمية رحمه الله كما في مجموع الفتاوى

(3/229):

وكنتُ أبيّنُ أنَّ ما نُقِلَ عن السلف والأئمة مِن إطلاق القول بتكفير مَن يقول كذا وكذا فهو أيضا حقٌّ؛ لكن يجب التفريقُ بين الإطلاق والتعيين

• «ከሰለፎችና ከአኢማዎች "ይህን፣ ይህን መሰል ንግግር የተናገረ ይከፍራል" እያሉ በኢጥላቅ (በልቆ) ተናግረውት ወደኛ የደረሰን ንግግራቸው ሐቅ መሆኑን እገልፅ ነበር፤ ነገር ግን በጥቅል የሚሰጠውንና በተዕዪን (በተናጠል)

የሚተሓኸመውን ብይን መለየት ግድ ነው» (አል ፈታዋ: 3/229 - መጅሙዕ ኢብኑ ቃሲም)

وقال أيضا رحمه الله تعالى «التَّكْفِيرُ لَهُ شُرُوطٌ وَمَوَانِعُ قَدْ تَنْتَفِي فِي حَقِّ الْمُعَيَّنِ، وَأَنَّ تَكْفِيرَ الْمُطْلَقِ لَا يَسْتَلْزِمُ تَكْفِيرَ الْمُعَيَّنِ إلَّا إذَا وُجِدَتْ الشُّرُوطُ وَانْتَفَتْ الْمَوَانِعُ

" [مجموع الفتاوى (12/487-488)].

«ሰውን ለማከፈር የራሱ የሆነ መስፈርቶችና ከልካይ ነገሮች አሉት፤ (ይህን፣ይህን የተናገረ ወይም የሰራ ካፊር ነው) እየተባለ በልቅ ሰዎችን ማከፈር፤ አንድን ሰው ነጥሎ ማከፈርን አያስይዝም (አያስፈርድም)፤ ነገር ግን (ኩፍር ውስጥ የወደቀ አካል ላይ) መስፈርቶች ከተሟሉና ለማከፈር የሚከለከሉ ምክንያቶች ከላዩ ላይ ከተወገዱ ካፊር ይደረጋል።» (መጅሙዑል ፈታዋ: 12/ 487: 488)

***** ***** ***** *****

ከላይ ካሳለፍናቸው የሰዎቹ መደገፊያ ከሆኑ የሸይኽል ኢስላም ንግግሮች መካከል አንዱ የሆነው ይህ ቀጣዩ ንግግር ማለትም እንዲህ የሚልበት:

«የአምስት አውቃት ሰላቶችን ግዴታነት ያላመነ ... ይህ ሰው ካፊርና ሙርተድ ነው፤ ተውበት ይጠየቃል፤ ከቶበተ ጥሩ፤ ካልሆነ ግን በአኢመቱል ሙስሊሚን ስምምነት ይገደላል። ላ ኢላህ ኢለ'ሏህ፤ ሙሐመዱን ረሱሉላህ ማለቱ አይጠቅመውም»

ይህና የመሳሰሉት ንግግሮቹም ለአንድ ሙዐይየን ዚሂራ በሆኑ መሳኢሎች ኢብኑ ተይሚያ ዐዝር ቢልጀህል እንደማይሰጥ ይጠቁማሉ ለሚለው አቋማቸው መደገፊያ ማድረጋቸው ትክክል አይሆንላቸውም። ምክንያቱም እነኚህ ንግግሮቹ በኢጥላቅ ወይም በጥቅል የበየኑባቸው አሕካሞቹ እንጂ በተዕዩን አንድ ግለሰብ ላይ የሚበይንባቸው ብይኖች አይደሉም። “ይህን ሽርክ ስራ የሰራ ካፊር (ሙርተድ) ይሆናል” እየተባለ የሰራውንና የሰሪው ሑክም በልቅ የሚበይኑባቸው የዑለማኦች ጥቅል አሕካሞች ላይ ደግሞ ሹሩጦችንና መዋኒዖችን የማያወሱባቸው በርካታ ኢጋጣሚዎች አሉ። ስለዚህ በልቅ የመጡ የሸይኹን አሕካሞች ለአቋማቸው መደገፊያ ማድረግ ትክክል አይሆንም። ኧረ

እንደውም ሸይኹ ራሱ ሁለቱን ነገሮች መቀላቀል ሳይሆን መለየት እንደሚገባ አጠንክሮ እንዲህ በማለት ተናግሯል፡-

وكنتُ أبيّنُ أنَّ ما نُقِلَ عن السلف والأئمة مِن إطلاق القول بتكفير مَن يقول كذا وكذا فهو أيضا حقٌّ؛ لكن يجب التفريقُ بين الإطلاق والتعيين

«ከሰለፎችና ከአኢማዎች "ይህን፣ ይህን መሰል ንግግር የተናገረ ይከፍራል" እያሉ በኢጥላቅ (በልቅ) ተናግረውት ወደኛ የደረሰን ንግግራቸው ሐቅ መሆኑን እገልፅ ነበር፤ ነገር ግን በጥቅል የሚሰጠውንና በተዕዩን (በተናጠል) የሚተሓኸመውን ብይን መለየት ግድ ነው» (አል ፈታዋ: 3/229 - መጅሙዕ ኢብኑ ቃሲም)

ስለዚህ ኢብኑ ተይሚያ ሰውን ሲያከፍር በዚሂራና በኸፊያ መካከል እንደሚለይ ይጠቁማሉ ብለው የሚያቀርቧቸው እነዚህና መሰል ንግግሮቹ የሰዎቹን ሀሳብ ከመደገፍ የራቁ ናቸው ማለት ነው።

ይልቁንም ከዝንባሌዎቻቸው ጋር እንደሚስማሙ የሚገምቷቸውን ንግግሮቹን ብቻ ሳይሆን በጉዳዩ የመጡ የሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ ረሒመሁሏህ አጠቃላይ ንግግሮችና ፈታዋዎችን ሰብሰብ አድርገው በሚገባ ካስተዋሏቸው ኢብኑ ተይሚያ ዘንድ ሰውን ማከፈር የሚባለው ጉዳይ በመስአላዋ ግልፅነት ላይ የተንጠለጠለ ወይም ያጠረ የሆነ ነገር ሳይሆን፤ ያ ኩፍር ላይ የወደቀው ሰውዬ ሑጃው ደርሶታል ወይም አልደረሰውም በሚለው ነጥብ ላይ ያጠረ መሆኑ በደንብ ይገለፅላቸዋል፤ ወሏሁል ሙወፍፊቅ።

●●●●●●●●●●●

ስለ ኢብኑ ተይሚያ ተማሪዎቹ የሰጡት ምስክርነት

قال الإمام ابن رجب في "ذيل طبقات الحنابلة "نقلا عن الذهبي قوله : «وَمَذْهَبُهُ - أي :شيخ الإسلام قدَّس اللهُ رُوحَه - تَوْسِعَةُ العُذْرِ للخَلْقِ، وَلَا يُكَفِّرُ أَحَدًا إلا بَعْدَ قِيامِ الحُجَّةِ عَلَيْهِ»

- የሐንበሊያ ዑለማኦችን ታሪክ ያሰፈረበት "ዘይሉ ጦበቃቲል ሐናቢላ» የተሰኘው ኪታቡ ላይ ከኢማም አዝ ዘሀቢይ ይዞ ኢማም አዝ ዘሀቢይ እንዲህ ማለቱን አውስቷል፡- «ሸይል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ - ነፍሱን አላህ ያፅዳለትና -

መዝሀቡ፡- የዑዝርን በር ለፍጡሩች ማስፋት ነው። ሑጃ ከቆመበት በኋላ እንጂ ማንንም ሰው አያከፍርምም ነበር።»

• ኢማም አዝ ዘሀቢይም "ሲየር አዕላም አን ኑበላእ: 15/88" ላይ ዛሂር አስ ሰርኸሲ ከተባለ ሰው በመያዝ ዛሂር እንዲህ ማለቱን አስተላልፏል፡-["አቡል ሐሰን አል አሽዐሪይ በቻዳድ የሚገኘው ቤቴ ውስጥ ሆኖ መሞቻ ዕለቱ በቀረበ ጊዜ ጠራኝና እሱ ዘንድ ስደርስ እንዲህ አለኝ፡-

اشهد عليَّ أني لا أكفِّر أحدًا من أهل القبلة؛ لأن الكل يشيرون إلى معبودٍ واحد،وإنما هذا كله اختلاف العبارات

"ከአህሉል ቂብላ አንድንም ሰው የማላከፍር መሆኔን ምስክሬ ሁን፤ ምክንያቱም የሀሳብ ልዩነት እንጂ ሁሉም ወደ አንድ አምላክ ነው የሚያመላክቱት"

قُلْتُ ـ أي :الذهبي ـ :وبنحو هذا أَدِينُ، وكذا كان شيخنا ابنُ تيمية في أواخر أيامه يقول أنا لا أُكَفِّرُ أحدًا من الأمة"، ويقول «قال النبي ﷺ لا يحافظ على الوضوء إلا مؤمن» فمن لازَمَ الصلوات فهو مسلمٌ

እኔ (አዝ - ዘሀቢይም) ይህንኑ በሚመስል እምነት አምናለሁ ባይ ነኝ፤ ልክ እንደዚሁ ሸይኻችን ኢብኑ ተይሚያም በህይወቱ መጨረሻ ላይ እንዲህ ይል ነበር፡- (እኔ ከዚህ ኡም - ማህ አንድንም ሰው አላከፍርም)፤ እንዲህም ብሏል: (ነቢዩ ﷺ: «ውዱኡን አጥብቆ የሚይዝ የለም አማኝ ቢሆን እንጂ» ብለዋል፤ ስለዚህ ሶላትን አጥብቆ በመያዝ ዘወትር የሚሰግድ የሆነ ማንኛውም ሰው ሙስሊም ነው)]

المصدر

: (15/88: سير أعلام النبلاء)

***** ***** ***** *****

ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ በተከፊሮች እይታ

በዑዝር ቢል ጀህል መስአላ ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያን በደንብ የሚያውቁት በውጩ አለም የሚገኙና በሀገር ውስጥ ያሉ ተከፊሪዮች እሱን ወይ ጠማማ ጀህሚይ፣ ወይም ሙርጂእ አለያም የጀህሚይ ጠበቃ አድርገው ነው የሚያዩት። ከፊል ተከፊሪዮችና ሰለፊዮች ነን የሚሉት ጫጩቶቻቸው ግን

"ኢብኑ ተይሚያ ዑዝርን የሚሰጠው ለተዕዚብ እንጂ ለሁክም ስላልሆነ ጥርት ያለ ሙወሂድ አድርገን ነው የምናየው" ይላሉ። ይህን ሀሳብ ይጠቁማሉ ብለው የሚያምኑባቸውን ንግግሮቹንም እንደመነሻ ሲጠቀሙ ይታያሉ።

ሀቂቀተን የላይኞቹ ተከፊሪዮች ኢብኑ ተይሚያን ጀህሚይ ማለታቸው ቢያስከፋንም፤ ከንግግሮቹ ኡዝር ቢል ጀህልን እንደሚያፀድቅ የተገነዘቡት ግንዛቤያቸው ግን ከታችኞቹ ተከፊሪዮች በጣም የተሻለና ትክክለኛ የሆነ ግንዛቤ ነው።

والكلُّ ضُلَّالٌ

ለመሆኑ ኢብኑ ተይሚያን ጀህሚይ ወይም ሙርጂእ አድርገው የሚያዩት ተከፊሪዮች ለአቋማቸው እንደመነሻ የሚጠቀሟቸው ንግግሮቹ ምን አይነት ንግግሮች ይሆኑ ይሆን!?

ንግግሮቹ አዲስ አይደሉም። ይልቁንም እነ ሸይኽ ዐብዱረሕማን አስ ሰዕዲ፣ ሸይኽ ሙሐመድ ቢን ሷሊሕ አል ዑሠይሚን፣ አል ኢማም አስ ሰለፊ ሙሐመድ ናሲሩዲነል አልባኒ፣ ሸይኽ ሙሐመድ አማን አልጀሚ፣ ሸይኽ ሙቅቢል አልዋዲዒ ረሒመሁሙሏሁ ጀሚዓ፣፣፣፣ እና መሰሎቻቸው በመስአላዋ ላይ አቋማቸውን ሲገልፁ የሚደገፉባቸው የሸይኹ ተቅሪራቶች ናቸው።

ለምሳሌ ያህል፦

① (መጅሙዑል ፈታዋ: 12/489 - 501) ላይ አንድን ግለሰብ የተከፊር መስፈርቶች እስካልተሟሉበትና ከልካዮቹም እስካልተወገዱ ድረስ በተዕዩን ነጥሎ ማከፈር እንደማይፈቀድ ካወሳ በኋላ እንዲህ ይላል፦

«ለዚህ ጉዳይ ማስረጃው ቁርኣን፣ ሐዲሥ፣ ኢጅማዕና ኢዕቲባር ነው።»

ከዚያም የተወሰኑ መረጃዎችን ይጠቅስና ቀጠል አድርጎ እንዲህ ይላል:

«በሐዲስ በሚብራራው የአላህ መፅሀፍ የነቢዩ ﷺ ኡምማ በስህተትና በመርሳት ለሚሰሩት ጥፋት አላህ ምህረት ያደረገላቸው መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፤ ይህ ደግሞ ጥብቅ የሆነ ጥቅል ብይን ነው፤ ከዚህ ኡማ የሆነን ስህተተኛ ቅጣት እንደሚረጋገጥበት የሚጠቁም ሸሪዓዊ መረጃ የለም።... ይህ ከታወቀ፤ የሚናገሩት ንግግር ያለ ጥርጥር ኩፍር ቢሆንም መልእክተኞችን የተቃረኑ መሆናቸው በእሷ አስረጅነት የሚገለፅባት ነቢያዊ ሑጃ እስከሚደርሳቸው ድረስ ከእነዚህ ጃሂል ከሆኑ ሰዎችና ከመሰሎቻቸው የሆነን አንድን ግለሰብ በተዕዩን ነጥሎ ማከፈርና

ከኩፋሮች ሆነሃል ብሎ መበየን አይፈቀድም። ይህ አባባል አጠቃላይ ሙዐይየኖችን (ያለ ቅድመ ሁኔታ) ማከፈር እንደማይቻል የምንገልፅበት ብይን ነው። ከሙስሊሞች የሆነ ማንኛውም ሙስሊም ቢያጠፋም ቢሳሳትም ሑጃ እስከሚደርሰውና ቅኑ መንገድ እስኪገለፅለት ድረስ ለማንም አካል ይህን ሰው ማከፈር አይፈቀድለትም። እነኚህ ቢድዓዎች ከፊሉ ከከፊሉ በጣም የከበደ (የከፋ) ከመሆኑ ጋር ሌሎች ዘንድ የማይገኘው ኢማን አንዳንድ የቢድዓ ሰዎች ዘንድ ሊገኝ ይችላል። ስለዚህ ሑጃ እስኪቆምበትና ቅኑ መንገድ እስከሚገለፅለት ድረስ ከሙስሊሞች የሆነን ማንኛውንም ግለሰብ ለማከፈር መብት ያለው አንድም አይነት ሰው የለም። እምነቱ በየቂን የተረጋገጠለት ሰው፤ በጥርጥር እምነቱን አይነጠቅም፤ ይልቁንም ሑጃ እስከሚደርሰውና ሹብሃው እስኪወገድለት ድረስ ሙስሊምነቱን አይቀማም»

② (መጅሙዑል ፈታዋ 12/487) ላይም እንዲህ ብሏል:

«ሰውን ማከፈር የራሱ የሆኑ መስፈርቶችና ከልካይ ነገሮች አሉት፤ (ይህን፣ይህን የተናገረ ወይም የሰራ ሰው ካፊር ነው) እየተባለ በኢጥላቅ (በልቅ) ሰዎችን ማከፈር፤ አንድን ሰው በተዕዩን ነጥሎ ማከፈርን አያስይዝም፤ ነገር ግን (ኩፍር ላይ የወደቀ አካል ላይ) መስፈርቶች ከተሟሉና ለማከፈር የሚከለክሉ ምክንያቶች ከተወገዱ ካፊር ይደረጋል። ይህን ጉዳይ የእነ ኢማሙ አሕመድ የፐራክቲካል አቋማቸው ያብራራዋል። ኢማሙ አሕመድን ጨምሮ በኢጥላቅ ያከፈሩ አጠቃላይ አኢማዎች የኩፍር ንግግሩን የተናገሩ አብዛኞችን ሰዎች በተዕዩን አላከፈሯቸውም። ኢማሙ አሕመድን ምሳሌ ብንወስድ ቁርኣንን መኽሉቅ ነው ብሎ እንዲናገርና የአላህን ሲፋዎች እንዲያወግዝ ጥሪ ያቀርቡለትና ያስገድዱት የነበሩ ጀህሚያዎች ጋር በቀጥታ ይፋጠጥ ነበር። ጀህሚያዎች አሕመድን ጨምሮ በጊዜው የነበሩ ዑለማኦችንና የነሱን አቋም ያልተቀበሉ ሙእሚኖችን በመደብደብ፣ በማሰር፣ በመግደል፣ ከሃላፊነት ቦታ በማግለል፣ ሪዝቃቸውን በማቋረጥ፣ ምስክርነታቸውን ውድቅ በማድረግና ለጠላት አሳልፎ በመስጠት ይፈትኗቸውና ያሰቃዮቸውም ነበር። ምክንያቱም በጊዜው የነበሩት ጀህሚያ የሆኑ የሀገር መሪዎችና ዳኞች እነሱን ያልተስማማ፣ እንደነሱ ጀህሚይ ያልሆነን፣ የቁርኣንን መኽሉቅነት ያልተቀበለና የአላህን ሲፋዎች ባጠቃላይ የማያወግዝ የሆነን ማንኛውንም ሰው ያከፍሩ ነበር። ... ይህ ጀህሚይነት መሆኑ የታወቀ ነው። አቋሙን (ጀህሚይነትን) እንዲቀበሉ ለሰዎች ጥሪ ማቅረብ አቋሙን አቋም አድርጎ ከማመን በላይ የከፋ ነው። የተቀበሉ ሰዎችን በመልካም መመንዳትና የማይቀበለውን ሰው መቅጣት ደግሞ ወደሷ ጥሪ በማቅረብ ላይ ብቻ ከማጠር የከፋ አደጋ ነው። (ይህ ሁሉ ከመሆኑ ጋር) ኢማም አሕመድ እሱን

ይደበድበውና ያስረው ለነበረው የጀህሚያ ኽሊፋና ለሌሎቹም ዱዓ ያደርግላቸውና ኢስቲሻፋርም ይለምንላቸው ነበር፤ እሱ ላይ ያደረሱበትን በደልና እንዲቀበለው ወደሱ ይጠሩትና ያስገድዱት የነበረውን ያን የኩፍር ንግግርም ይቅር ብሏቸዋል። እነኚህ ሰዎች ከኢስላም የወጡ ሙርተዶች ቢሆኑ ኑሮ ለነሱ ኢስቲሻፋር መጠየቁ አይፈቀድለትም ነበር። ምክንያቱም ለኩፋሮች ምህረት መለመን በቁርኣን፣ በሐዲስና በኢጅማእ የማይፈቀድ ነውና። (በዚህ ጉዳይ) ከኢማሙ አሕመድና ከሌሎች አኢማዎች የተገኙ ንግግሮችና ተግባሮች ባጠቃላይ "ቁርኣን መኽሉቅ ነው፤ አላህ በኣኺራ አይታይም፣፣፣" ይሉ የነበሩ ጀህሚያዎችን በተዕዩን ነጥለው ያከፍሩ እንዳልነበር በግልፅ ይጠቁማሉ። የጀህሚያዎችን ንግግር የሚናገሩ የተወሰኑ ሰዎችን በተዕዩይን ያከፈራቸው መሆኑን የሚያመላክት ወሬ በርግጥ ከአሕመድ ተዘግቧል፤ ሆኖም በዚህ ጉዳይ (ሁለት አይነት አቋም እንዳለው ተደርጎ በሚታሰብ መልኩ) ሁለት አይነት ዘገባዎች ከእሱ መፅሳቱ፤ ይህ ችግር አለበት (ትክክል አይደለም)። ወይም ደግሞ በተፍሲል ለያይተን ልናየው ይገባል፤ ማለትም፡- በተዕዩይን ያከፈረው ሰው ሹሩጦች መሟላታቸውንና መዋኒዖች መወገዳቸውን የሚጠቁም መረጃ ስለተገኘበት ነው ይባላል፤ በተዕዩይን ያላከፈረው ሰው ደግሞ መስፈርቶቹ ስላልተሟሉበትና ከልካዮቹ ከላዩ ላይ ስላልተወገዱ ነው ይባላል ማለት ነው...»

③ «አንድ ንግግር ኩፍር መሆኑ ያን ንግግር በጅህልና እና በተእዊል የተናገረው ሰው ሁሉ ይከፍራል ማለትን አያስይዝም። ምክንያቱም አንድ ግለሰብ ላይ የኩፍር (ብይን) መረጋገጡ በሰውየው ላይ በኣኺራ የቅጣት ዛቻ ይረጋገጥበታል ብሎ እንደመበየን ነውና። ይህም (ማለትም በተዕዩይን ማክፈር) ሌሎች ቦታዎች ላይ በሰፊው እንዳብራራነው የራሱ የሆነ መስፈርቶችና ከልካዮች ያሉት ነገር ነው።» (ሚንሃጁ አስ ሱንና አን ነበዊያ: 5/240)

ወቢላሂትተውፊቅ።

አቡ ዐብዲላህ ሰዒድ ሙሐመድ አሕመድ

5/9/1444